# ትግላችን ዜና


አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

Prepared by the Ethiopian Students Union
in Europe

P.O.Box 3198, 10364 Stockholm 3 SWEDEN






## የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግል
## የክፍላተ ሀገር ዜና


VOL.4 N°3
APRIL 1977

ቁጥር 3
ሚያዝያ 1969

## ይ_ዞ_ታ


- መግቢያ
- የበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሃገር ሁኔታ
- የወለጋ ክፍለ ሃገር
- ስለ ሰርጐ ገቦች
  በተለይ በአሬሮ፣ በጀምጀምና በነገሌ ቦረና
  አውራጃዎች
- የገሙ ጎፋ ክፍለ ሃገር
- የከፋ ክፍለ ሃገር


## ተጨማሪ


- ጆን—ኤች ስፔንሰር የተባለ አሜሪካዊ
  የኢትዮጵያን አብዮት ለመ ቀለበስ ስለ
  ሚቻልበት ዘዴ ለአሜሪካ ምክር ቤት
  /ሰኔት/ ያቀረበው ራፖር ሲጋለጥ፡፡

## መግቢያ

እነዚህን መስመሮች ስንጽፍ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ አብዮታዊ ትግል እየተካሄደ ነው::

በገጠር ኢትዮጵያ ሰፊው ገበሬ የሚያደርገው ፀረ ባላባት ትግልም ሆነ በከተማ ከታሸጉት አድሃሪያች ጋር የከተማው ህዝብ የሚያካሄደው ተጋድሎ ስማያዳግም ሁኔታ መልክ እየያዘ ነው::በንቃት በድርጅትም ሆነ በትጥቅ የማይናቅ እርምጃዎች ተደርገዋል::

ይህ በሚሆንበት ስአት ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ እየነቃ ፣ እየተደራጀና እየታጠቀ ሃይሉን የሚሰበስበውን ያህል ለፀረ አቢዮት የተሰለፉ ሃይሎች በበኩላቸው ሃይላቸውን በማስተባበርና በአብዮቱ ላይ ለመዝመት እየተዘጋጁ ናቸው::

የትግሉ አዝማሚያ በከፍተኛ ፍጥነት ወደ መጨረሻው ፍልሚያ እየተቃረበ የምንሄድበት አዝማሚያ ዛሬ የማያጠራጥር ሃቅ ሆንዋል::የዚህም የመጨረሻ ትንንቅ ውጤት የኢትዮጵያን ህዝቦች የነፃነት ትግል መሳካትና አለመሳካት ይወስናል::

የፀረ አብዮት ሰፈር የሚያካሄዳቸው ትግሎች ዛሬ የተለያዩ መልኮች ይዘው ይታያሉ::ባንድ በኩል ባገራችን የሚገኙት የባላባቱ የኢምፔሪያሊስቶችና የቢሮክራቲክ ከበርቴ ጥቅም ጠባቂዎች የታጠቀ የፀረ አብዮት ትግል ሲያካሂዱ ፣ በሌላ በኩል ጎረቤት አገሮች በተለያዩ ምክንያቶች ተገፋፍተው በነዚህ ሃይሎች እርዳታቸውን በሰፊው በመለገስ ላይ ናቸው::ከመሃከላቸው በተለይ የሱዳን መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር ቀጥተኛ ግጭት ለመፍጠር ወደ ኋላ የሚል አይመስልም::

የኢትዮጵያ ህዝቦችና የኢትዮጵያ ተራማጆች ይህንን የተቀናበረ የፀረ አቢዮት ሃይሎች ዘመቻ የሚመከቱበት የትግል መሥመር አላቸው::ይኸውም በዛሬው የትግል ደረጃ በውስጥ ጠላቶች ላይ አትኩሮ ንቃት ድርጅትንና ትጥቅን ማጠናከር:: የጎረቤት አገሮች ለመጪር የሚፈልጉትን ጦርነት ለመቋቋም መዘጋጀት ፣ ነገር ግን እነዚህ ጠላቶች የመጀመሪያ ጠላቶቻችን ስላልሆኑ ከነርሱ ጋር ጦርነት ቢነሳ የመደብ ትግሉን ስለሚያቀዛቅዝና የውጭ መንግሥታትን ጣልቃ ገብነት በሰሚጠራ ይህ ጦርነት እንዳይነሳ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ::በሌም ለውስጥ አድሃሪያች በነዚህ መንግሥታት የሚሰጠውን እርዳታ ባጭሩ ለመቁጨት መታገል ናቸው:: ይህን ካደረገ ፣ ማለትም የጊዜውን ዋና ጠላቶች ለይቶ ከመጣ ፣ በዚህ ትግል ውስጥ ንቃት ፣ ድርጅትና ትጥቅን ካራመደ የኢትዮጵያ ህዝቦች የነፃነት ትግል ድል የሚቀዳጁበትን የትግል ፋና ይዘዋል ለማለት ይቻላል::አብዮታዊያን ለመጨረሻው የትግል ፍልሚያ የሚዘጋጁት በዚህ አንፃር በሚያደርጉት ትግል ነው::



ዛሬ በኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ውስጥ የተወሰነም ቢሆን ሚና ለመጫወት ከተፈለገ ደግሞ ባገራችን ያለውን ውስብስብ ሁኔታ አበጠርጥሮ ማወቅ ያሻል እንላለን::በዚህ ደረጃ በየክፍለ አገሩ ያሉትን የትግል ሁኔታዎች ማወቅ ከፍተኛ ቦታ ይኖረዋል ብለን ስለገመትን በዚህ የትግላችን ዜና እትም ካገር ቤት የተገኙ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን አትመናል::

ይሁንናም ብዙ ጠቃሚ ጽሑፎች ያዘሉ ቢሆኑም ከጽሑፎቹ መረዳት እንደሚቻለው ባለፈት ሁለት ወራት ስለተካሄዱት ከፍተኛ ትግሎችና የትግል ውጤቶች እንዲሁም በተፈሪ በንቴ በነአለማየሁ ተጠንስሶ በአብዮታዊ እርምጃ ስለተደመሰሰው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አያትቱም::

በኛ ግምት የዚህ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መክሸፍና በደርጉ ውስጥ ስርገው የገቡ አድሃሪ መኰንኖች ቢያንስ በደርጉ አመራር በከፊል መወገዳቸው በማያዳግም ሁኔታ ለትግላችን አዲስ ምዕራፍ ከፍተዋል::ከዚያን ጊዜም ጀምሮ የተካሄዱትም ትግሎች ልዩ ሂደት እንደተከተሉ አንጠራጠርም::ሆኖም ግን ለዚህ ለአዲስ የትግል ምዕራፍ ብቁ ለመሆን ፣ ለወደፊትም ለምናካሄደው ተጋድሎ ጠንካራ መሠረት ይኖረን ዘንድ ፣ እንደኛ ይህን አዲስ የትግል ምዕራፍ ለመጀመር ያስቻሉንን ሁኔታዎች እንዲሁም ደግሞ ይህ ምዕራፍ ሲከፈት ትግላችን የደረሰበትን ደረጃ በሚገባ ማወቅና መረዳት አለብን ብለን እናምናለን::በዚህ መጽሔት የቀረቡት ጸሁፎች በዚህ አንጻር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ ብለን ስለገመትን ለአንባቢያቻችን አቅርበናቸዋል::

በሌላ በኩል በቅርብ ስለተከናወኑት ድርጊቶች ካገር ቤት ጋዜጦችም ሆነ ከነፃ ጋዜጦች የተገኙትን በልዩ እትም መልክ አቅርበናል::በዚህናው መጽሄት የቀረቡት ጽሑፎች በልዩ እትሞቻችን ያስተላለፍናቸውን ዜናዎች መሠረታዊ ይዘት ለመረዳት እንደሚያግዙ አንጠራጠርም::ስለሆነም በነዚህ ፅሑፎችም ሆነ በተላለፉት ዜናዎች ላይ ሰፊው የማህበራችን አባላት የሃሳብ ለውውጥ ካደረጉ ፣ ሂስና አስተያየት ካቀረቡ ፣ ማህበራችን በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ፣ ከሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በቅርብ የተያያዘና ከሰፊው ህዝብ የቀን ተቀን ትግል ጎን ቁሞ ወደፊት የሚራመድ ማህበር ይሆናል::ይህም ማለት ፣ ወደፊት ለሚጠብቀን መራራ ትግሎች ብቁ ለመሆን እንችላለን ማለት ነው::

በቀላሉ ልንረዳው እንደምንችለው ዛሬ አገራችን ያለችበት ሁኔታ ከመቼውም ይበልጥ ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር መያያዝን ይጠይቃል::ዛሬ ጠላቶቻችን ሃይላቸውን በመሰብሰብና በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ወሳኝ ዘመቻ በማዘጋጀት ላይ ናቸው:: በዚሁ መጠን ሰፊው ህዝብ ንቃቱን እያዳበረ በድርጅት እየተራመደ ትጥቁንም ማስፋት ጀምርዋል:: የመጨረሻው ወሳኝ ፍልሚያ ተቃርቧል::ለዚህ ወሳኝ ፍልሚያ አብዮታዊያን መዘጋጀት አለባቸው::ማለትም ስለ አገራችን ሁኔታ ከመቼውም ይበልጥ

ዛሬ ጠጋ ብለን መመራመር ፣ ካለም ህዝቦች ትግል መማር ፣ በአብዮታዊ የትግል መገረብ ታንጸን ለብሄራዊ ነፃነታችን ፣ ራሳችንን በራሳችን ችለን የነፃ የተደራጀና የታጠቀ ትግላችንን የምናራምድበትን ሁኔታ መፍጠር አለብን ማለት ነው።። ይህ ከሆነ ፣ ባለፉት ዓመታት የሰራው ጥቀን ህዝብ ትግል ድል በድል እንደተቀናጀ ሁሉ ከወደፊትም ትግል አሸናፊ ሆኖ የማይወጣበት ምንም ምክኒያት ሊኖር አይችልም።።

## ትግላችን ዜና

ጥር 23 ቀን 1969 ዓ.ም.

## የበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ሁኔታ

በአሁኑ ጊዜ የበጌምድርና ሰሜንን ክፍለ ሀገር ሁኔታ ለማጥናት አብዮቱ በውጥረት ላይ በሚገኝበት ደረጃ ላይ ተመስርቶ እንደሚከተለው ከፋፍሎ ማየት ይቻላል ። አብዮቱ ከፍተኛ ውጥረትና አደጋ ያለበት በጎንደር ዙሪያ አውራጃ፣ በጭልጋ አውራጃ፣ በወገራ አውራጃና በሰሜን አውራጃ ነው ። ከእነዚህ አውራጃዎች ዝቅ ባለ ሁኔታ ደግሞ በደብረ ታቦር፣ በጋይንትና በሊቦ አውራጃዎች አብዮቱ ውጥረት ላይ ነው ። የጎንደር ከተማም እራሱን የቻለ የውጥረት ቀበሌ ነው ።

### ጭልጊያ አውራጃ፣

የአብዮት ኃይሎች፣ ወታደሩን በደፈናው በዚህ ውስጥ ከመደብነው በዚህ አውራጃ በአይከል ከተማ አንዱ የሻምበል ፈጥኖ፣ እንዲሁም በመተማ ከተማ ሌላ የጦር ኃይል ይገኛሉ ። በቀርቡ 190 ያህል የአባት ጦር አባሎች ተመልምለው ጥቂቶቹ በጫኪት፣ ቀላ ዱባና ጉርጉራ አካባቢ ይገኛሉ ። ከሱዳን በሚዋሰነው በቀላው ክፍል በርከት ያሉ ያልታጠቁ ያልተደራጁ በርካታ ወዛ አደሮች አሉ ። በገጠሩም ሲበዘበዙ የነበሩ አራሽ ገበሬዎችና ጥቀን ብጠረሰቦች/ ነገደ ቀማንት/ ይገኛሉ ። ነገር ግን አብዮቱ ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ሕዝቡ ስለ አብዮቱ ገለጻ ከማግኘት ይልቅ በፀረ–አብዮት ፕሮፓጋንዳ ሲበከል ስለቆየ በዚህ አውራጃ የአብዮት ኃይሎች ለአብዮታዊ ትግል ዝግጁት አላደረጉም ።

የፀረ አብዮት ኃይሎች፣ እነዚህ በአሁኑ ጊዜ ተሰብስበው የሚገኙት በኢ.ዲ.ሕ. ሥር ነው ። በተለይ በዚህ አውራጃ ያለውን ግንባር የሚመራው ሻለቃ በመባል እራሱን የሾመው የዱር ከበርቴ አጤናው ዋሴ የሚባል ሲሆን እነ ግራዝማች አየለ ቸኮልና ሌሎችም በእሱ አካባቢ ይሠራሉ ። የፀረ አብዮት ኃይሎች መሠረት ሊጥሉ የቻሉባቸው ክፍሎች ፈረሰኛ ጉልተኛ፣ ጭቃ ሹም በመባል የሚታወቁትን ሀብታም ገበሬዎች ሲሆን በሃይማኖት በኩል በተለይ በዚህ አውራጃ ለብዙ ዘመናት እራሱን ችሎ የኖረው ማህበረ ሥላሴ የሚባለው ገዳም ለኢ.ዲ.ሕ. ድጋፉን በማሳየ ጭቁኑም ገበሬ በሃይማኖት ተጽእኖ የፀረ–አብዮት መሣሪያ ሆኗል ። ስለዚህ የፀረ–አብዮት ኃይል ያሰለፋቸውን ለምን እንደሚታገሉ የሚያውቁና /ሲበዘበዙ የነበረውን ለማስመለስ/ የተወናበዱትም ቁጥራቸው ከፍ ያለ ነው ። ይህም በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በአውራጃው ይህ ኃይል የበላይነትን ይዞ ይገኛል ። በቅርቡ ፈንጂ በመቅበር ከአዲስ አበባ ጎንደር የሚሄደው መንገድ ድረስ /ማክሰኚት/ መኖሩን ያሳየው ይህ ኃይል ከጎንደር ደቡብ በጉርጉራ ጫኪት ቀላ ዱባ አካባቢ፣ በደለጊ ውስጥና አካባቢ፣ በአይከል አካባቢና፣ ከአይከል ወዲያ እስከ መተማ ድረስ ያለውን ቦታ በቁጥጥሩ ሥር ያደረገ ይመስላል ። አይከል ያለው አንዱ ሻምበል በተለያዩ ምክንያቶች ከከተማው ወጥቶ እስከ አሁን አላጠቃም፣ መተማ ያለው ጦር ለመጀመሪያ ጊዜ ከመተማ ውጭ ተንቀሳቅሶ በጎንደር መንገዱ 12 ኪሎ ሜትር ላይ የምትገኘውን ኩኪት ከኢ.ዲ.ሕ. አስለቅቋል ። ጦሩ እዚያ መቆየት ስላልቻለ ተመልሶ በኢ.ዲ.ሕ. እጅ ሊገባ ይችላል ። ቀደም ባለ ጊዜ በአይከል አካባቢ ያለው " ሕዝባዊ ጦር " ተገሸ ተንቀሳቅሶ ከኢ.ዲ.ሕ. ጦር ጋር ተጋጥሞ ነበር ። ነገር ግን ከዚያ አካባቢ ይህንን ኃይል እስከ መጨረሻው ሊያስወጣ አልቻለም ።

ደሴን ለሁንም በኢ.ዲ.ሕ. ኃይል እንደተያዘች ነው ። ይህም ለጣና ሀይቅ ለኢ.ዲ.ሕ. አንዱ በር ከፍ ቶለታል፣ በዚህ በመጠቀም ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገርና ወደ ደብረ ታቦር፣ ጋይ ንት መመላለስ ያስቻለዋል ።

በዚህ አውራጃ የፀረ—አብዮት /ኢ.ዲ.ሕ./ ኃይል እንቅስቃሴ ሲታይ ፈጣንና ሰፊ ነው ። ከመተማ ደበብ አካባቢ /ተሃ/ የተነሳው ጦር በቋራ በኩል አድርጉ ለመጀመሪያ ጊዜ በጎንደር አንጋጠ ላይ ደለጊን ያዘ ሲባል በወቅቱ ኃይል ሰላል ነበረ ያሉት ጦረኛ የአብዮት ጦር /100/ ወደዚያ ሲላክ ባልታሰበ ሁኔታ የአውራጃውን ዋና ከተማ አይከለን ያዘ ። ከዚያም ከአዲስ አበባ አንዱ ሻምበል ፈጥኖ ደራሽ ወጥቶ ከተማውን ለማስለቀቅ ሲሄድ በጎንደር መንገድ ከአይከል 20 ኪሎ ሜትር ላይ በደፈጣ ውጊያ ስለ ታያዘ ቦታ ሰበው ጊዜ ባይደርስም ከአንዱ ቀን ውጊያ በኋላ ከተማ ሲገባ የኢ.ዲ.ሕ. ኃይል አፈገፈገ፤ ግን ከዚያም አካባቢ ባለማውጣት በደለጊና በአይከል መሀል ባለው አካባቢና በመተማ መንገድ አካባቢ ሲዘዋወር ቆየ ። እስከ አሁን የፈጥኖ ጦር አይከል ከተማ ተቀምጧል ። " የሕዝባዊ ጦሩም" እምብዛም ሊሰራ አልቻለም፣ ግን የኢ.ዲ.ሕ. ጦር የደረሰበትን ጊዜያዊ መሸነፍ እንደገና እያጠናከረ ነው ። ከላይ የተጠቀሱት በቅርቡ የሚወሰዱባቸውም እርምጃዎች ይህንን ያሳያሉ ።

## ጎንደር ዙሪያ አውራጃ

የአብዮት ኃይሎች፣ ከጎንደር ከተማ 25 ኪሎ ሜትር ላይ ትከል ድንጋይ በሚባል ቦታ አንዱ ሻምበል ነበልባል፣ አንዱ ሻምበል ፈጥኖ ደራሽ ጦር ይገኛል እንዲሁም አብደራፊ ከተማ የምድር ጦር ነበር ። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ይህ ጦር ወደ መተማ መሄዱ ይወራል ። በተረፈ በቀረው ክፍል ከሱዳን በሚዋሰኑት ቀበሌዎች ያልታጠቁ ያልተደራጁ ወዝ—አደሮች አሉ ። በዚህም አውራጃ ጥቂት ገበሬዎች መኖራቸው ገለጸ ነው ። በጎንደር ከተማ አካባቢ ከዚህ በፊት ሲጨቀኑ ሲናቁ የነበሩ ቅጣንቶች አሉ ። የአብዮት ኃይሎች ሁኔታ ከዚህ በፊት ሰላለው አውራጃ እንደተባለው ነው ።

የፀረ—አብዮት ኃይሎች፣ በዚህም አውራጃ የፀረ—አብዮት ኃይሎች በኢ.ዲ.ሕ. አካባቢ ነው የተሰለፉት ። በዚህ አካባቢ ያሉት የኢ.ዲ.ሕ. ቀንደኞች በዋንኛም ነጠ የሚቀነባበሩ ናቸው ይባላል ። የፀረ—አብዮት ኃይል በተለይ የተጠናከረው በትከል ድንጋይ አካባቢ ነው ። በርከት ያሉ ምሽጎችን ይዟል ። የዚህ ኃይል መሠረት በጎንደር ዙሪያ አውራጃ የሚታየውን አይነት ነው ። በዚህ በኩል ያለው የኢ.ዲ.ሕ. ጦር ከሱዳን አካባቢ ሲነሳ ከነቢትወደድ አዳነ ጦር ጋር አንድነት የነበረ ይመስላል ግን በኋላ ወደ ደበብ ተገንጥሎ ሲገሰግስ ከጎንደር 25 ኪሎ ሜትር ላይ ነው ሊገታ የቻለው ። ከቅርብ ጊዜ በፊት ለብዙ ቀናት በምሽጉ ተቆጦ ሲታከስ የነበረው በአፍ ጦር አጥቂነት ውጊያው እንደገና ተቀስቅሶ ደህና ጠላት ከተገፋ በኋላ በልዩ ልዩ ምክንያት ግስጋሴውን በመግታት እንዲያውም በመጨረሻ ወደነበረበት እንዲመለስ ሆኗል ። በዚህ ጊዜ በመጠኑም ቢሆን የ " ሕዝባዊ ጦር " አብሮ ተሰልፎ ነበር ።



## ወገራ አውራጃ

የአብዮት ኃይል፣ ቀደም ሲል በሀመራ ከነበረው ጦር ጥቂት ሲደመሰስ ከፊሉ ከከሃዲው ኩሉነል ጋር ሲሄዱ የተቀረው ተከፋፍሎ በተለያየ አቅጣጫ ካለው የመንግሥት ጦር ጋር እየተደባለቀ ነው ይባላል ። በተረፈ በዳባት አነስተኛ ጦር አለ ። በሀመራ የነበረት የታጠቀ ወዝ አደሮች አሁን ሁኔታቸው እንዴት እንደሆነ ገለጸ አይደለም ። ግን ባይደመሰሱ አይቀሩም ። ጥቂት አርሶ አደሮች እንደሌሎቹ አውራጃዎች ሁሉ አሉ ። በዳባት አካባቢ ምናልባት ትንሽ " ሕዝባዊ ጦር " ይኖር ይሆናል ። በአጠቃላይ በዚህ አውራጃ የአብዮት ኃይሎች በጣም ደካማ ናቸው ።

የፀረ—አብዮት ኃይል፣ በዚህ አውራጃም ይህ ኃይል የተሰበሰበው በኢ.ዲ.ሕ. አካባቢ ነው ። ዋናው የዚህ አውራጃ የኢ.ዲ.ሕ. ጦር መሪ ለብዙ ዓመት የአውራጃው አስተዳዳሪ የነበሩ ቢትወደድ አዳነ መኮንን ናቸው ። የፀረ—አብዮት ኃይል መሠረት በዚህም አውራጃ ያው ጉልተኛ፣ ፈረስና ነጭለባሽ የሚባሉት ሀብታም ገበሬዎች ናቸው ። የተወናበደም ደሀ ገበሬ አብሯቸው ተሰልፏል ። በዚህ አውራጃ ውስጥ ከዳባት ወደ ምዕራብ 25 ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ ጃኖራ የሚባል ቦታ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበልባል ከፀረ—አብዮት ኃይሎች ጋር ተጋጥሞ ሊደቃም ባለመቻሉ ወደ ዳባት ከተመለሰ በኋላ ቢትወደድ አዳነ በአውራጃው አብዛኛው ደጋ ክፍል እንደልብ ይፈነጭበታል ። በቅርቡ አዲረመጥ የምትባል ከተማ ሲይዙ የገጠር የመሬት አዋጅ የሚሻር የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጅ የሚሻር አዋጅ አውጥተው ሹም ሽር እስከማድረግ ደርሰዋል ። እርግጥ ይህ እርምጃ የተወናበደውን ደሀ ገበሬ ኢ.ዲ.ሕ. ለእሱ እንደማይቆምለት በገለጸ ስለሚያሳየው መልካም ነው ። እንደሚታወቀው በቅርብ ጊዜ የፀረ—አብዮት ኃይል በዚህ አውራጃ በሀመራ ከተማ ከፍተኛ ድል ተቀዳጅቷል ። ከተማውን በቁጥጥር ስር ለማድረግ ከመቻሉም በላይ አንዱ የሻለቃ አዛዥ ጥቂትም ቢሆኑ ከወታደሮቹ ጋር " እጅን መስጠቱ" ነው ። እርግጥ ይዞት የሄደው ጦር አንዱ ሻለቃ ሙሉ ያለመሆኑ ገለጽ ነው ። ግን ድርጊቱ ብቻ ትልቅ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ነው ።

## ሰሜን አውራጃ

የአብዮት ኃይል፣ በዚህ አውራጃ ጦር የለም ። በአካባቢው ወዝ—አደር የለም ። ግን እርግጥ ጥቂት ደሀ ገበሬዎች ይኖራሉ ። ይህ ኃይል በንቃትም በድርጅትም ሆነ በትጥቅ እዚህ ደረጃ ላይ ነው ያለው ለማለት አይቻልም ።

ፀረ—አብዮት ኃይል፣ ከዚህ በፊት በተጠቀሱት አውራጃዎች ለየት ባለ አኳኋን ይገኛል ። እዚህ ቀንደኛው ፀረ—አብዮት ድርጅት ኢ.ሕ.አ.ፓ. ነው ። ምን ያህል ብያች እንዳሉት የማይታወቀው ኢ.ሕ.አ.ሠ. በመባል የሚጠራ አካል የአብዮቱ ኃይል ከመዳከሙ የተነሳ በዚህ አውራጃ እንደልቡ ይዘዋወራል ይባላል ። እስከ አሁን በመንግሥት ጦር ጋር ያደረገው ግጥሚያ የለም ። ግን በኢ.ሕ.አ.ፓ. ሽብር ፈጣሪነትና ዱንፋታ አማካኝነት የሰሜን አውራጃ ከመንግሥት እጅ ፈልቅቆ ያወጣ የሚያስመስል ወሬ ተጋኖ ይወራል ። እርግጥ በትግራይ ክፍለ ሀገር ያለው ሁኔታ አመቺ ባይሆን ወደዚህ አውራጃ የመሸጋገሩና የመጠናከሩ እድል ከፍተኛ ነው ። በተጨማሪ በዚህ አውራጃ " የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት " የተባለውም ባይኖር አይቀርም የሚል ጥርጣሬ አለ ። ይህ በተለይ የተከዜን ወንዝ ተከትሉ ባለው አካባቢ ነው ።

## የደብረ ታቦር ጋይንትና ሊቦ አውራጃዎች

የአብዮቱ ኃይል፤ በዚህ አካባቢ የመንግሥት ጦር የለም ። /ደብረ ታቦር ለገዱ ተገንጣይ መቶ ቻይናዎችን ከሚጠብቁ በስተቀር/ በከተሞች ውስጥ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችና ከመንገድ ሥራ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች በስተቀር በዚህ አካባቢ ይህ ነው የሚባል የወዝ–አደር መደብ የለም ። በገጠር በርካታ ጭቃን ደሀ ገበሬዎች አሉ ። በእነዚህ አውራጃዎች የአብዮት ኃይል በገጠሩና በድርጅቱም በተጥቀም በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ይገኛል ።

የፀረ–አብዮት ኃይል፤ በእነዚህ አውራጃዎች ይህን ኃይል ያስተባብራል የሚባል ድርጅት በአሁኑ ጊዜ የለም ። በሽፍትነት ደረጃ የሚታዩ እነ አድማሱ እንዲሁም ከወሉ ክፍለ ሀገር በርገው የገቡ ሽፍቶች አሉ ። ግን ይህ ሁኔታ በዚህ መልኩ ብዙ ጊዜ ሳይ ቆይ ይችላል ። እየተንሰራራ ያለ የሚባለው አድማሱ እስከ አሁን ከኢ.ዲ.ሕ. ጋር ግንኙነት ባያደርግ ይቀራል ብሎ መገመት አይቻልም ። ሆኖም እዚህ አካባቢ የፀረ–አብዮት መሠረት ሊሆኑ የሚችሉትን መደቦች ማስተባበርና ደሀውን ገበሬ ማወናበድ በቀላሉ ላይሳካ ይችላል ። የዚህ ዋናው ምክንያት ባለፈው ዓመት ተነሳስተው የነበሩ አመጸኞችን ለመደምሰስ ወታደሩ የወሰዳቸው እርምጃዎች አሁንም ያልተረሱ መሆናቸውን ነው ። ግን የሚታወሱት በበጎ ሳይሆን በክፉነታቸው በመሆኑ ይህ ፍርሃት እስከ ዘላለም ሕዝቡን በኢ.ዲ.ሕ. ሰበካ ከመጠምዘዝ አያግዱትም ።

## የጎንደር ከተማ

የአብዮት ኃይል፤ በከተማ ውስጥ ምንም ጦር የለም ማለት ይቻላል ። የፖሊስና የአንዳንድ ክፍሎች ርዝራዦች ናቸው ያሉት ። በከተማው ውስጥ በርከት ያሉ ወዝ–አደሮች ይገኛሉ ። በአብዮቱ እምነት ያለው ንዑስ ከበርቴም ይገኛል ። የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ባደረገውና በሚያደርገው ቅስቀሳ በፀረ–አብዮት ሰበካ የተወናበዱ የአብዮት ወገኖች ወደ አብዮቱ እየተመለሱ ናቸው ።

የፀረ–አብዮት ኃይል፤ ይህን ኃይል በማስተባበር ጎልተው የሚታዩት ድርጅቶች ኢ.ሕ.አ.ፓ. እና ኢ.ዲ.ሕ. ናቸው ። ሁለቱም በቅስቀሳና በድርጊት ከፍተኛ ግና ይጫወታሉ ። ኢ.ሕ.አ.ፓ. እንደተለመደው በተማሪውና በአስተማሪው ውስጥ ኢ.ዲ.ሕ. ደግሞ በቢሮክራሲው በፖሊስ፤ በነጋዴው፤ በከበርቴው የከተማ ነዋሪ ውስጥ ከፍተኛ የተቀነባበረ ቅስቀሳ ያካሂዳሉ ። ስለ ኢ.ዲ.ሕ. የሚደረገው የወሬ ማሰራጨት ተግባር በጣም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ። በኢ.ሕ.አ.ፓ. እና በኢ.ዲ.ሕ. እንቅስቃሴ የመቀነባበር መልክ ይታይበታል ። በኅዳር ወር መጨረሻ አይከል በኢ.ዲ.ሕ. ተይዞ ለጎንደርም ያሰጋታል በሚባልበት ጊዜና የጎንደር ሕዝብ በመንግሥት አካባቢ ተሰልፎ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ መከላከል በሚያስፈልግበት ጊዜ፤ ሽብር ለማስነሳትና መንግሥትና ሕዝብን ለማጣላት ውጤቱም ምን ሊሆን እንደሚችል የሚታወቅ " የሰላማዊ" ሰልፍ በማስደረግ የብዙ ንጹሀን ደም እንዲፈስና ለኢ.ዲ.ሕ. ጎንደር መግባት አመቺ የሆነ የሕዝብ መንፈስ እንዲፈጠር በማድረግ ኅዳር 29 ቀን 1969 ዓ.ም. ከፍተኛ ወንጀል በኢ.ሕ.አ.ፓ. ተፈጽሟል ። የኢ.ዲ.ሕ. ፀረ–አብዮት ኃይል ለመደምሰስ እንዲቻል ሕዝቡን ለማንቃትና ለማደራጀት ለሰማሩ በተዘጋጁ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ካድሬዎች ላይ አደጋ በመጣል በሁለት ሳምንት ውስጥ አንዱ ጓድ ሲሞት አራት ጓዶች ቆስለዋል ። በውስጡ ከነበሩት ሰዎች በተገኘው መረጃ እነ አጣናው የሲ " ከደርግ ኢ.ሕ.አ.ፓ. ይሻላል" እያሉ ሕዝቡን ይሰብካሉ ። ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ በሰሜን አውራጃ ውስጥ የኢ.ሕ.አ.ሠ. ኃይል እየጨመረና እየተነሳሳ ነው ።



በውጭ የሚታተመው የኢ.ዲ.ሕ. ጋዜጣም ኢ.ሕ.አ.ፓ.ን " የማርክሲስት–ሌኒንስት ቡድን" እያለ ያሞካሽዋል ። እነዚህና ሌሎች ሁኔታዎች በሁለቱ ድርጅቶች መሀል በበጌምድር ውስጥ የድርጊት አንድነት መፈጠሩን ያመለክታሉ ። በዚህ ምክንያት የጎንደር ከተማ ከየትኛውም ቦታ ይበልጥ በበጌምድር ክፍለ ሀገር የፀረ–አብዮት ኃይል ጠንካራ የሆነበትና ሰንኩፉ ያለበት ሆኖ መታየት አለበት ።

## እንዴትና ለምን ይህ ሁኔታ ሊፈጠር ቻለ

አብዮቱ በአለበት ፀረ–አብዮት ስለሚኖር፤ በበጌምድርና በሰሜን ክፍለ ሀገር ያለውን ሁኔታ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ሁኔታ ነጥሎ ማየት ስህተት ይሆናል ። በኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ ንቅናቄ የሚካሄድ አብዮት በአለም የፀረ–አብዮት መናር የታሪክ ሂደት ሐቅ ነው ። ስለዚህ በበጌምድር ውስጥ ያለው ሁኔታ ምንም እንኳን በልዩ ልዩ ከታች በሚዘረዘሩ ምክንያቶች የበላይነትን አሁን ለጊዜው ፀረ–አብዮት ሀይል መያዙ መወገዱ ነበረበት ቢባልም ሁኔታው ጭራሽ መፈጠር አለነበረበትም /ጭራሽ/ ለማለት አይቻልም ። ይህ የታሪክን ሂደት ሕግጋት መካድ ይሆናልና ። ፀረ–አብዮት ኃይል አይሉ የበላይነትን የሚይዘው የአብዮቱ ኃይል ደከም በሚገኝበት ቦታ ነው ። ዋናው መተንተን ያለበትና ከዚያም መወገዱ የሚገባው ይህ የአብዮትን ኃይል ወዳከም ያደረሰው መሠረታዊ ምክንያትና አጣፋሪ ምክንያቶቹ ናቸው ። ከዚህ በታች የሚዘረዘሩት ምክንያቶችም በዚህ አንጻር እየታዩ ነው ።

የሰሜን ክፍላተ ሀገር የተለዩ ሆነው በመታየታቸው፤ ይህ በእነዚህ ክፍላተ ሀገር በየጊዜው ለተነሳው ፀረ–አብዮት ኃይል መሠረታዊ ምክንያት ነው ። የበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር እንደዚህ ይታይ እንደነበረ ገለጽ ነው ። የየካቲት 1966 ዓ.ም. እንቅስቃሴ ቢፈነዳ ክፍለ ሀገር ሳይለይ ከዳር እስከዳር መሆኑ የታወቀ ነው ። ምናልባት አንዳንዱ አካባቢ ከሌላው በተለየ ኃይል ቢፈነዳ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሕዝቡን የበለጠ ማንቀሳቀስ ስለቻለ እንጂ የፊውዳል ሥርዓት የዘረጋው ድር በአንድ ቦታ የመወፈር ሌላው ቦታ የመቅጠን ጉዳይ አይደለም ። ባለፈው የፊውዳል ቡርዧ የገዥ ነገሥት አገዛዝ ሥርዓት ጊዜ የሰሜኑን ክፍላተ ሀገር በሥርዓቱ ከሚበዘበዙ ይልቅ የሚጠቀሙ አስመስሎ በማቅረብ የሰሜኑንም ሕዝብ ሆነ የሌላውን አስተባስቦ ለማጋጨት ያሳደረገው ጥረት አለ ነበረም ። ይህ ጥረት ሙሉ በሙሉ ከሽፏል ለማለት አይቻልም ። በሳልከሸፈም የኢትዮጵያን ፊውዳል ሥነ ሥርዓት ጥናት በሚያደርጉም ሆነ በሌሎች ሰዎች የፊውዳሊዝም የከፋና ፊት ለፊት የሚታይ መልኩ በደቡብ ኢትዮጵያ ብቻ እንደሚገኝና በሰሜኑ ፊውዳሊዝም በአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ ውስጥ የዚህ ዓይነት ግፍ የለውም የሚል አስተሳሰብ አሳድሮባቸዋል ። ይህም ሊሆን የቻለው የፊውዳል ግንኙነትን በአንዱ በቀላሉ በሚታይ ገጽ፤ ይኸውም በመሬት ላይ ባለው የባለቤትነት አቋም ላይ ብቻ በማተኮር የፊውዳሊዝም አስከፊነት መለኪያ የጭሰኛና የባለመሬት ብዛት ሆኖ መወሰዱ ነው ። ስለ ፊውዳሊዝም ሥነ ሥርዓት በሚወሳበት ጊዜ የማምረቻ መሣሪያ ይዞታ ከምርቱ ተገንጥሎ አይታይም ። በሰሜን ክፍላተ ሀገር ምንም እንኳን መሬት የጋር ዋጋ ይዞት አለው ቢባልም የምርቱን ሁኔታ በምናይበት ጊዜ ግን የፊውዳሊዝም የአረጀ ሽፋን ሆኖ እናገኘዋለን ። ለምሳሌ በበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ሁሉም የፊውዳሊዝም ምልክት ነው ብሎ በሚያምነው መለኪያ በገናገር 15% ጭሰኛ አለ ይባላል ። ግን ምርትን ከመረተ በኋላ በሚኖረው አቋም ስንመለከት ከአለው አርሶ አደር ወደ 80% ምርትን ለሌላ የሚያከፍል ሆኖ እናገኘዋለን ። በመጀመሪያው ቁጥር መሠረት የዚህን ክፍለ ሀገር ሁኔታ ለምሳሌ 85% ጭሰኛ ከነበረበት ከኢሉባቦር ጋር ስናመዛዝን ፊውዳሊዝም ከበጌምድር ይልቅ በኢሉባቦር በበለጠ ተስፋፍቷል እንላለን፤ ግን በሁለተኛው ቁጥር/80%/

መሠረት ደግሞ በሁለቱ ከፍለ ሀገር ውሀል ያለው ልዩነት እስከዚህ የጎላ አይደለም ::

በሌላ በኩል ደግሞ የበጌምድር ሰሜን ሕዝብ ወግ አጥባቂ ነው ኃይለኛ ነው በጥንቃቄ መያዝ አለበት የሚል አስተሳሰብም አለ :: አብዮቱ ለምን እንደመጣ ሳይገባቸው ይቸላሉና ስለ ወደብ ትግል ስለብዝበዛና ጭቁና ብዙም ሳይነገረው ሕዝቡ " ሳይከፋፈል" በአንድነት አብዮቱን ሊቀበል ይችል ይመስል ብዙ ቅስቀሳ አልተደረገበትም :: በመንግሥትም በኩል ይህ የታመነበት ነበር የሚያሰኘው ወደ ከፍለ ሀገሩ የሚላኩት አስተዳዳሪያቸ አብዩ ታዊ ትግሉን አፋፍመው ሕዝቡን የሚያንቀሳቅሱ ሳይሆን ከፍለ ሀገሩን " በተረጋጋ" መልክ የሚይዙ በአብዮቱ ላይ ቢቆሙ እንኳ ለአብዮቱ ይቆማሉ የማይባሉ አይነቶቸ መኖራቸው ነው :: " ተወላጅ የገዛው አገርና በጎ የጋጠው መሬት" የሚሉት አስተሳሰብ በይፋ በሥራ የተተረጎመ ሆኖ ይታያል :: በማንኛውም በታ የገዒታ የአገሩ ሰው አስተዳዳሪ መሆን የለበትም ለማለት ሳይሆን ግን የገዒታ መሆን አለበት የሚለውም ትክክል አልነበረም :: በመጀመሪያ ደረጃ መታየት የነበረበት በአብዮቱ አንጻር ያለው አቋም ነበር :: በዓና አስተዳዳሪነት የሚሾሙትም በበኩላቸው በአውራጃ በወረዳና በምክትል ወረዳ አስተዳዳሪነት የሚያሾሟቸውና የሚሾሟቸው ሰዎቸ የአነሱው ብጤ ስለነበሩ በአጠቃላይ በከፍለ አገሩ ውስጥ አድሃሪ አስተዳዳሪያቸ ታጉረው ሕዝቡን አፍነውት ከርመዋል :: ከዚህም አልፎ ለኢትዮጵያ አርሶ አደር በሙሉ ከፍተኛ ብዝበዛ ያስቀረለትን የገጠርን መሬት ለሕዝብ ያደረገው አዋጅ አንኳን በበጌምድርና ሰሜን ከፍለ ሀገር በታ የሌለው ነው በማለት በአደባባይ በመስበክ ይፋ ፀረ–አብዮት ፕሮፓጋንዳ ያካሄዱ ነበር :: በዚህም ምክንያት አርሶ አደሩ ለጉልተኞቸና ለፈረሰኞቸ ሲገብር እንዲቀይ ከማድረጋቸውም በላይ በአዋጁ ባገኘው መብት ተጠቅሞ በመደብ አንጻር እንዳይደራጅ የገበሬ ማህበራትን በሚገባ እንዳይቋቋሙ አንቅፋቶቸ ሆነዋል :: የተሳሳተ መረጃን ለመንግሥት በማቅረብም ያልሆኑ ውሳኔያቸ እንዲተላለፉ ምክንያቶቸ ሆነዋል :: የአዱገት በሕብረት የዐጭቀትና የሥራ ዘመቻ በሕዝቡ ውስጥ አስፈላጊውን ቅስቀሳ በሚያደርጉበት ጊዜ ከአድሃሪያቸ ጋር በመጋጠር ስም ከማጥፋታቸውም በላይ ዘማቾቸ ከአንዳንድ ጣቢያ እንዲነሱ አድርገዋል :: ይህ ሁሉ በሚደረግበት ጊዜ መንግሥት ሕዝቡ እንዳይጋጭ ለባበሱ የመያዝ ፖሊሲ ስለነበረው አድሃሪ አስተዳዳሪያቸ እንደምክንያት በሚገባ ይጠቀሙበት ነበር ::

ግን በሌላ አንጻር እነዚህ አስተዳዳሪያቸ የኢ.ሕ.አ.ፓን ፀረ አብዮት ቅስቀሳ ለቀ በመልቀቃቸው የኢ.ዲ.ሕን /የራሳቸው ድርጅት/ ፀረ ሕዝብ ድርጊት ለማለባበስ በመቀራቸው ሁለቱም ድርጅቶቸ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፉ እንዲሄዱ አድርገዋል :: ለምሳሌ በጊዜው መመታት የነበረበትን ቢተወደድ አዳነ መኰንንን ከመንግሥት ጋር አስታርቃለሁ በሚል ሰበብ ለመጠናከሪያ ጊዜ ገዝቶለታል :: በአጠቃላይ ለመናገር ይህን ከፍለ ሀገር በተለይ ተመለከቶ " አረጋገተው የሚይዙ" ሰዎቸን መሾሙ የፀረ አብዮት እንቅስቃሴ ከቀን ወደ ቀን እያየለ እንዲሄድ ጊዜ የሚሰጡ ምክንያቶቸን በመፍጠር ያሁኑን ሁኔታ አስከትሏል ::

<u>የመሬት ይዞታ አዋጅ በምዕራብ ቆላ ከፍል በሥራ ላይ ያለመዋሉ፣</u> ይህ እንዲደረግ በየጊዜው ከአካባቢው ተጽእኖ እንደነበረ ግልጽ ነው :: በዚያ አካባቢ ከሀመራ እስከ መተማ ዱረስ በርከት ያሉ /እስከ 700/ የግል ባለሀብታዎቸ እርሻ ጀምረው በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመት ምርት እንደሚያስመርቱ ይታወቃል :: በሥራቸውም በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ወዝ አደሮቸ



ተቀጥረው ይሰሩ ነበር :: በእነዚህ እርሻዎቸ ውስጥ የነበረው /አሁን ያለው/ ብዝበዛና የወዝ አደሩ ስቃይ በጣም ከፍተኛ ነው :: አሰርቱ ያለመከፈለ ወዝ አደሩ ትንቢ ለመብቱ ሲከራከር መገደል አዲስ ነገር አልነበረም :: በመሠረቱ የአካባቢው ሕግና ሥርዓት የከበርቴው ጥቅምና ገቢ ያለመጉደል ነበር :: በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የነበረው ወዝ አደር የገጠርን መሬት ለሕዝብ ያደረገው አዋጅ በወጣ ጊዜ ከፍተኛ ደስታ ተሰማው :: መብቱን በሙሉ የሚጠበቅለት የመንግሥት ተቀጣሪ እሆናለሁ ወይም ይህ አንድ ሰው ሲበዘብዝ የነበረው የጉልበቱ ውጤት በሕብረት በመሥራት የጋራ ይሆናል የሚል ምኞት ነበር ያደረበት :: ግን መንግሥት በጊዜው በማመስለ የአወናባጆቸ አስተሳሰብ ተመርቶ በምዕራብ ቆላ ከፍል ያለው መሬት የመሬቱ አዋጅ እማይመለከተው እንደነበረ በግለሰቦቸ እጅ እንዲቀይ ወሰነ :: ምናልባትም ይህ ውሳኔ ቢደረግ አገደኛ ብዙ ሚሊዮን ብር የፈሰሰበት በለሀነ መንግሥት ቢይዘው ወይም ወዝ አደሩ ተረክቦ ቢሰራው በሚገባ አይካሄድም ብሎ በማሰብ :: ሁለተኛ፣ አካባቢው ጠረፍ ስለሆነና ከበርቴዎቹም አንዳንድ ጊዜ ያሳቸውን መሣሪያ በመጠቀም የውጭ ወረራንም ሆነ የኤርትራን ነፃ አውጪ ድርጅቶቸ ሰርጉ መግባት ከሕዝቡ ጋር ሆነው ይቋቋሙ ስለነበረ እንደዚያው ይቀጥላሉ ብሎ በማመን /እንደ ፕር 1967 የአምሀጅሩ ሁኔታ/ ሊሆን ይቸላል :: ግን በሁለቱም አንጻር ሲታይ የተሳሳተ ትንተና ነበር :: የመሬት ይዞታ አዋጅ ከመታወጁ በፊት ሕብረተሰብአዊነት /ሶሻሊዝም/ መታወጁ ይታወቃል :: እንግዲህ በዚህ ፍልስፍና መሠረት የዚህ አይነት አብዩት መሠረት ወዝ–አደሩ መሆኑ ግልጽ መሆን ነበረበት :: በኢትዮጵያ በሙሉ የሠራ አዋጅ በአንዳንድ አካባቢ ብቻ በመመሪያ ከሥራ ላይ የማይውለው ለጊዜው ቸገር ስለአለ እንጂ ለዘለቄታው ታምኖበት ያለመሆኑ ለማንም ግልጽ በለሚሆን እርሻሀ ለጊዜው በአንተ እጅ እንዲቀይ መንግሥት ፈቅዷል የሚባለው ከበርቴም ይህ እንደሚገባው መታወቅ ነበረበት :: ይህ ከሆነ ዘንዱ ከበርቴው እስከአለ ዱረስ ምርትን ቀንሶ ኢኮኖሚን ማቆር ቀዝና ከተመረተውም የሚገኘውን ገቢ እንዴት ለፀረ አብዮት ድርጊት እንደሚያውለው ያወጠነናል እንጂ ምርት ማደግና የአገር ጠረፍ መጠበቁ ደንታውም አይሆን :: ይህ ደግሞ በድርጊት ታይቷል ::

የመንግሥት ውሳኔ ምንን አስከተለ? አስቲ አንዱ በአንዱ እንመልከታቸው ::

– ቀን ወጣልን ብሎ በጉጉት ለውጡን የተቀበለው ወዝ አደር በደርግ ላይ ያለው እምነት ወደቀ :: ደርግ በዚያ አካባቢ ለወዝ አደሩ ጥቅም ሳይሆን ለከበርቴው ጥቅም የቆመ ነው ብሎ ተቀበለ :: ቀደም ሲል መንግሥት /ደርግ/ ከጉኔ ነው ብሎ እንደልቡ ለመብቱ መከራከር የጀመረው ወዝ አደር በከበርቴዎቸ " ዝም በል ደርግ እንደሆን ከእኛ ጋር ነው አታይም? " እየተባለ ተመልሶ ባሪያነቱ ገባ :: በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር የአብዮቱ ኃይል ከአብዮቱ መዱረክ ወረደ :: ያ አካባቢ የከበርቴዎቸ ባለሙሉ ስልጣንነት መሰለ ነገሰበት :: በመሠረቱ ምርትንም ለማሳደግ ሆነ የአገርን ጠረፍ በማንኛውም ኃይል ሳለማስደፈር ይህንን ወዝ አደር አደራጅቶና አስታጥቆ የምርቱ ባለቤት /ተቀጥሮ ለመንግሥት በመሥራትም ሆነ በሕብረት በመሥራት/ ከማድረግ የተሻለ አማራጭ አልነበረለትም :: አድሃሪያቸ የሚፈሩትም የዚህ አይነት ሁኔታ መፈጠሩን ስለነበረ ነገሩ ሌላ መልክ ሲይዝላቸው ፈንጥዘዋል ::

— ፀረ አብዮት ኃይሎች የፈነጠዙበት ሌላም ምክንያት ነበራቸው ። በመጀመሪያ ደረጃ ለፀረ አብዮት ድርጊታቸው ሊያውሉት የሚችሉት ሀብት ማፍራት መቻላቸው ሲሆን በተጨማሪም ለዚሁ ድርጊታቸው ሴራ መጠንሰሻ ከመንግሥት አይን እርቀ የሚገኝና እንደልብ ከኢትዮጵያ መውጣትና ወደ ኢትዮጵያ መግባት የሚቻልበት ቦታ በቁጥጥራቸው ሥር መሆኑ ነበር ። በቢሮክራሲው ውስጥ ተሰግስጐ የነበረው አብዛኛው በቆላው እርሻ የነበረው ስለሆነ የጥቅም መገናኘት የአቋምንም በበለጠ ግቀነባበር ፈጠረ ። በአካባቢው የነበሩ የመሬት ከበርቴዎች ቀን ተቀን ፀረ—አብዮት ድርጊቶቻቸውን እያፋፋሙ ሄዱ ። አንዳንዶቹ በቀጥታ ትራክተሮቻቸውንና ሰብላቸውን ወደ ሱዳን እየያዙ መግባት ጀመሩ ሌሎችም እዚያው ሆነው ግልጽ በሆነ መንገድ የኢ.ዲ.ሕ. ከመሀል አገር ጋር አገናኝ ወኪል ሆኑ ። ወዝ አደሩ እየተተው የሄዱትን እርሻዎች በሕብረት ለማካሄድ በሞከረበት ጊዜ አድሃሪው በመሣሪያ ሲያጠቃው ቢሮክራሲው ደግሞ በማስፈራራት ያስበረግገዋል ። በመጨረሻም በተፈጠረው ሁኔታ አብዛኛው ከበርቴ ለይቶለት ወደ ኢ.ዲ.ሕ. ሲገባ በምርት መቀዛቀዝ ደመወዙን ባለማግኘት በዝኑ የሆነው ወዝ አደር እየተወናበደና እየተገደደ የኢ.ዲ.ሕ. ምልምል ሆነ ። በዚህም አኳኋን የኢ.ዲ.ሕ. ኃይል አድጉ ወደ ደጋው እንደልቡ መሄድ ቻለ፤ ከዚያ ሲጠቃም መርጫ አቅጣጫውን ወደ ቆላው ነው ።

<u>የኤርትራ ዘመቻ፤</u> " ሕዝባዊ ሠራዊት " ወደ ኤርትራ ለማዝመት ታስቦ የነበረ ጊዜ አድሃሪው በጎንደር ውስጥ ሀሳቡን በሚገባ አራግቦት ነበር ። የኢ.ዲ.ሕ. አባላትና የማያጠራጥረው በቢሮክራሲ ውስጥ የተሰገሰገው አድሃሪ " ማዝመት " ሥራዬ ብሎ ይዞ ሲፎክር ድርጅቱ ከጐን ፀረ ዘመቻ የሆነ ቅስቀሳ ያደርግ ነበር ። በዚህ ቅስቀሳ ባቢያ ኢ.ሕ.አ.ፓም አጠቃላይ ፀረ አብዮት ፕሮፓጋንዳውን ለመንፋት እድል አጋጥሞታል ። አድሃሪ ቢሮክራሲው በወቅቱ የኤርትራን ዘመቻ እንደዚያ ሲያናፍስ የነበረው በአገር ወዳድነት ሳይሆን ይህን እስከ አደረገ ድረስ ድርጅቱ በደርግ ላይ ለሚያደርገው ቅስቀሳ ድጋ ምክንያት እንደሚያገኝ ስለሚያውቅ ነው ። በዚህም ቅስቀሳ ምክንያት ኢ.ዲ.ሕ. በሕዝብ ውስጥ እንደሚገባና ለመተዋወቅ እድል እንደሚያገኙ ያውቃል ። ግን ይህ ሁሉ ሆኖ አሁን ያለውን ሁኔታ ሊያባብሱ የቻሉት ከኤርትራ ዘመቻ ጋር ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው ።

— ለኤርትራ ዘመቻ ተብሎ ትጥቅ በታደለበት ጊዜ ይህንን ትጥቅ ያገኘው አብዛኛው አሁን ኢ.ዲ.ሕ. መሠረት ያደረገው ጉልተኛ ፈረሰኛና ነጭ ለባሽ የሚባለው የሀብታም ገበሬ መደብ ነበር ። ስለዚህ ይህ " የአገርን ነፃነትና አንድነት ለመጠበቅ " የታደለ መሣሪያ በአሁኑ ጊዜ የዚህ ዓላማ ተጻራሪ ለሆነ አቋም እንዲያገለግል ሆኗል ።

— ለዚሁ ዘመቻ ተመልምሎ የነበረ የከተማ ቡዘኛም ዘመቻው በተሰረዘ ጊዜ ወደ ከተማ ሲመለስ የታደለውን መሣሪያ በቀላል ዋጋ ያው ገንዘብ ለአለው ለአድሃሪው ክፍል ሸጠአል ። ይህም በተለይ የከተማውን አድሃሪ የትጥቅ አቋም ለማጠናከርና የልብ ልብ እንዲሰጠው አንዱ ምክንያት ሆኗል ።

— ለኤርትራ ዘመቻ ትፈለጋላችሁ ተብለው ከቆላው ክፍል ተመልምለው የነበሩ ወዝ አደሮች /ከሥራ የተፈናቀሉ/ ዘመቻው ከተሰረዘ በኋላ በወታደርነት ትቀጠራላችሁ ተብለው ቆይተው ነበር ። ነገር ግን በመጨረሻ ወታደርነት መቀጠሩም በቀረበት ጊዜ ተመልሰው ወደ ቆላው ሥራ ፍለጋ ሄደው ከእነሱ ውስጥ ብዙዎቹ በኋላ በኢ.ዲ.ሕ. መልመላቸው ይወራል ።



<u>በወቅቱ የፀረ አብዮትን ኃይል አቋም አለመገንዘብ፤</u> በተለይ ይህ የሚመለከተው ኢ.ዲ.ሕን ነው ። ይህ ድርጅት ተቋቋሚል ግለት በተከማ ጊዜ የንቁና ምንም ሊሰራ እንደማይችል ኃይል ተገምቷል ። ከዚያም ሥራ መጀመሩን ወረቀት በመበተን በበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ባበሰረ ጊዜ ቢሮክራሲው በወቅቱ ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ጥረት አላደረገም ። የአብዮቱ ኃይሎችም የኢ.ዲ.ሕ. ፀረ አብዮተኛነት ኃይልን <u>የወረቀት ነብር በሚለው ቀላል አነጋገር አለፈውት</u> ነበር ። ነገር ግን ወረቀት ከመበተን አልፎ የጦር መሣሪያ ይዞ ትግሉን በቀጠለበት ጊዜም ይህ አስተሳሰብ አልጠፋም ነበር ። ቢሮክራሲው የዚህን አይነት መረጃዎች በቁንጽል መልክ ለመንግሥት ያቀርብ ነበር ። መንግሥትም ኢ.ዲ.ሕ. የሚያደርገውን የመሣሪያ ትግል በየቦታው እንደሚደረጉት የግለሰብ ወይም የቡድን ሽፍታ እንቅስቃሴ አድርጉ ቆጥሮት የነበረ ይመስላል ።

ግን አሁን በአጠቃላይ ሲታይ የኢ.ዲ.ሕ. ጦር የተቀነባበረ አመራር ያለው ሆኖ ይገኛል ። በ1967 እና በ1968 በየክፍላተ ሀገሩ ይደረጉ ከነበሩት ግብታዊ የተነጠለ የአንዳንድ አምባገነን ተናጊዎች እንቅስቃሴ የተለየ ነው ። ድርጅታዊ መዋቅሩም በመላው ኢትዮጵያ የተዘረጋ በመሆኑ የጦር ስልቱና ፕሮፓጋንዳው በጣም የተያያዘ ነው ። እርግጥ ጦሩ የዘመቀ ተናጊ ጠባይ የለውም ። ተከታዬቹን /ደሌውን ጭምር/ በማበዛትና አንዳንድ ጊዜም በከባድ መሣሪያ በመጠቀም ገበሬውን በኃይላቸውም ጭምር ሲያስበረግጉት የጦሩንም ሞራል በመጠኑም ቢሆን ለማዳከም ጠቅሟቸዋል ። ገና በመስከረም 1969 ዓ.ም. በጠረፍ /በሁመራና በመተማ/ አካባቢ የኢ.ዲ.ሕ. ጦር መታየት በጀመረበት ጊዜ እንኳን የተቀነባበረ እርምጃ በወሰዱ ኖሮ አሁን ያለው ሁኔታ ምናልባት ሳይፈጠር ይቸል ነበር ለማለት ያስደፍራል ። ከተሞቹን /አንዳንዶቹን/ ለማስጠበቅ፤ በተለይ በጠረፍ ላይ ያሉትን፤ አንዳንድ አገበተኛ እርምጃዎች በወሰደም ከችግሩ ጋር ተመጣጣኝ ኃይልና ችሎታ በወቅቱ አልተመደበም ። መሀል በጌምድር እነ ኢ.ዲ.ሕን እንዲያጋና እንዲደምም እርምጃ አልተወሰደም ።

<u>በአንዳንድ አከባቢ የአስተዳደርና የፖሊስ ሰዎች አብዮቱን በጠነከረ አቋም አለመደገፍ፤</u>

ይህ በተለይ ጉልቶ የሚታየው ውጥረት በተፈጠረባቸውና የኢ.ዲ.ሕ. ጦር ከዛሬ ነገ ይገባል በሚባልባቸው ቦታዎች ነው ። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ የመንግሥት ወኪልና የመንግሥት ሥልጣን ምልክት የሆነ አቋም ማድረግ ያለበት ሕዝቡን አስተባብሮ እስከተቻለ ድረስ የጠላትን ጦር መቋቋም ሲሆን፤ ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚደረገው መ/ቤትን ዘግቶ መፈርጠጥ ነው ። በብዙ ቦታ ሕዝቡ " እንዴት ትሄዱብናላችሁ አብረን ተባብረን ጠላትን እንመክት " እያላቸው አሻፈረኝ በማለት በሌሊት ሕዝብ ሳያያቸው ይጠፋሉ ። ሕዝቡም መንግሥት ያለጠበቀውንና ጥሎ የሄደውን ከተማ እና ምን አለፋን በማለት ከጥቂት ቆይታ በኋላ የሚገባውን የኢ.ዲ.ሕ. ኃይል ያሳንዳች ተከክ ይቀበለዋል ። በአንዳንድ ቦታ ደግሞ የአስተዳደሩ ሰው እጁን አጣምሮ ይቀመጥና ከተማዋ ስትያዝ ለኢ.ዲ.ሕ. እጁን ይሰጣል ። በልዩ ልዩ መንገድ አስተዳደር ላይና በፖሊስ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሰዎች የኢ.ዲ.ሕ. የውስጥ አርበኛ ሆነው የሚሰሩ መሆናቸውን በማያጠራጥር ሁኔታ እያስመሰከሩ ናቸው ።

በፖሊሲና በአስተዳደር በኩል በፀረ-አብዮት ገለሰቦችና ድርጅቶች ላይ የሚደረግ ክትትል በአፍና በወሬ ብቻ ነው ። ከልዩ ልዩ የተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች እንደሚገባው መረዳት እንደሚቻለው በአፍ ከመንግሥት ጋር በተገባር ግን ፍጹም የተለያዩ ናቸው ። " ተቦት ነው የተገኙ ፀረ-አብዮት ወረቀቶች ግን እንደበቱና ቸው ክትትል አድርገን እናስታውቃለን" የሚለው አባባል በሥራ ተተርጉሞ አይታይም ። ግን ወረቀት መበተኑ ይቀጥላል ። በርከት ያሉ የወረዳና የምክትል ወረዳ አስተዳዳሪዎቹ፤ የፖሊስ አዛዦች በአሁኑ ጊዜ ለይቶላቸው ወደ ኢ.ዲ.ሕ. ገብተዋል ። ግን ከትንሽ ጊዜ በፊት እነሱንም ታማኝ ብሎ በሹመት ላይ መንግሥት አቁይቷቸው ነበር ። በቅርቡ በሀመሬ የነበረው ሻለቃ አዛዥ የፈጸመውም ድርጊት ትምህርትና ሌላው ምስክር ነው ።

## ሁኔታው ወዴት ሊያመራ ይችላል ?

<u>በአገር ውስጥ ከአለው አጠቃላይ ሁኔታ ጋር ሲታይ፤</u> በጎንደርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ውስጥ የሚካሄደው ሁኔታ በሌሎችም ሥፍራዎች በተለያየ መልኩ ሊፈጠር ይችላል ። ኢ.ዲ.ሕ. በመሰፍንትና መሳፍንቱ ባላባቶቹ ርዝራዦች ወስጥ፤ ፀረ ሶሺያሊስት በሆነ ከበርቱና ከፍተኛ ገዐስ ከበርቴ ውስጥ ክፍለ ሀገር ሳይለይ የፖለቲካ ተቀባይነትን በአሁኑ ጊዜ አግኝቷል ብሎ መገመት ይቻላል ። በኢ.ሕ.አ.ፓ. ወሮበሎችና ውንፋታ ከአብዮት ኃይሎች ዝግፍና የነበረው የኢ.ዲ.ሕ. አባሎች ፀረ አብዮት አቋም አሁን በየቦታው ግልጽ እየሆነ ነው ። በበርክራሲው ውስጥ በተለይ ጎልቶ ይታያል ። ቀደም ሲል ለደርግ የሚሸቁጠቁጡ ቢሮክራሲ አሁን የልብ ልብ በቅቶታል ። ለአብዮቱ ማነቆ ከሆነበትም ደረጃ ወጥቶ አሁን ግልጽ በሆነ አኳኋን የአብዮት ቀለበሳ ሥራውን ያካሄዳል ። ይህ ሁኔታ በአሰቦት አካባቢ ኢ.ዲ.ሕ. በበጎንደር ውስጥ የትጥቅ ትግሉን ማስፋፋትና ማጠናከር በጎንደርን ነፃሉ ለብቻ ለመያዝ ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ይሆናል ። በዚህ ክፍለ ሀገር ውስጥ የተጀመረው የትጥቅ ትግል በጎጃም ወለጋና ሲዳሞ ክፍላተ ሀገርም ሊጀመር ይቻላል ። ወይም አሁን በእነዚህ ክፍላተ ሀገር በግል ሽፍትነት የሚገኙትን ሰዎች በማስተባበር ኢ.ዲ.ሕ. የራሱ ጦር ሊያደርጋቸው ይችላል ። በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ቀደም ሲል ከደረሱት ሁኔታዎች ይህ በሥራ ላይ ውሉ ይሆናል ብሎ መጠርጠር ይቻላል ። የሞያሌ ወረዳ፤ በአሬርና በከብረ መንግሥት አካባቢ ያለው የተጠናከረ ሽፍታ የኢ.ዲ.ሕ.ን ጠረን ይሸታል ። በወለጋ ክፍለ ሀገር በአሶሳ አውራጃ አንዳንዱ አጠራጣሪ እንቅስቃሴዎች ይደረጋሉ ። በአጠቃላይ ከሱዳንና ከኬንያ በሚዋሰኑ ክፍላተ ሀገር ውስጥ የኢ.ዲ.ሕ. ሰርጎ መግባት እድሉ ከፍ ያለ ነው ። በወሉ ክፍለ ሀገርም ቀደም ሲል ተነስተው የነበሩ ሽፍቶች እንደገና በኢ.ዲ.ሕ. አጋርነትና አስተባባሪነት እንዲያገበሩፈ ሊደረጉ ይቻላሉ ። እንዲያውም አንዳንዱ ሽፍቶች ይህን ግንኙነት ሳያበጁ አልቀሩም የሚል ጥርጣሬ አለ ።

እንግዲህ ይህን ሁሉ ለማድረግ ኢ.ዲ.ሕ. ኃይል ማሰየትና ተባባሪ መሳብ ደኖር በታል ። ያለበለዚያ በየቦታው ሽፍታ ቢነሳ ጥንቅላቱን መመታቱ የተለመደ በለሆነ ያለ አስተሳሰቡ ኃይል እንደገና እንበራርቶ እንደገና ከመመታት አብዛኛው ሽፍታ በዚያው ሟሞቶ መቅረቱን ለምርጥ ይቻላል ። አሁን በጎንደር ላይ ኢ.ዲ.ሕ. የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በዚህ መልክ ማየት ይቻላል ። ጉንደርን ከዛሬ ነገ ይይዛል ተብሎ የሚወራለት ኃይል አስተሳሰቡ በለሚመስል ጥሬውን ሰዎቶ የሚተባበረው ሊበዛ ይቻላል ። የኢ.ዲ.ሕ. የትጥቅ



<u>ትግል በአሁኑ ደረጃው በእውነት የስልጣን መያዢያ መሣሪያ ከመሆን ይልቅ የግርፓጋንዳ መሣሪያ ነው ማለት ይቻላል ።</u>

ሌላው ኢ.ዲ.ሕ. ሊያቀነባብር የሚችለው ድርጊት በአዲስ አበባ ውስጥ የመንግሥት ግለበጣ ነው ። በሆነም ይህንን ብቻውን ያደርገዋል ብሎ መገመት አይቻልም ። ኢ.ዲ.ሕና ኢ.ሕ.አ.ፓ. እንዲሁም የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር ሳይመስርቱ አልቀሩም የሚባለው " ፀረ ፋሽስት ግንባር " ለዚህ መሣሪያ ሊሆን ይችላል ። የኢ.ዲ.ሕና የኤርትራ ነፃ አወጪ ግንባር ወዳጅነት በአሁኑ ጊዜ በአደባባይ ዎሰጪር ነው ። ከተባለው ግንባር ኢ.ዲ.ሕ ልዩ ልዩ የቴክኒክ እርዳታ ያገኛል ። የኢ.ሕ.አ.ፓና የኢ.ዲ.ሕም መቀራረብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየታየ ነው ። " ኢ.ዲ.ዩ. አድቮኬት" በሚባለው የውጭ ጋዜጣው ውስጥ ኢ.ዲ.ሕ. ስለ ኢ.ሕ.አ.ፓ. ማርከሲስት ድርጅትነት ይሰብካል፤ ስለደረሰበት "ጭፍጨፋ" ጠዘኑን ይገልጻል፤ እንዲት የደርግ " ፋሺስትነትን" በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ " እንደሚያጋለጥ" ያሳያል ። በአገር ውስጥ ደግሞ የኢ.ዲ.ሕ. " ጦር መሪዎች" ለኢትዮጵያ ከደርግ ይልቅ ኢ.ሕ.አ.ፓ. እንደሚሻል ለሕዝብ ይሰብካሉ ። ኢ.ሕ.አ.ፓ. የኤርትራን በፊ ሕዝብ ጥቅም ለጥቂት መሣሪያ ከሸጠ ጊዜ ጀምሮ በአሰና በኤርትራ ነፃ አወጪ ግንባር መሀል ከፍተኛ " ወዳጅነት" ተመስርቷል ። እነዚህን ሦስቱን የሚያስተሳስራቸው ሁሉም የሚዋጉት " ፋሺስት" ደርግን ስለሆነ " ፀረ ፋሺስት ግንባር" አሰፈጠሩም ብሉ.ማመን ያስቸግራል ። <u>እንግዲህ በአዲስ አበባ ውስጥ ሊሞከር የሚችለውም የመንግሥት ግለበጣ በእዚህ ግንባር አማካኝነት ይሆናል ብሎ መገመት ይቻላል ።</u> እንደሚገመተውም የኢ.ሕ.አ.ፓ. ሚና የተከነበት ሽብር መፍጠር፤ የኤርትራ ነፃ አወጪ ግንባር ሰው መግደል፤ የኢ.ዲ.ሕ. ደግሞ አዱሃሪ መለዩ ለባሾችን መሣሪያ በማድረግ ስልጣን መቆጣትና የሚትካውን " የሲቪል መንግሥት" ማቅረብ ሊሆን ይቻላል ።

<u>በጎረቤት አገሮች የተቀነባበረ ፀረ ኢትዮጵያ ሴራ ጋር ሲታይ፤</u> የበጎንደርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ሁኔታ በጣም አሳሳቢ ነው ። ከበዙ አቅጣጫ ሲታይ ኢምፔሪያሊስትና አዱሃሪ የአረብ መንግሥታት የተቀነባበረ ፀረ ኢትዮጵያ በትራተጂ ያወጡ ይመስላል ። የበጎንደርም ሁኔታ በዚሁ ስትራተጂ ውስጥ ያለ ታክቲካዊ ሁኔታ ነው ለማለት ይቻላል ። ይህንን ለመረዳት በዝርዝር ጉዳዩን መመርመር ያስፈልጋል ። ምንም እንኳን የመረጃ አለመኖር እንዳንጉን ሁኔታ "የፈጠራ" ቢያስመስለውም ጉዳዩን ደፍረን እንዱንፍርበው ትንተናው ያስገድደናል ።

በመጀመሪያ ለምን ሱዳን በዚህ ደረጃ ኢ.ዲ.ሕን ትረዳለች? ለምን በኢትዮጵያ ጠረፍ የጦር ዝግጅቷን አፋፋመች? የሚሉትን ጥያቄዎች እንመልከት ። በመጀመሪያ የተራማጅነት መልክ ይዞ የነበረው ኒሜሪ ቀስ በቀስ በኢምፔሪያሊስትና በአዱሃሪ አረብ መንግሥታት /በተለይ ሳውዲ አረቢያ/ ተጽእኖ ስር ከወደቀ ወዲህ በአገሩ ውስጥ የሰፊውን ሕዝብ ዱጋፍ አያገኝ ነው ። ተራማጆች የኒሜሪን መንግሥት ለማስወገድ አንዳንዱ ጥረት ማድረጋቸው የታወቀ ነው ። በአፈ በለሶሺያሊዝም እያወራ በድርጊት ግን ፀረ ሶሺያሊስት መሆኑ ቀን ተቀን ኒሜሪ በሚወስዳቸው እርምጃዎች እየተጋለጠ ነው ። ስለዚህ በጎረቤት አገር /ያውም ከሱዳን በኋላ/ ስለ ሶሺያሊዝም መነገር ብቻ ሳይሆን ወደዚሁ የሚያመራ እርምጃ ሲወሰዱ ኒሜሪን እንደሚያሳስበው ግልጽ ነው ። የኢትዮጵያ አብዮት በሁለት ዓመት እድሜው ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም የወሰዳቸው እርምጃዎች እንኳንስ በጎረቤት አገሮችና ከባህር ማዶም ዝናን አትርፏል ። አንዳንዱ እንደዚሁ እንደ ኒሜሪ የኢትዮጵያ አብዮት እርምጃዎች ያሳስባቸው

መሰሎቹ የአፍሪካ መሪያቸ በኢስገራሬ አቀማመጣቸው ሌላ እርምጃ ሊወስዱ ባይችሉም " ከውጭ የተቀዳ ሪፎርሙን" በማለት የኢትዮጵያን ሪፎርሙን እንደ አቃ ወደ አገር ውስጥ የገባ ለማስመሰል ይጥራሉ ። ግን ኒሜሪ ከዚህ የተሻለ እድል አለው ። ወደፊት ለሱዳን ሰፊ ሕዝብና ተራማጆች ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆን የሚችል አብዮት በጐረቤት አገሩ ሲያድግ ይህን አብዮት ለመቃወት ከወሬ ብቻ ድርጊትንም ሊያከለበት ይቻላል ። በአሁኑ ጊዜ ይህ ነው እየተደረገ ያለው ። ኢ.ዲ.ሕ. የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀለበስ የተነሳ ድርጅት በመሆኑ በሌላ ባይሆን በዚህ ጉዳይ ላይ ከኒሜሪ ጋር የጋራ ግንባር መፍጠሩ ተከታዩ ውጤት ነው ።

የኢትዮጵያን አብዮት ለማጥፋት ባይሳካም ለማዳከም ኒሜሪ ሌላ አበይ ምክንያት ያለው ይመስላል ። ይኸውም ከሳውዲ አረቢያና ከሱማሊያ ጋር ያለው ግንኙነት ነው ። በአሁኑ ወቀት የሱዳን የኢኮኖሚ እድገት ተስፋ በከፍተኛ ደረጃ በሳውዲ አረቢያ ላይ ነው ያለው ። ሌሎች አድሃሪ አረብ መንግሥታትም የዘይት ሀያቸ ብራቸውን በሱዳን ላይ ለማፍሰ ፈቃደኛነትን እያሳዩ ናቸው ። የሳውዲ አረቢያ መንግሥትና እንዲሁም ሌሎች አድሃሪ አረብ መንግሥታት በቀይ ባህር ባለቤትነት አማካኝነው በኤርትራ ጥያቄ ላይ ያላቸው አቋም የታወቀ ነው ። " አረባዊት " ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ የእነሱ ቡችላ እንድትሆን ይፈልጋሉ ። አሁን የኢትዮጵያ አብዮት በየቦታው በተወጠረበት ጊዜና ወታደሩ በየቦታው በሚበተንበት ጊዜ ለዚሁ ዓላማቸው ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል በለው ያምናሉ ። ስለዚህ ሱዳን የኢኮኖሚ እር ዳታን እንድታገኝ ከፈለገች በዚህ መተባበር አለባት በለው ያምናሉ ። ይህ የኒትሮ ዶላር ኢምፔሪያሊዝም ነው ። ግን ሱዳን ገለጸ ጠርነት በማንሳት ኢትዮጵያን ለተፃጋ ስለማትችል ይህን ተብበጅን ለማሳየት አሁንም አመቺ ሆና የተገኘው የኢ.ዲ.ሕ. መፈጠርና መነሳት ነው ።

ሱዳን የሱማሊያን " ጥቃም " ለማስጠበቅ በተለ የምትወስደውም እርምጃ ተመሳሳይ ነው ። በተለይ ሱማሊያ ፍላጎቷ የኤርትራ መገንጠል ብቻ ባይሆን የጅቡቲ ጥያቄና ከጥንት ጀምሮ የምትመኘው ኦጋዴን እሷ በፈለገችው መንገዱ እንዲፈታ ትፈልጋለች ። ይህም ሆኖ ሱማሊያ የኢትዮጵያ ጦር ኃይል በእሷ ላይ ብቻ ሳይሆን የሚያተኩረውና የሚጠብቀው በየቦታው መከፋፈሉንና መገነጣጠሉን አጥብቃ ትገፋበታለች ። ለዚህም ዓላማ ሱዳን አሁን በያዘችው መስክ ተብብጅን ታሳያለች ።

በመሠረቱ በአሁኑ ጊዜ ሱዳን ለኢ.ዲ.ሕ. ከየአቅጣጫው ለሚሰጠው እርዳታ ዱሳይይም ጥምር ሆና እንደምታገለግል መገንዘብ ይቻላል ። ፀረ ሶሺያሊስት ኃይሎች በሙሉ የኢትዮ ጵያን አብዮት ለማጥፋት ከኢ.ዲ.ሕ.፣ ኢ.ሕ.አ.ፓ. የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር የተሻለ ቀንጃት አያገኙም ። ስለዚህ ይህን ቀንጃት ለማሳደግ ይረባረባሉ ። ለማያውቃቸው ኢ.ሕ. አ.ፓና የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባር በማደነፋት ሶሺያሊዝም ቀመስ ተራማጆች ስለሚመስሉ የፀረ ሶሺያሊስት አምብርት ኢ.ዲ.ሕ. እንዲሆን ማጠናከሩ የጊዜው የፀረ አብዮቶች ታክ ቲክ ይመስላል ። ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ አብዮት ወዳጅና ጠላት መለየት በሶሺያሊስትና በፀረ ሶሺያሊስት አቋም ላይ የተመሠረተ ያደርገዋል ። ይህ ለኢትዮጵያ አብዮት በጣም አመቺን ሁኔታ ይፈጥራል ። ለተወሰነ ጊዜ ኢ.ሕ.አ.ፓና የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር አወናብደውት የነበረው የሶሺያሊስት ካምፕ ያለውን ሁኔታ በገለጸ እንዲረዳ እድል ይሰጣል ። የዚህም ውጤት የሕዝባዊ ዴሞክራቲክ የመን ሪፐብሊክና የሶቭየት ሕብረት የወሰዷቸው እርምጃዎች አይነት ይሆናል ። ኢትዮጵያ ይህን ቀራኔ በትክክል መፍታት እስከ ቀጠለች ድረስ ይህ የሚና መለየት ጉዳይ ይቀጥላል ።



ምን መደረግ አለበት

1. በበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ውስጥ፣

ከዚህ በታች የሚዘረዘሩት እርምጃዎች የሚወሰዱት እንደአቀራረባቸው ቅደም ተከተል ሳይሆን ሁሉም በተመሳሳይ ጊዜ ሊወሰዱ ይቻላሉ ። በብዙ ሁኔታ ይህ መደረግ ይኖርበታል ። ምንም እንኳን አሁን አድሃሪያን በተጥቀ ትግል ቢገጥሙንና የእናም መሰክ በመጀመሪያ ደረጃ በዚያው መስክ መሆን ቢኖርበትም፣ እሱን ለማሟላት የቅስቀሳው ሥራም አብሮ መያዝ አለበት ። ሕዝብ ተቀስቅሶ ለመናገት ወይም እየተናጋ ሲቀሰቀስ መሠረታዊ የሆነውን ድር ጅታዊ አቋሙን ማጠናከር ስለሚገባው በዚህም በኩል ከፍተኛ ሥራ ማከናወን አለበት ። ስለ ዚህ ሁሉንም ማየት የሚቻለው በቅደም ተከተል መሰካቸው ሳይሆን እንደቀለበት ባለው ፍር ማቸው ነው ።

የፖለቲካ ቅስቀሳና ድርጅት፣ ቅስቀሳን በሚመለከት ረገድ ክፍለ ሀገሩን በሁለት መከፈል ያስፈልጋል ። እነሱም ውጥረት ያለባቸው ቦታዎች፣ /ዊልጊያ፣ ጉንደር ዙሪያ፣ ወገራና ሰሜን አውራጃዎች/ ለጊዜው ጸጥታው የተረጋጋባቸው ቦታዎች/ ደብረ ታቦር፣ ጋይ ንትና ሊቦ/ ናቸው ። የቅስቀሳው ሥራ የተጥቀ ውጊያውን በሚያገዝ አይነት ማካሄዱ ስለ አለበት ውጥረት በአለባቸው ቦታዎች ከተናገው ጦር ጋር የሚሆኑ የታጠቁ በርካታ ካድሬዎች መመደብ አለባቸው ። የእነዚህ ካድሬዎች ተግባር፣

ሀ/ በመደባዊ ጦር ጐን የሚሰለፍ ሕዝባዊ ጦር የሚቋቋምበትን ቅስቀሳ ማድረግ፣
ለ/ በመደባዊ ጦር ውስጥ የፖለቲካ ትምህርት መስጠት፣
ሐ/ ጦር በሚያልፍባቸው ቦታዎች ስለ አብዮቱ ገለጻ ማድረግ፣
መ/ ጦር አለፍ የሚሄዱባቸው ቦታዎች ተመለሰው በአድሃሪያች እንዳይያዙ በገበሬዎች ማህበራት አማካኝነት ሕዝባዊ ጦር ማቋቋምና ማስታጠቅ፣
ሠ/ በከተሞች ውስጥ የአብዮት ጥበቃ ከሚቴ አቋቁሞ በሱ ስር የሕዝብ ደህንነት ጠባቂዎችን ማስታጠቅ፣ ካድሬዎች ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ለተመሳሳይ ዓላማ የቆሙ የደርግ አባላት አብረዋቸው በስለፉ ሥራው የበለጠ ሊሳካ ይችላል ። ካድሬዎች ገለ ጻና ቅስቀሳ በሚያደርጉበት ጊዜ በተለይ ኢ.ዲ.ሕ.ና ሌሎች አድሃሪያች በአካባቢው የሚ ያደርጉትን ፕሮፓጋንዳ ማክሸፍን ቀዳሚያ መስጠት አለባቸው ። ይኸውም የፕሮፓጋንዳ ይዘት የሚያገጸባርቀው የመደብን አቋም በመሆኑ የኢ.ዲ.ሕ. ፕሮፓጋንዳ ሙሉ በሙሉ እየተደመሰሰ በመሄዱ ላይ ያለውን የፊውዳሉን ሥርዓትና ሕልውና ያንጸባርቃል ። ይዘቱም " መሬትህንና በትህን ተነጠቅህ" "ኃይማኖትህ ረከሰ" የረደም ጊዜ ታሪክህ ጉደፈ" ወ.ዘ.ተ. በሚሉ አድሃሪ መፈክሮች ዙሪያ ነው ። ሰፊው የበጌምድርና ሰሜን ሕዝብ የአካባቢውን ቀራኔ መሠረት በማድረግ ጠለቅ ያለ ቅስቀሳ ባላለተደረገለት፣ በውዝግቡ በተደጋጋሚ በሚደርስበት ጉዳት ብሶት እንዲገባው፣ የቆደመው " የቸገር ሰላም" ዘለዓለማዊነትና ተናፋቂነት እንዲ ታየው ያደርጉታል ። አብዮቱ የመጣላቸው ወደቦች አሁንም በፊውዳሉ ርዕዮተ ዓለም ተጽእኖ ሥር ያሉ በመሆናቸው የኢ.ዲ.ሕ. ፕሮፓጋንዳ ለጊዜው ሊፈታቸው የቻለው "ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን" ይሻላል በሚል የጥንቀት አማራጭ ብቻ ነው ። በተከታታይ ግን አብዮት ለምን እንደመጣና ለማን እንደሚቆም የአካባቢው ሕዝብ ሊገባው በሚችል መስክ ማስረዳት ያስፈልጋል ። የሶሺያሊዝምን መሠረት ሀሳብ፣ ዲያሌክቲካዊ የታሪክ ቁስ አካልነትን

አስተምራለሁ ብሎ መነሳት ጊዜው የማይሆንበት ብዙ ቦታዎች እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል ::

ውጥረት በሌለባቸው ቦታዎች የሚደረገው ቅስቀሳ ወታደራ በሌለበት አካባቢ ነው
የሚደረገው :: ሆኖም ካድሬዎቹ መታጠቅ ይኖርባቸዋል :: በእነዚህ ቦታዎች የኢ.ዲ.ሕ.
ኃይል እንዳይገባና ተቀባይነትን እንዳያገኝ ቅስቀሳ ማድረግ ቅድሚያ ሲሰጠው፣ ግን ሊገ
ባም ቢሞክር በሕዝባዊ ጦር ለመታ እንዲችል ይህንን ጦር የማዘጋጀት ኃላፊነት ይኖርባቸ
ዋል :: የየከተማው ሕዝብም በአብዮት ጥበቃ ኮሚቴ ሥር የሚሆን የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ
ሠራዊት እንዲኖረው መጣጣር ያስፈልጋል :: ከዚህ በፊት ወደ ኤርትራ ይዘምታል ተብሎ ተዘ
ጋጅቶ የነበረው " ሕዝባዊ ጦር " የአብዮትን ጥቅም ፍጹም ሊጠብቅ የሚችል ባለመሆኑ
አዲስ ሕዝባዊ ሠራዊት መቋቋም ይኖርበታል :: ይህ ሠራዊት ደግሞ በገበሬ ማህበራት ስር
መሆን እንዳለበት በግልጽ ማስረዳት ያስፈልጋል :: አሁን በአለው ሁኔታ ይህ አምበዛም
አይታወቅም :: ለአብዮቱ የሚቆም ሕዝባዊ ሠራዊትን በስሩ ለማስተዳደር በመጀመሪያ የገበሬ
ማህበሩም አብዮታዊ ይዘት እንዲኖረው ያስፈልጋል :: እስከ ዛሬ በክፍለ ሀገሬ የገበሬ
ማህበራት አቋም ይህንን የሚያስተማምን አይደለም :: ስለዚህ በብዙ ቦታ የገበሬ ማህበ
ራትን በአዲስ መንፈስ እንደገና የማቋቋም ሥራ መካሄድ አለበት :: ይህ በሚደረግበትና
የገጠሬን ሕዝብ በመደቡ ለማደራጀት በሚሞከርበት ጊዜ በጣም የተወሳሰበው የመሬት ስሪት
በሚገባ መታወቅ አለበት :: ያለበለዚያ አብዮትን ደጋፊዎች ማስቀየምና የአብዮትን ጠላቶች
ማስጠጋት የሚያስችል ስህተት ሊሰራ ይችላል ::

በቅስቀሳውና በማደራጀቱ በኩል በምዕራብ ቆላ ክፍሎች የሚደረገው ከሌላው ቦታ
ይለያል :: በዚህ አካባቢ የሚገኘው የአብዮቱ ወገን በብዙ ሺህ የሚቆጠር የወዝ አደር
ነው :: ምናልባት " ትናንሽ " ገበሬዎችም ሊኖሩ ይችላሉ :: እንደሚታወቀው በመደብ ጠባዩ
የተነሳ የወዝ አደሩ የዚህ አብዮት ወገን እንጂ ጠላት አይደለም :: እንዲያውም ከነቃና
ከተደራጀ የአብዮቱ መሪ እሱ ነው መሆን ያለበት :: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዚህ
አካባቢ ወዝ አደር አብዮትን በጉሪጥ የሚያይበት በቂ ምክንያት አለው :: ይኸውም የመሬት
አዋጁ በእሱ አካባቢ ተፈጻሚነትን ያለማግኘቱ ነው :: አሁንም ይህ አብዮት እውነተኛ ወዳ
ጁን እንዲያውም ባለቤቱን አግኝቶ መቆየት ስለማይችል ወዝ አደሩን መሳብ መቻል አለበት ::
ግን ይህን በተባካ ሁኔታ ለማከናወን በመጀመሪያ ደረጃ ወዝ አደሩን የአርሻው ባለቤት
ወይም መንግሥት እርሻዎቹን ተረክቦ መብቱ የተጠበቀለትና በሥራ ማካሄዱ የሚሳተፍ እንዲ
ሆን ማድረግ ያስፈልጋል :: በአካባቢውም ያሉ " ትንንሽ " ገበሬዎች በሕብረት ሥራ ተደ
ራጅተው የወዝ አደሩን ሳይበዘብዙ ሥራቸውን የሚቀጥሉበት መንገዱ መፈለግ አለበት :: ይህ
ከተደረገ ትክክለኛና ሰፋ ያለ ቅስቀሳ የዚያን አካባቢ ወዝ አደር በቅርብ ጊዜ በሙሉ
ልቡ ለአብዮቱ እንዲቆም ማድረግ ይቻላል :: በመሠረቱ ኢትዮጵያ በዚያ አካባቢ ፀረ አብዮት
ኃይል ከውጭም እንዳይገባ ወደ ውጭም እንዳይወጣ ሊያደርግ የሚችል የሰው ግርግዳ ነው
ያላት :: ግን አልተጠቀመችበትም :: አሁንም ይህንን ከፍተኛ ኃይል መብቱን ጠብቆ አንቅ
ቶና አደራጅቶ ማስታጠቅ የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ::

በጎንደር ከተማ የሚደረገውን ቅስቀሳ ድርጅታዊ አቅጣጫ ማስያዝ ትንሽ ለየት ሊል
ይችላል :: በከተማው ውስጥ መጠነኛ ወዝ አደሮች አሉ፣ በቅርቡ በማጠናከሪያው አዋጅ መሠ
ረት የተቋቋሙ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት የተሻለ አመራር አላቸው፣ በአናርኪስቶች የተ
ወናበደው ወጣትም መደቡን እየለየ ሊሄድ ይችላል፣ መጠነኛ የሆነ ንዑስ ከበርቴ በቢሮክ
ራሲውና በንግዱ ሥራ ላይ ይገኛል :: እነዚህ በሙሉ ወደ አብዮቱ ሊሳቡ የሚችሉበት ሁኔታ



እንዲፈጠር ቅስቀሳው ተመጣጣኝ በሆነ መልክ መካሄድ አለበት :: ከላይ እንደተጠቀሰው
በበጌምድር ክፍለ ሀገር ሳሉት ፀረ አብዮት ኃይሎች ጎንደር ዋና መቀመጫ ነው ::
በዚህም ምክንያት በርከት ያሉ ፀረ አብዮት ፕሮፓጋንዳዎች ይነዛሉ :: የሚደረገው ቅስቀ
ሳና የፕሮፓጋንዳ ሥራ እነሱንም ለማክሸፍ መቻል አለበት ::

የትጥቅ ውጊያ፣

በአሁኑ ወቅት በበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ይህ ወሳኝ ጥያቄ ነው :: የፀረ
አብዮት ኃይል በዚህ በኩል አይሎ መገኘቱ ለብዙ ጊዜ መቆየት የለበትም :: ይህ ቅስቀሳ
ውንም ሆነ ፕሮፓጋንዳውን ዋጋ ቢስ ሊያደርገው ይችላል :: ከላይ እንደተጠቀሰው በአሁኑ
ጊዜ ኢ.ዲ.ሕ. በሱዳን በመረዳት ፀረ አብዮት የትጥቅ ትግሉን ያፋፋመው ዋናው ምክንያት
በርከት ያለ መደበኛ ጦር ወደ ክፍለ ሀገሩ በመሳብ በሌላ አንገብጋቢ ቦታዎች እጥረት
ለመፍጠር ነው የሚል ግምት አለ :: ስለዚህ የአብዮትን የታጠቀ ኃይል ለማጠናከር በሚወ
ሰደው እርምጃ ይህ ሁልጊዜ መገናዘብ አለበት :: ዋናው ወሳኝ ዘሮ ዘሮ ሰፊው ሕዝብ ስለ
ሆነ የትጥቅ ውጊያው በሚደረግበት ወቅት በተለያየ መልክ ሕዝቡን ማስተባበር ያስፈልጋል ::
የጦር ውጊያው የፀረ አብዮትን ኃይል የሚያዳክምና የሚደመስስ ብቻ ሳይሆን ሕዝባዊ የሆነ
ውን የአብዮት ኃይል በተጠናከረ አስተማማኝ ሁኔታ ላይ ሊገኝ እንዲችል ማድረግም አለበት ::

ምናልባት በአለው ተጨባጭ ሁኔታ በየቦታው ያለውን ፀረ አብዮት ኃይል በተመሳሳይ
ጊዜ ለመምታት የማይቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል :: ስለዚህ እንደ አስፈላጊነቱ ቅደም
ተከተል እየተሰጠው በተለያዩ አቅጣጫዎች ያሉትን መደምሰስ ይቻላል :: በመሠረቱ በአሁኑ
ወቅት የኢ.ዲ.ሕ. ሠራዊት የፊውዳል ሠራዊት ጠባይ አለው :: ይህም አውራው በመታበት
የመበታተን ጠባይ ነው :: በዚህም በኩል እንዲታሰብበት ያስፈልጋል :: የፊውዳል ጦር ከመ
ሆኑም ሌላ በግል ደብደግነት ካልሆነ በስተቀር ምልምሎቹ የውጊያ ልምድ የሌላቸው ናቸው ::
እስከ አሁን ያገኙትም ልምድ ይህን ያህል የሚያስተማምናቸው አይደለም ::

የትጥቅ ውጊያ ወሳኝ የሚሆንበትም አንዱ ሌላ ምክንያት የፕሮፓጋንዳ ይዘቱ ነው ::
በገጠር ውስጥ ብዙ በአብዮትና በፀረ አብዮት ካምፕ መሀል የሚወላውል ገበሬ አለ :: አን
ዳንዱም በእምነቱ ለአብዮቱ የቆመ ግን በአካባቢው የአብዮት ኃይል ደካማ በመሆኑ የፀረ
አብዮትን ተጽእኖ ተቀብሎ ተቀምጧል :: ማለትም ቀን ይጠብቃል :: ስለዚህ የሚወላውሉውንም
ወደ አብዮቱ ለመሳብ ቀን ለሚጠብቀውም አይል ለመስጠት የአብዮቱ ኃይል በፀረ አብዮቱ
ኃይል ላይ የበላይነቱን ማሳየት አለበት :: በብዙ ቦታ ከፕሮፓጋንዳ ይልቅ ተጨባጭ ድር
ጊትን ይፈልጋል ::

ከላይ በአጭሩ በለትጥቅ ውጊያ የተጠቀሱትንም ሆነ ሌላ ብዙ ሊኖሩ የሚችሉትን
ነጥቦች በማመዛዘን አጠቃላይ እቅድ በማውጣት አስፈላጊም ከሆነ ቅደም ተከተል ያላቸው
ወታደራዊ እርምጃዎች በማዘጋጀት በማያወላውል አቋም የሚመራ አንድ ማእከላዊ አካል በጣም
አስፈላጊ ነው :: ሰውም መሣሪያውም ሁሉም ቢኖሩ ዘመቻው ያለ እቅድ ከተያዘ ግቡን አይ
መታም :: ይህም ማእከላዊ አካል ግብተኛነት የማያጠቃው፣ የተናጠል ዱላ የማያረካው፣ የተ
ናጠለ መሸነፍ የማያሸብረው ሆኖ አንዳንዱ ጊዜ ጥፍን እምነትም በመሰለ ዘሮ ዘሮ ዱላ
የአብዮቱ እንደሚሆን የሚያምን መሆን ይኖርበታል ::

ከተሞችን ማጽዳት፣

ይህ በተለይ በጎንደር ከተማ በአስቸኳይ መደረግ ያለበት ሲሆን ሌሎቹም የክፍለ
ሀገሬ ከተሞች ከዚህ የሚድኑ መሆን የለባቸውም :: በከተማ ያለው አድሃሪ ኃይል የለበ ለበ

የቡቃው ይመስላል ። "እስቲ አይነካ ከተነካ እንችለው ይሆናል" የሚለው ዘዴ ለአድሃሪው ጊዜ ሰጥቶታል ። አሁን በጎርጡ በጎንደር ከተማ ቢፈራ ሲቸር አንዳንዱ አድሃሪዎችን ቀስ በቀስ በቁጥጥር ስር ለማድረግ በተወሰደው እርምጃ የተቀረው በርግጉ ፈረጠጠ እንጂ ምንም እርምጃ አልወሰደም ። በውነት የወረቀት ነብርነቱን አሳይቷል ከተማ ውስጥ፣ ግን ይህ ዘላቂ ላይሆን ይችላል ። አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረግ አለበት ። ሆኖም ይህ ጥንቃቄ ፍርሃት አዘል ሆኖ እርምጃ እስከ ላለመውሰድ ማድረስ የለበትም ። በከተማ ውስጥ ያለውን የአብዮትና የፀረ አብዮት የትግል ሚዛን በአስቸኳይ መቀየር ያስፈልጋል ። ለዚህም አድሃሪውን አስፈትቶ ተራማጁን ማስታጠቅ ግዴታ ይሆናል ። በብዙ ከተማዎች የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴ ማደራጀትና የጸጥታ ጥበቃ ጓዱ መመስረት ይቻላል ። ትጥቁን ለእነዚህ አካላት ይሆናል ። በተወሰነ ደረጃም ትጥቅ ማስፈታቱ ብቻ በቂ አይሆንም ። ስለዚህም ቀንደኞቹን አድሃሪዎች በቁጥጥር ሥር ማድረግ ሌላው ቢቀር ተመልሰው እንዳይታጠቁ ያደርጋቸዋልና አስፈላጊ ይሆናል ።

በከተማ ውስጥ ሌላ መጠቃት ያለበት የቢሮክራሲውና /በተለይ አስተዳደር/ የፖሊስ ተቋሞች ናቸው ። በእነዚህ ውስጥ የተሰገሰጉ የኢ.ዲ.ሕ. የውስጥ አርበኞች ለመኖራቸው እስከ አሁን የደረሱት ነገሮች ያስተማሩናል ። በኢ.ሕ.አ.ፓም የተወናበዱ አይጠፉም ። እነዚህ ሁለት ተቋሞች ውስጥ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች እያሉ ከላይ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች ብቻ በመውሰዱ ድል ይገኛል ብሎ መገመት አይቻልም ።

2. <u>ከበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ውጭ፣</u>

<u>በተለይ በወሎ፣ በጎጃምና በትግራይ ክፍለ ሀገር</u>

እነዚህ ክፍላተ ሀገር የበጌምድርና ሰሜንን ክፍለ ሀገር የሚዋሰኑ በመሆናቸው የተለየ ጥንቃቄ እንዲደረግባቸው ያስፈልጋል ። በእነሱ ውስጥ ያሉ ፀረ-አብዮት ኃይሎች በሙሉ ከኢ.ዲ.ሕ. ጋር ግንኙነት ለማድረግና የተቀናጀ እርምጃ ለወሰዱ እንደሚችሉ ቀደም ብሎ ተጠቁሟል ። ይህ ተጨባጭ አደጋ በቅድሚያ መወገዱ ስለአለበት በእነዚህ ክፍላተ ሀገር ውስጥ ኢ.ዲ.ሕን የሚያጋልጥ ቅስቀሳ በሰፊው መካሄድ አለበት ። ሰፊው ሕዝብ ይህን አደጋ ተገንዝቦ በተጠንቀቅ እንዲጠብቅ መሆን ይኖርበታል ። መንግሥትም በእነዚህ ክፍላተ ሀገር ያለውን የትጥቅ አቅም በሚገባ ማጠናከር ይኖርበታል ። የኢ.ዲ.ሕ. ወኪሎች ሆነው ጠርነት ሊደፍሩ የሚችሉት ቀደም ብለው ተነስተው ግን በኋላ ተመትተው ጭንቅላታቸውን የቀበሩት ሽፍቶች ስለሚሆኑ እንደገና ከማንሰራራታቸው በፊት ሕዝቡ እንዲያጠፋቸው ማድረግ ያስፈልጋል ። በቢሮክራሲውና በሌላም ቦታ ሊኖር የሚችለውን የኢ.ዲ.ሕ. የውስጥ አርበኛ ለቅሞ ማውጣት ግዴታ ነው ።

<u>በተለይ በአዲስ አበባ ውስጥ፣</u>

በአሁኑ ጊዜ ከበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር እየኮበለሉ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ አድሃሪዎች አሉ ። እነሱን አዲስ አበባ ተቀብላ ማስተናገዱ በሌለባት ቁጥጥር ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው ። እዚሁ አዲስ አበባም የኢ.ዲ.ሕ. የተጠናከረ አካል መኖሩ ስለሚያጠራጥር ጥብቅ ክትትል ተደርጎ የሚጋለጥበት ዘዴ መገኘት አለበት ። አዲስ አበባ የአድሃሪዎች መናኸሪያ መሆኗ አያጠራጥርም ። ከላይ እንደተጠቀሰው አድሃሪ በየትም አቅጣጫ ተሯሩጦ ዞር ዞር የመጨረሻና ወሳኝ የሚሆነውን ትግሉን የሚያካሂደው አዲስ አበባ ውስጥ ነው ። ይህም አዲስ አበባን ልዩ ሁኔታ ላይ ይጥላታል ። አሁንም እንደገና ብዙ



ጊዜ የተነገረውን ለመድገም አዲስ አበባን የአድሃሪዎች መዝናኛ ከሆነችበት ከአሁኑ ሁኔታ በአፋጣኝ ማውጣት ያስፈልጋል ። በዚህ ላይ መንግሥት የያዘው አቋም በጣም አደገኛ መሆኑን መገንዘብ አለበት ። ተራማጆች አንዱ ባንዱ በአድሃሪዎች ሲለቀሙ ምናልባት የቡድን ጥል ነው ብሎ መገመት ካልሆነ በስተቀር፣ ዝም ብሎ ማየት ከታሪክ አለመማር ይሆናል ። የብዙ አብዮቶች የመቀልበሻ ምዕራፍ የጀመረው ከዚህ አይነቱ የድርጊት ገጽ ነው ። ብዙዎቹ ከቀለበሳ የዳኑት ይህን ምልከታ ሲያዩ የማያወላውል እርምጃ በመውሰዳቸው ነው ። አሁንም የኢትዮጵያ አብዮት የሚጠይቀው ይህንን እርምጃ ስለሆነ ሰፊው ሕዝብ አብዮቱን እንከብከብ በመያዝ በደሙ ከጠላት ሊጋርዳት እንዲችል <u>ትጥቅ</u>፣ <u>ትጥቅ</u>፣ <u>ትጥቅ</u> ። ለኢ.ዲ.ሕ. ሴራን ከዚህ የተሻለ ማከሸፊያ የለም ።

<u>በኢትዮጵያ በሙሉ፣</u>

በአሁኑ ጊዜ አብዮቱ ያለበትን ችግር በግልጽ ሕዝቡ እንዲያውቀው ማድረግ ያስፈልጋል ። የኢ.ዲ.ሕና የመሰሎቹ ፀረ አብዮት ድርጅቶች ያላንዓቸ መሸፋፈን ሰፊው ሕዝብ እንዲያውቃቸው መደረግ ይኖርበታል ። ይህ የሚያሳየው የአብዮቱን ደካማነት ወይም ደርግ ኢትዮጵያን በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር አለማድረጉን ሳይሆን የሕዝቡን በጠላቱ ላይ ሳይዘናጋ ነቅቶ የመጠበቅ መንፈሱን መጠናከር ነው ። እርግጥ የአቀራረብ ሁኔታ ሽብርን፣ ያለጊዜው መደናገጥንና ጠላትን ከመጠን በላይ አጉልቶ ማየትን በማያስከትል መልክ መሆን አለበት ። የጠላትን አስጊነትና የሰፊውን ሕዝብ የማይቀር ድል አጣምሮ ማቅረብ ያስፈልጋል ። ይቻላልም ። ጨለማን አሳይቶ ኩራዝም እንዳለ ማረጋገጥ ዞር ዞር ብርሃን ይመጣል የሚለን እምነት እንጂ በጭለማ ተውጬ እቀራለሁ የሚል አስተሳሰብን አይፈጥርም ።

በአሁኑ ጊዜ በተጨባጭ ሁኔታ የምናየው የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስና የሰፊውን ሕዝብ አንድነት፣ የአገሪቱን ነፃነት ለመገሰስ የተነሱት የውጭ ኃይሎችም ናቸው ። ይህ እስከዛሬ በተጠናከረ መልክ ለሕዝቡ ቀርቦ አያውቅም ። በአጠቃላይ አድሃሪ የአረብ መንግሥታት የሚሰሩት ፀረ አንድነት ድርጊት ተወስቷል ። ግን አሁን ይህ ሁሉ ተያይዞ የውጭ ፀረ አብዮት ኃይሎች የሚተበትቡት ሴራ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተጨባጭ ሁኔታ መቅረብ ይኖርበታል ። እርግጥ አሁንም ቢሆን የአቀራረብ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። አንደኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ በማንም ሕዝብ ላይ ቢሆን ጥላቻ እንዳይኖረው፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጠላቶች የማንም ሰፊ ሕዝብ ጠላቶች በመሆናቸው እንዲያውም ከማንኛውም አገር ሰፊ ሕዝብ ጋር የሚያስተባብረው፣ ሁለተኛ በዓለም አቀፍ የተራማጆች መድረክ ላይ የኢትዮጵያን ጠቀናነትና አብዮታዊ አቋም በግልጽ በሚያሳይ መልክ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል ።

<u>ማ ጠ ቃ ለ ያ</u>

ይህች ጽሁፍ ለመጠቆም የሞከረችው የበጌምድርና ሰሜን ክፍለ ሀገር ሁኔታ ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር በማይገነጣጠል መልክ መያያዙን ነው ። መፍትሔውም በአጠቃላይ አብዮቱ ያለበትን ችግር ለመፍታት ከሚወሰዱት እርምጃዎች ጋር የተያያዘ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል ። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ አብዮት ቀንደኛ ተቀናቃኝ በኢ.ዲ.ሕ. መልክ የተነሳበት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። ለብዙ ጊዜ ይህ ተቀናቃኝ ሊቆይ እንደሚችልም ከሌሎች የአብዮት ታሪኮች እንማራለን ። እስከ አሁንም የተራማጆችንና የመንግሥትን አይን በመሳብ ለኢ.ዲ.ሕ. እድገት ሽፋን የሆነው ኢ.ሕ.አ.ፓ. አሁን ለዚህ አገልግሎቱ ወርቃውን መቀበያ ጊዜ ስለሆነ ሄዶ ከኢ.ዲ.ሕ. ተቀላቅሏል ። ይህ ሁኔታውን ትንበ

ይቀይረዋል ። ሆኖም እንኳንስ ኢ.ዲ.ሕ. ምንም የተራማጅ ሽፋን የሌለውንና እንደዚያ የሰፊውን ሕዝብ በተራማጅ ካባው ውዥንብር ውስጥ የጣለውን ኢ.ሕ.አ.ፓን በአጭር ጊዜ ውስጥ ያጋለጠው የሰፊው ሕዝብ ትግል አሁንም እንደሚያሸንፍ ጥርጥር የለም ።
ግን ይህ ለአብዮቱና ለሰፊው ሕዝብ ቆሚያለሁ የሚለው መንግሥት ከዚህ በፊት ይህንን በድርጊት እንዳረጋገጠ ሁሉ አሁንም ወሳኝ በሆነ ወቅት ባያወላውል በድጋሚ በድርጊት ካላረጋገጠ የሰፊው ሕዝብ ድልና የአብዮቱ እድል አጠራጣሪ ሁኔታ ላይ ይወድቃል ።

============== ////// ==============

የካቲት 1969

የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት
የፍልስፍና ማስፋፊያና ማስታወቂያ ኮሚቴ
የወለጋ ክፍለ ሀገር ወርሀዊ ሪፖርት
የካቲት 1969

<u>በዓላት</u>

የአድዋን ድል ምክንያት በማድረግ በብዙ ሺህ የሚቆጠር የከተማው ነዋሪ በአብዮት አደባባይ ቀደም ብሎ ወደ ተዘጋጀለት ቦታ ተገኙ፤

1. በአድዋ ድል ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ የፈለገችው ኢጣሊያ ቅስሟ ተሰብሮ ከአገራችን በከባድ ተጋድሎና ቆራጥነት መውጣቷን፤

2. የነቢዩ መሐመድ የልደት ቀን ሁኖ ለእስላም ወገኖች ሃይማኖት መሪ መሆኑን በማውሳት፤

ሀ/ የማዘጋጃ ቤት ሹም
ለ/ የከተማው የትምህርትና የመስጊድ ኮሚቴ አባል፤
ሐ/ የአውራጃው ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አባል፤
መ/ የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ
ሠ/ በክፍለ ሀገሩ የሠፈሩት የደርግ አባል ንግግር አድርገዋል ።

ከየት/ቤቱ የተውጣጡትም ወጣት ተማሪዎች አብዮታዊ መዝሙሮችን እስ ምተው በዓሉ አበቅቷል ። በዚህ ቀን በጣም ትዝ ከሚሉና በሕዝቡ ቅሬታን ካስ ደረጉት ውስጥ <u>የቦክሲቱ</u> ፀሐፊና ቸው ከበለው የሚጠሩት የክ/ሀገሩ አስተዳዳሪ በፀረ ኢምፔሪያሊዝም አንድም መከበር የነበረበትን በዓል በዓላቸው በፀረ ሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት አንፃር ባገነው "አንዳንድ ድርጅቶች እና ብቻ አለን የሚሉ ከስንፍና የተነሣ ሥራቸውን ሳይሠሩ ቁርተው የቢሮክራሲ ማነቆ የሚሉትን መን ግሥት እነዚህ አብዮቱን እንዳይበርዙ አጥር መጠበቅ አለበት "ማለታቸው ነው ።

በተረፈ በዓሉ በደህና ሁኔታና ፀረ ኢምፔሪያሊዝም አንድም ባዘሉ ንግ ግሮችና መፈክሮች ታጅቦ ተከራክሯል ።

የካቲት 27 ቀን 1969 ዓ.ም. ይህ ቀን በነቀምቴ በፊት የከ/ሀገሩ ከተሞች ከፍ ባለ ሁኔታ ተከበረ ::

ነቀምቴ የከተማው ሴቶች በየቀበሌያቸው ስር ተሰልፈው በመከታተል አብዮት አደባባይ ደርሰው በታቸውን ያዙ፤ ከዚያን፤

1. የከ/ሀገሩ ሴቶች አንቂ ጓዶች አባል ወት/አሰለፈች አያና የበዓሉን ዓላማ አብራርታ
2. የሴቶች ተወካይ ሲያስቃያቸው የቆየውን በዝባዥ ሥርዓቶች
   ሀ/ የሰጅ በወንድ ስም መጠራት
   ለ/ የወንዶች ከቤት ይበለጣሉ ተበሎ መታሰብና መነገር፤ በመናገር፤
   ሐ/ የወንዶች በቤት ማዘዝ፤ አገስተው ለወደፊቱ ሥርዓቱን ለመደምሰስ ከወንዶች ወገደሞቻቸው ጋር በመሆን እንደሚዋጉ፤ ገለጠው

3. የወጣት ሴቶች ተወካይ፤ ወጣቶች ሴቶች በአብዮቱም አንጻሻቹ የሚያነቃቃ ንግግር በግጥም አገባ፤

4. ከዘጠኙ ቀበሌ የተውጣጡት እናቶች ወኔ የሚቀሰቅሱ ቀረርቶዎች ና ፉከራዎችን አሰምተው፤

5. ወጣቶች የሴቶችን ጭቁ የሚያመለከት ድራማ በማሳየት ለወደፊት ሊደረገ እንደማይ ቻለና ከጓደኖቻቸው ጎን በመሆን ሥርዓቱን እንደሚዋጉ አረጋገጠዋል ::

የደርግ አበሳት

የካቲት 12 ቀን 1969 ዓ.ም. በከተማው /ነቀምቴ/ የአብዮት አደባባይ ሕዝቡ ተጠርቶ ወጥቷል፤ ከዚያም በከፍለ ሀገሩ የተመደቡት የደርግ አባላት አስተባባሪነት፤ ስብሰባ ተካሄደ፤



1. በፋሽስት ኢጣሊያ የተጨፈጨፉት ሰማዕታትና ለአብዮቱ የሞቱት ጓዶች ታሰበዋል ::
2. የኢትዮጵያን አንድነት ለማናጋትና አብዮታችንን ለመቀልበስ የሚፍጨረጨሩት አድሀሪያንን የከፍለ ሀገሩ ሕዝብ ነቅቶ እንዲጠባበቅ፤

   ሀ/ የቀድሞ በዝባዥ መሳፍንትና መኳንንት ተጠሪዎች የሆኑት እነ መንገሻ በዕምና ነጋ ተገኝ የድሮውን ሥርዓታቸውን ለመመለስ በሰሜን ክፍለ ሀገር ከጭቁኑ መለዩ ለባሽና አርሶ አደር ጋር በከፍተኛ ግብግብ ላይ መሆናቸው፤

   ለ/ የኤርትራን ጉዳይ መንግሥት በበጤራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት መለስተኛ ፕሮግራም ለመፍታት ጥረት እያደረገ የአካባቢ አድሀሪ ኃይሎች በጎን በአብዮቱን ማሴራቸው፤

   ሐ/ በውስጥ በተለያዩ የቀጸል ቦዎች እየተጠሩ አብዮቱ እንዲከሰብ ማድረጋቸው በስፊው ተብራርቶ፤ ለዚህም ተራማጅና አገር ወዳድ የሆነ ሁሉ ይህን አውቆ አቋሙን እንዲለይ፤ ለሀገሩም በቁራጥነት እንዲቆም ጠይቀዋል :: ከዚያም፤ በስብሰባ ተካፋዮች፤

   ሀ/ የትጥቅን መዘግየት፤
   ለ/ የከተማውን አድሀሪያን ትጥቅ አለመፍታት፤
   ሐ/ የተያዙት አድሀሪያን አብዮታዊ ቅጣት ሳይቀበሉ መለቀቃቸው በማመለከት ጥያቄዎች ቀርበው መልስ ተሰጥቶባቸዋል :: በዚሁ ቀን ሻምበል ለምቤ እታለማሁ የተባለው አድሀሪ በ1968 ዓ.ም. አምስት ዘማቾችን ከሰብአዊ ርኅራኄ ውጭ ገድሎ ማምለጡና ባካባቢ ሕዝብ ትብብር መያዙ ተነገሮ፤ አብዮታዊ ቅጣት እንዲፈጸምበት እንዲደረግ ጥያቄ ቀርቦ፤ ፊትም ሕዝቡ ሲጠይቀው የቆየ ጥያቄ የአስተዳደር ክፍሉ "ያገኑን ሰው መብት መንካት አይገባም" በሚል አጉል ርኅራኄ ያቆየው መሆኑን በመረዳት አብዮታዊ የአስተዳደርና የልማት ኮሚቴ ጥሩ ቀን በጥምና ዓይነት ቅጣቱን እንዲፈጸምበት የደርግ አባላቱ ወስነዋል :: በዚሁ መሠረት የካቲት 17 ቀን 69 ዓ.ም. ወንጀሉን በፈጸመበት በሆሮ አውራጃ በጀማ ገነቴ ወረዳ በየዱ ቀበሌ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አብዮታዊ ቅጣት ተፈጸመበታል :: በዚህን ጊዜም ሕዝቡ በጭፈራና በእልልታ የተወሰደውን እርምጃ ደገፉ ::

## የከተማ ቀበሌ ሕብረት ሥራ ማኅበርና የተከናወኑ ሥራዎች

በየከተማዎቹ ያሉት የከተማ የሕብረት ሥራ ማኅበራት አንዳንድ ድክመቶች ለምሳሌ ተቀራርቦ የመሥራት ለዘብተኛነት ቢታዩባቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ ጠቃሚ የልማት ሥራዎችን እያከናወኑና የከተማዎችን ፀጥታ ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ እየተቆጣጠሩ ናቸው ። በነቀምቴ ከተማ የ04 ቀበሌ በዚህ ወር ከኢኮኖሚ አሻጥረኞች ብዝበዛና ምዝበራ ለመዳን ባደረገው ጥረት፤ $166633/ አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር/፤

ሀ/ ሁለት የእህል ወፍጮ

ለ/ አንድ መጋዘን አሠርቶ አስመርቋል ። በዚሁ ወቅት፤

ሀ/ የቀበሌ ኅብረት ሥራ ማኅበር ሊቀመንበር

ለ/ የክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ፤ በየተራ ባደረጉአቸው ንግግሮች የከተማው ነዋሪ ሕዝብ በከተማ ከመሸጉት አሻጥረኞች ለመዳን እነርሱንም ለማጥፋት ከፍተኛ ንቃትና ድርጅት እንዲኖረው ማስፈለጉንና ምን ጊዜም ቢሆን በአብዮት ውስጥ ጥቅማቸው የተነካባቸው አድሀሪያን ልዩ ልዩ ፀረ አብዮት ድርጊት ከመፈጸም የማይቦዙ ስለሆነ ጭቁኑ ተደራጅቶ አድሀሪውን መደምሰስ እንዳለበት አስረድተዋል ። በቀበሌው ሴቶች የተሠሩ የእጅ ሥራ ውጤቶችም ተሽጠዋል ። የተለያዩ አብዮታዊ መዝሙሮችም በቀበሌው ወጣቶች ተዘምረው አብቅቷል ።

2/ የአካባቢው ገበሬዎችና ጭቁን የከተማው ነዋሪዎች ከብዙ ጊዜያት ጀምረው በየከተሞች ከነትጥቃቸው የመሸጉት አድሀሪያን እንዲፈቱ ሲጠይቁ ኖረዋል ። የአስተዳደሩ ክፍል ግን "የሰው መብት መንካት" በሚለው ፀረ መደብ ትግል አመለካከት ውጭ ያሉትን ከማስፈታትም በከፍተኛ ወንጀል የታሰሩትን እንኳ ሲያስለቅቅ ኖረዋል ። የሕዝቡ አብዮት በእውነት ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት መሸጋገሩ የሚረጋገጠው ሲታጠቅ ብቻ ስለሆነ ለዚህም በአድሀሪያን እጅ ያለውን አስፈትቶ መታጠቅ ተፈላጊ ነው ።

በሕዝቡ ጥያቄ መሠረት በክ/ሀገሩ የተመደቡት የደርግ አባላት በነቀምቴ ከዘጠኙ የቀበሌ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ተመራጮች የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት አባላትን የዘጠኙ ቀበሌ ተራማጅ ወጣቶች ተራማጅ የፀጥታ አስከባሪዎችንም በማስተባበር አድሀሪያንን አገኙበት ገብተው በተካከ ሁኔታ ትጥቅ አስፈትተዋል ።



በጊምቢ ከተማ በቄለም አውራጃም በደምቢ ደሎ በሙጊ ወረዳ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት አባላት የከተማዎችን ቀበሌ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በማስተባበር ተመሣሣይ እርምጃ ወስደዋል ።

3/ የደርግ አባላም፤ የከተማውን ወጣቶችና የቀበሌ ሕብረት ሥራ ማኅበራትን አንድ ላይ በመጥራት የካቲት 26/69 ዓ.ም.

ሀ/ አድምን

ለ/ የቀበሌ ኅብረት ሥራ ማኅበር አሠራርን

ሐ/ የተፈታውን ትጥቅ እንዴት መጠቀም እንደሚገባ በማመልከት ሰፋ ያለ ገለጻ አድርገዋል ። ከዚያም በከተማው /ነቀምቴ/ ወጣቶችና የኅብረት ሥራ ማኅበር በመካከላቸው ያለውን ቅራኔ በመፍታት ክንዳቸውን በማጠንከር አድሀሪያን ላይ እንደሚዘምቱ ተስማምተዋል ።

**ቢሮክራሲ ፤**

የክፍለ ሀገሩን ሕዝብ አብዮት ለቅልበሳ በማመቻቸት ላይ ያለው የክፍለ ሀገሩ ቢሮክራቶች ድርጊት ነው ። ቀደም ሲል በቄለም አውራጃ ለጥበቃ ተብሎ የብሔራዊ ጦር አባላት በደምቢ ደሎ እንዲሰጥና አካባቢውን እንዲጠብቁ ተብሎ ነበር ። በዚህ ዓመት ግን የደረሰ ነገር ምንም ሳይታወቅ ያሉት የብሔራዊ ጦር አባላት ተነስተዋል ። ቢጠየቅ የደረሰውን ነገር ሊታወቅ አልተቻለም ።

እንደዚሁም ያለው የጦር መሣሪያ ለአካባቢው ሳይታሰብ በሙሉ ተነስቷል ለምን እንደሆነ የአስተዳደሩ ክፍል ቢጠየቅ ደሮ ዓባ ለበስ ሆነ ።

የወለጋና የሱዳንን ጠረፍ ጥበቃ በሚመለከት ጉዳይ ከሥፍራው በመገኘት የተጠና ቀረው ሪፖርትና ለጊዜው መፍትሔ ይሆናሉ ተብለው የተሰጡትም ሃሳቦች እንዱም መልስ ሳያገኙ ቀርተዋል ።

በከተሞች፤ በነቀምቴ፤ በጊምቢ፤ በደምቢ ደሎ፤...ወዘተ የመሸጉት አድሀሪያን ትጥቅ ይፈታ ተብሎ ሲጠየቅ "አይ፤ የግለሰብን መብት መንካት አይፈቀድም አይነር ሊበላል እንዴ" ተብሎ ዘገይቶ ቆይቷል ። አሁንም ቢሆን ፀረ አብዮት ድርጊቶችን በረቀቀ ዘዴ በመፈጸም አብዮትን ለቅልበሳ እያመቻቸ ነው፤ ሁኔታውም ለተፈላጊዎቹ እየተከሰተላቸው መጥቷልና አብዮትን ሳያስቀለብሱ እንደሚደመስሱ እንተማመናለን ።

<u>የመሳፍንትና የባላባቶች ድርጅት /ኢ.ዲ.ህ/</u>

ኢ.ዲ.ህ ተብሎ የሚጠራው አድሀሪ ድርጅት በነጋ ተገኘ በነመንገሻ ስዩም የበላይ ጠባቂነት ጭቆናን ሕዝብ ከአረብ አገር በማመጸወቱና በሚያገኙት ገንዘብ የራሱን አብዮት አሳልፎ እንዲሰጥ ለማስደረግ በሱዳን አገር በከፍተኛ ዝግጅት ላይ እንዳሉ ተደጋግሞ ተነግሯል ::

የዚህ ድርጅት የፖለቲካ ረዳት አባልና በወወጋ ክፍለ ሀገር ፀሐፊ ተብሎ የተሰየመው አቶ አምባው ለሙ የድርጅቱን አድሀሪነትና ፀረ ጭቆን ሕዝብ አቋሙን ድርጅቱን ከድቶ በመውጣት ከሕዝባዊ ሠራዊት ጋር ወጥቶ አሰሳ በማድረግ በድብቅ የቡድኑን አባላት ገደሎ ልዩ ልዩ፣ ሰነዶች

ሀ/ የኢ.ዲ.ሁ ጠቅላላ ምስጢር

ለ/ የአባላት ስም ዝርዝር

ሐ/ በክ/ሀገሩ የጦር መሪ ተብሎ የተሰየመው የአስገዱ መርዕድ ሁለት ቡሬና ሽሚዝ እንዲሁም መታወቂያ፣ ካርድ፣ 2400፣ ጥይት፣ 2 ዓምተፎር፣ 2 ቦምብ አስጥሎ ተመልሷል፣ ከአውራጃው ፀጥታ እስከ ባሪያዎች ዓለሙ ገለታ የተባለው ወታደር ሳምት በድብቅ የሚሆኑ ደግሞ መጠኛ የመቅሰል አደጋ ደርሰባቸው በሙሉ ድነዋል :: በዚሁ ወቅት የሕዝባዊ ሠራዊት አባላትና የአካባቢው አርሶ አደሮች ከልብ የመከላከል ባደ እጃቸውን ወጥተው እንደነበርም ተነገሮ ያም ዱል ሊገኘ የቻለው አቶ አምባው ከጠላቱ መኸል በመግባት አንጉን በተማረው የጦር ታክቲክ ገደሎ በተቀበለው መመንኛ መሆኑም ተገልጧል ::

አቶ አምባው እንደተናገረው ከሱዳን ወለጋ ክፍለ ሀገር ከገቡ ስድስት ወር ሲሆናቸው የቁለም አውራጃ ቀኝ ሌት በመዘር እንዳዳረሱ አማካይ ይሆናሉ የተባሉትንም ቦታዎች በደምብ እንዳዘጋጁ አስረድተዋል ::

አቶ አምባው አሁን በአውራጃው እየዘዋወሩ የገበሬ ተብሎ ማኅበራት የሕዝባዊ ሠራዊትን የጦር ታክቲክ እያሰለጠኑ ነው :: በአሰሳ አውራጃም ሰፈን ሰሰ የተባለው አድሀሪ የመሬት ከበርቴ ሕዝቡን እያስቸገረና ለኢዲህ አባልነት እያስመዘገባቸው መሆኑ ይነገራል :: ለዚህም የጊዳሚ ወረዳ ሕዝባዊ ሠራዊት አባላትና ፀጥታ አስከባሪዎች በጋራ ጊሚ አካባቢ አሰሳ እያደረጉ ናቸው ::



<u>ገበሬዎች</u> በየቦታው ገበሬዎቹ የመደብ ጠላቶቻቸውን እስከመጨረሻው ለመዋጋትና መብታቸውን ለማስከበር ቆርጠው ተነስተዋል :: በየጊዜውም ስብሰባና ሴሚናር እያዘጋጁ የመነጋገሪያ አርእስቶችም ቆርበው ይወያዩባቸዋል :: ከወረ ከቁለም አውራጃ የተውጣጡት ገበሬ ተወካዮች የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት አባላት፣ ከአስተዳደር የተካፈሉበት የኢኮኖሚ በሽሽል ግንኙነቶችና ባሕል እንደዚሁም ስለፖለቲካ የተወያዩበት ከየካቲት 20-25 ሴሚናር ተካሂዷል :: በዚህም ሴሚናር ላይ በክ/ሀገሩ የተሳኩት አንዳንድ ሰዎች የአውራጃውን ሕዝብ በጠባብ ብሔረተኝነት አሳብ ለመርዙት ባደረጉአቸው ገለጻዎች ምክረው ሥፍራው በተገኙት የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት አባላትና ተራማጆች በቅሉ ከሽፏል፣

በዓሌ ሰዒ ወረዳ የሚገኙትም አርሶ አደሮች ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ የፀረ አብዮቶችን ሴራ አውግዘዋል ::

<u>አናርኪስቶች፣</u>

በነቀምቴ ከተማ ከተለያዩ ቦታዎች በመምጣት ከከተማው ሕዝብና ተማሪ ጋር በመቀላቀል ሲያወናብዱ ቆይተው አምልጠው የሄዱትን ለመሄድ ያቀዱትን እንደዚሁም ከአርሶ አደሩ ለመቀላቀልና ሲያወናብዱ የተነሳባቸውን ወጣቶች የቀበሌ ሠራተኞችና ተራማጅ ወጣቶች በአሰሳ ይዘው አስረዋል ::

በአርጆ አውራጃ በተወደደ መኮንን 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ አብዮታውያን ተማሪዎች ሰሞኑን ጠቅላላ ስብሰባ አድርገው 16 የኢህአፓ ነፍሰ ገዳይ ቀጥረኞችንና ፀረ አብዮቶችን ይዘው በቁጥጥራቸው ስር አውለዋል :: እነዚህ የኢህአፓ ምልምሎችና የሲአይኤ ቀጥረኞች ሊጋለጡ የቻሉት፣

ሀ/ በት/ቤቱ ውስጥ በሚደረገው አብዮታዊ የውይይት ክበብ ላይ ለመገኘት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው

ለ/ አንዳንድ ጊዜም ውይይትን አቋርጠው በመውጣት

ሐ/ በአለቱ በት/ቤቱ ላይ ፀረ አብዮት ድርጊት ለመፈጸም በመምከራቸው ነበር ::

በአለቱም በት/ቤቱ አጥር ግቢ ብዙ የመደባደብና ተኩስ ነበር ግን የሞተ ሰው አልነበረም :: ከእነዚሁም 16 የኢህአፓ ምልምሎችና የሲአይኤ ቀጥረኞች ተማሪዎች የቀድሞው የመሬት ከበርቴ የከተማ ቦታ ትርፍ ቤት የተወረሰባቸው ናቸው ::

እነዚሁ ተማሪዎች "ቅስቀሳና" "ንቃት" በተባሉ ወረቀቶች የሚታለሉና የሚወናበዱ አልፈውም የቀሩትን የሚያወናብዱ ናቸው ::

"ቅስቀሳና" "ንቃት" "ስለኢህአፓ አሸናፊነት" የሚያበስሩና የኅብረተሰቡን ስድብ ያዘሉ ጨቅላ ወረቀቶች /መሆናቸው ተገልጧል/ በገምቢ አውራጃም በገምቢ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ግቢ ውስጥ ፀረ ጭቁን ሕዝቦች አብዮት ወረቀት በኢህአፓ አባላት ተበትኖ በተራማጆች ጥረትና አርቆ አሳቢነት በክትትል ተደርሶባቸው 21 ወጣቶችና አንድ ቀንደኛ /ወረታ ገ/ማርያም/ ተይዘው ታስረዋል ::

ተጠቃሹም /ወረታ ገ/ማርያም/ የተባለው ቀንደኛ ከዚህ በፊት የኢህአፓ ቀጥረኛና የሲአይኤ ምንደኛ እንደነበር ብዙዎቹን ወጣቶችም እንዳወናበደ አምኖ በድርጊቱ ተጸጽቶ ለወደፊት የቀሩትን የኢህአፓን ነፍሰ ገዳይ ቡድን ተከታዮችን አሳምኖ በትክክለኛው የትግል ጎዳና ከጭቁን ሕዝቦች አባሎች ጋር እንደሚሠራና አብዮትን እንደሚደግፍ ቃል ገብቷል :: ሆኖም እነዚህም ወጣቶች በፖሊስ ቁጥጥር ስር ይገኛሉ ::

ማጠቃለያ ፣

ከሞላ ጎደል የጽ/ቤቱንና የከ/ሀገሩን አጣዳፊ ችግሮች በጥር ወር 69 ዓ.ም. ሪፖርት አቅርበናል፣ በተለይ ባሁኑ ጊዜ ለጽ/ቤቱ ሥራና ለከ/ሀገሩ ጭቁን ሕዝብ አደገኛ መስሎ የሚታየን፣ የከ/ሀገሩ ሕዝብ ባንድነት ክንዱን አጠንክሮ በመደብ ጠላቶቹ ላይ መነሳት ስለጀመረበትና ሕዝቡም ሆነ ጽ/ቤቱ ለዚህ ሲሠራ የአስተዳደሩ ክፍል ባካባቢው የሚገኙትን የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት አባላትን ማጥላላትና ጽ/ቤቱ ሳንድ ድርጅት ብቻ የተደገፈ ለማስመሰል ይሞክራሉ :: ከጊዜ ወደጊዜ እንደታየውና ለወደፊትም ቢሆን እንደሚታየው በጠባብ ብሔረተኛነት በሽታ የተያዘ ስለሆነ መፍጋት /መከላከል/ ተደምሯል :: መንግሥትም በዚህ ነገር ድጋፉን እንደመጠመር እነዚህን ለመከላከል እንዲረዳ እንጠይቃለን ::

በከ/ሀገሩም ያሉት ገበሬዎች አብዮትን ተቀብለው የባላባታዊውን ሥርዓት ለመደምሰስ ቆርጠው ተነስተዋል :: ለዚህም ከጽ/ቤቱ ጋር ቀርብ ግንኙነት



አላቸው :: ከገበሬው መካል ግን ታምኖባቸው ገበሬዎችን ይመራሉ ተብለው የተመረጡት ጥቂት ተወካዮች ፊት የያዙትን የአሠራር ዘዴ ሳይቀይሩና ሳያሻሽሉ ቁርተው በጊዜው ሁኔታ ተወናብደዋል :: በዚህም ፊት ከቀ/ጸ/ቤቶች ጋር በቅርብ በመወያየት ይሠሩ የነበረት አሁን የማጥላላት ዘመቻ ጀምረዋል :: ለዚህም በተቻለ መጠን በቀ/ጸ/ቤቶች አባሎች እነዚህ ሰዎች የጊዜውን ሁኔታ እንዲረዱ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው ::

የከተማ ቀበሌ ነበረት ሥራ ተመራጮች ደህና ሁነው ሳሉ በጥቂቶች ከአስተዳደሩ ክፍል የቢሮክራሲ በሽታ እየተጋባባቸው ነው :: ይህንንም ለማረም ሂስና ግለሂስ እንዲደረግ ተወስኖ ባንዳንድ ቦታዎች ተደምሯል ::

ከዚህ በፊትም ሆነ አሁንም የተራማጆችና ለአብዮቱ ፍስትና ጽ ጥያቄ ትጥቅ ነው :: ለዚህም በክፍለ ሀገሩ በተደረጉት የደርግ አባላት እንደተነገረው በእውነት ለአብዮቱ የቆሙት እንደሚታጠቁ ነው :: ይህም በአጭር ጊዜ ውስጥ በጋደኛነት ብቻ አብዮተኛ ነን ለሚሉትና ለነቁ አድሀሪያን ሳይሆን ከቢሮክራሲ ወጣ ውረድ ነፃ ሆኖ የአብዮትን ልር በተከተለ ሁኔታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተራማጆችና የጭቁን ሕዝብ ወገኖች እንደሚታጠቁ ተስፋ እናደርጋለን ::

ፀረ አብዮተኞች ይወድማሉ

የጭቁን ሕዝቦች አብዮት ያሸንፋል ::

## የ ሰ ር ጎ ገ ቦ ች

ሰርጎ ገቦች በሠሰቱም አውራጃዎች ማለትም በአረር በደምደምና በነገሌ ቦረና በብዛት መግባታቸውና ፀረ–አብዮት የሆኑ ድርጊት በመሥራት ላይ መሆናቸውን ደጋግሞ መገለጹ የሚታወስ ነው ። ይሽው የሰርጎ ገቦች ፀረ–አብዮት እንቅስቃሴ ባሁኑ ጊዜ አይሎ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ።

ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና የኢትዮጵያን ግዛት ቆርሶ ለመውሰድ ላላት አቅዱ ከኢምፔሪያሊስቶችና ከአድሃሪ የአረብ መንግሥታት በምታገኘው እርዳታ በሠለቱ አውራጃዎች ከየብሔረሰቡ የሚገኙትን ዘላን ኢትዮጵያውያንን በማስታጠቅ ሽብር ዘርፍታና ገድያ እንዲኖር የምታደርገው ሶማሊያ ናት ። በተለይ ከየብሔረሰቡ ለዘላን ነት ኑሮ የተሰማሩ ሰዎች እርስ በርሳቸው በሚያደርጉዋቸው ግጭቶች ቅራኔዎች በመሀከላቸው እንዲፈጠሩ ስላደረገ አብዮቱን ለመቀልበስ ሶማሊያ ላላት ዓላማ ደህና መሣሪያ በመሆን አብዮቱ የመጣላቸው መሆኑን ባለመረዳት በአብዮታቸው ላይ ጠላት የሆኑት እነዚህ ዘላኖች ናቸው ። አሁን ከሶማሊያ መሣሪያ የወሰዱ ዘላኖቹ ለሚፈጽሙት ድርጊት መነሻ የሆነው ምክንያት የብሔረሰቦች ግጭት ነው ። ሰርጎ–ገቦች ራሳቸው የብሔረሰብ ግጭት ውጤት ናቸው ። ሌላው ለሰርጎ–ገቦች አመቺ ሁኔታ የፈጠረው የቦርከራሰው ሣራ ነው ። ብሔረሰቦች ግጭት በሚያደርጉበት ጊዜ በቅጽበት አስፈላጊው ርምጃ በወሰዱ ኖሮ ዘላኑም ክፍል ይህንን ያህል ለመሣሪያ ብቻ ብሎ ችግር አይፈጥርም ነበር ። ሰርጎ–ገቦች መግባት እንደጀመሩ እርምጃ እንዳይወሰድ በቦርከራሰው እንቅፋት ባይሆን ኖሮ የሰርጎ–ገብ ችግር በተቃለለ ነበር ።

ከጥር 2 ጀምሮ እስከሁን ድረስ በአረር አውራጃ በሃገረማሪያም ወረዳ ከሶማሊያ ሄደው መሣሪያ ጠመውሰድ ለሶማሊያ አድሃሪ የተካከለ ሣራ መሣሪያ በሆኑት በዳዋ ክፍል ውስጥ በሚገኙ ዘላን የጉጂ ግሣና በደጋው ክፍል በሚገኙ በጉጂ ገበሬዎች መሀከል እስከሁን ድረስ ከፍተኛ ውጊያ በመካሄድ ላይ ነው ። እስከሁን ድረስ ከገበሬው ክፍል ከአስር በላይ የሚሆኑ ሰዎች ሲገደሉ ወደ ስድስት የሚሆኑ ገበሬዎች ቆሰሉና ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል ። ከወንበዴዎች መሀከል እስከሁን ወደ 30 የሚሆኑ ተገድለዋል ። ገበሬው ለነዚሁ ሠርጎ ገቦች ገብረ አበር የሆኑትን 20 ሰዎች ረሽኗል ። እነዚሁ ወንበዴዎች፣

ሀ/ ዉለማን ተገን በማድረግና መሣሪያ ያላቸውን ሰዎች ቤት በመከበብ ከገበሬው ክፍል ብዙ መሣሪያ ዘርፈዋል ። ከገበሬ ሚሊሺያዎችም ቤታቸውን በሌሊት በመከበብ ወይም ለብቻቸው ሲሄዱ መንገድ ላይ አድፍጠው በመጠበቅ መሣሪያቸውን ነጥቀዋል ።

ለ/ የገበሬውን በሬ በብዛት ዘርፈዋል ።



ሐ/ ከነርሱ ጋር በሀሳብም ሆነ በድርጊት የማይስማሙትንና የሚቃወሙትን ሰዎች ከብቶች በጅምላ ወርሰዋል ። መሣሪያ አለባም አድርገዋል ።

መ/ በናገዜዋ ከተማ 13 ሚሊሾች ገድለዋል ። ልጆነትና ደም ግባት ያላቸውን ሴቶች በማስገደድ መልካ ሶዩ ወደተባለው ካምፓቸው ወስደዋል ።

ሠ/ የቀለንቦ ከተማን ደምስሰው የነዋሪዎችን ቤት ንብረትና ሱቅ ዘርፈዋል ።

ረ/ የፍርድ ሸንጎ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላትንና የሊቀመናብርትን ቤት እየሰባበሩ ሲዘርፉ እነዚሁኑ የገበሬ መሪዎች ከሰባዊ ርኅራኄ ውጭ በሆነ መንገድ ይዘው በማሰር እየደበደቡ አንገላተዋል ።

ሰ/ በትራንስፖርት መኪናዎች ላይ ተኩስ በመክፈት ከሀገረማሪያም ከተማ በታች ንግድ ወይም የትራንስፖርት መኪናዎች እንዳያልፉ አድርገዋል ።

ሸ/ በጌድኦና በጉጂ ብሔረሰቦች መካከል ቅራኔ እንዲፈጠር ምክንያት ሆነዋል ።

ቀ/ በቡርጂ ብሔረሰቦች ላይ እነዚህ ወንበዴዎች ዘምተው የቡርጂ ወረዳ ዋና ጸሐፊንና አንድ ሕፃን ሲገድሉ ከወንበዴዎች ወደ መሀከል ስድስት ተገድለዋል ። እነዚህ ወንበዴዎች ወደ ቦረና ብሔረሰቦች ዘምተው በከብት በሚተዳደሩ ዘላኖች ላይ ብዙ ከብቶችን ሲዘርፉ አያሌ ሰዎችን ገድለዋል ።

### በሰርጎ ገቦች ምክንያት የጉጂና የጌድኦ ብሔረሰቦች ግንኙነት እንዴት እንደ ተበላሸ

በሀገረ ማርያም ወረዳ በዳዋ ምክተል ወረዳ ጋሌባ፣ ቀርጫ፣ ቦኬ፣ ብሌዳ፣ አሩሲ ዓርባና ቦቦርቻ በተባሉ ቀበሌዎች በሚኖሩ የጉጂና የጌድኦ ብሔረሰቦች መካከል ሰርጎ ገቦች ከመግባታቸው በፊት፣

ሀ/ ጌድኦች ደን መንጥረው እንሰትና ቡና ለመትከል ሲፈልጉ ጉጂዎች ደግሞ ቆፍ የምንሰቀልበትን ደን እንዴት ታጠፋብናላችሁ የሚል

ለ/ ጌድኦች በፍርድ ሸንጎ፣ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት ውስጥ ስለበዙበትና ሊቃነመናብርት በሆኑበት አካባቢ ሥልጣናቸውን ተገን በመደረግ በተራው የጉጂ ገበሬ ላይ ተጽዕኖ ስለሚያደርጉ

ሐ/ በመስከረም ወር ሰርጎ-ገቦች ከደምቢዶ አውራጃ ፈለሰው ብጪ የምትባል ትንሽ ከተማ በቀጥታ ቸው ሥር ባደረጉበት ጊዜ ሰርጎ-ገቦችን ለመደምሰስ እርዳታ ከጌዶስ ተጠይቆ ነበር ። የጌዶስ አውራጃ ሚሊሺያዎች ከሥነ ሥርዓት ውጭ በሆነ መንገድ ገለሻገረደቸን ሕግ ያጠፉ ስለነበር፣ ወንበዴ ሆነው ከአንዲት ቡት ጋር የሥጋ ግንኙነት ያደርጉ ስለነበር ወገብዛ ሀገውን ሳይለዩ የአካባቢ ገበሬ ቤት ይዘርፉ ያቃጥሉና ከብት ዘርፈው በማረድ ይበሉ ስለነበር በጉኚና በጌዶስ ብሔረሰቦች መሀከል ቅራኔዎች ተፈጥረው ነበር ።

በተለይ የጌዶስ ሚሊሺያዎች ሰርጎገቦችን ለመደምሰስ እርዳታ ተጠይቀው ከዘመቱ ጊዜ የፈጸሙትን የበለግና ድርጊቶች በጉኚና በጌዶስ ብሔረሰቦች መሀከል ያለው ቅራኔ የባሰውን እንዲከር አድርጓል ። ብጪ ከተባለው አካባቢ መሣሪያ ሄደው ከሰማሊያ ፲ወሰዱ ሰዎች ከላይ የተጠቀሱትን ቅራኔዎች መሠረት በማድረግ ከሀገረማርያም ወረዳ ከሚኖሩ ጌዶች ጋር ግጭት አደረጉ:: ጌዶች ጋር በተለይ በሶኬ በጋሌሳና በቡሌዳ አካባቢ ከሚኖሩ ጌዶች ጋር ግጭት ይህ ግጭት በጌዴዎ አውራጃ በሚኖሩ ጌዶች ሌላ ትርጉም ተሰጥቶት ለእርዳታ በመጡበት ጊዜ ጉኚ የተባለ ሁሉ ሠርጎ ገብ ነው በማለት ሰላማዊ ሰው መግደል፣ ማሰርና ቤት ማቃጠል ጀመሩ ። ይኸው ድርጊት እየተባባሰ ለመሄዱ ባሁኑ ጊዜ የጉኚና የጌዶስ ብሔረሰቦች እንደጠላት ነው የሚተያዩት ። በተለይ የጌዶስ ሕዝባዊ ሠራዊት ጉኚ በሙሉ ሠርጎ ገብ ነው የሚል አቋም ወስደ ሰላማዊ ሰው ባይገድል ቤት ባይቃጠል በሕመም በንግድና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ ዲላ፣ ይርጋ ዓለም፣ ጨፌ፣ አዋሳና አዲስ አበባ የሚመላለሱትን ሰዎች ባይዘርፉ ባያንገላቱና ባያስሩ ኖሮ ሰርጎገቦች የሃገረማርያም ወረዳ ገበሬዎችን ባለተፈታተኑና ለማጥቃት ባልቀከሩ ነበር ። የጌዶች ከሀገረማርያም ወረዳ ልጆቻቸውን ሚስቶቻቸውንና ተንቀሳቃሽ ሀብታቸውን ይዘው ወደ ጌዶስ አውራጃ መሸሽ በጉኚዎች ዘንድ ቤተሰቦቻቸውንና ንብረታቸውን ካሸሹ በኋላ እኛን ተመልሰው ይወጋሉ የሚል ጥርጣሬ አሳደረባቸው ። በዚህ ምክንያት እኛ በሰርጎ ገቦች ላይ በምንዘምትበት ጊዜ ጌዶች መጥተው በሰዎቻችንና በንብረታችን ላይ አደጋ ያደርሳሉ በሚል ፍርሃትና ጥርጣሬ መሣሪያ ያላቸው ጉኚዎች ሀይላቸውንና ከንዳቸውን አስተባብረን በሰርጎ ገቦች ላይ ለመነሳት አልቻሉም ።

ከሀ-ጠ በተጠቀሱ ቅራኔዎች በሰርጎ ገቦች ጠብ ጫርነት ምክንያት ሁለቱም ብሔረሰቦች ባደረጉት ግጭት በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል ። ብዙ የጌዶስ ሰዎች ወደ ጌዶስ አውራጃ በሸሸት ገብተዋል ። ይሁን እንጂ በሀገረማርያም ወረዳ እስካሁን ድረስ በቀሌንቦ የ11 ገበሬ ማህበራት ገውስ ጣቢያና በገርባ የ12 ገበሬ ማህበራት ገውስ ጣቢያ የሚገኙ የጉኚና የጌዶስ ገበሬዎች እጅ ለእጅ ተያይዘው ሰርጎ ገቦን በመደምሰስ ላይ ናቸው ። የጌዶስ አውራጃና የአረር አውራጃ የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች የሕዝብ ማስፈርና የርሻ መሥሪያ ቤት ሠራተኞችና የነቁ ገበሬዎች



ሁኔታውን ለመቆጣጠርና ሁለቱ ብሔረሰቦች በመሀከላቸው የተፈጠሩትን መለስተኛ ቅራኔዎች ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አስወግደው እንደቀድሞው አንድ ላይ ለመኖር የሚችሉበትን መፍትሔ በመፈለግ ላይ ናቸው ።

በደጋው ክፍል የነቁ የጉኚ ገበሬ ማህበራት ኃይላቸውን በማስተባበር እነሱም በዛም በራሳቸውና ከመንግሥት በሚሰጣቸው ጥቂት ጥይቶች ከመንግሥት ጎን በመሰለፍና በግላቸው ከሰርጎ ገቦች ጋር በሚያደርጉት የሞት ሽረት ትግል የሰርጎ-ገቦችን ቅስም ሰብረዋል ። ሰርጎገቦች አሁን በጣም ወደኋላ አፈግፍገዋል ። የገበሬውን ሞራል እንከተበት አድርጎ የሚሰብር ነገር ቢኖር የጥይትና የመሣሪያ እጦት ነው ። ገበሬው መንግሥት በቂ ጥይት የማይሰጠን ከሆነ በራሳችን ፍራንክ እንኳን እንድንገዛ ለምን ነጋዴዎች እንዳይሸጡ ከከለከለ ራሱ ለምን አይሸጥልንም? የሚል ደረጃ ላይ ደርሷል ። አሁንም በአስቸኳይ የነቃው ገበሬ እንዲታጠቅ ካልተደረገ በደቡብ በኩል የሚካሄደው አብዮት በሰርጎ ገቦች የሚደመሰስ መሆኑ መታወቅ አለበት ።

በአሬሮ አውራጃ በአሬሮ ወረዳና በሀገረማርያም ወረዳ ሰነጉሉ በረና አውራጃ በሁሉም ወረዳዎችና በደምቢዶ አውራጃ በአጋ ሻኪሶና በዋደራ ወረዳዎች ሰርጎ-ገቦች በብዛት ተሰገሰገዋል ። በጥር ወር ውስጥ የአሬሮ ወረዳ ረዳት የሕዝብ ድርጅት ኃላፊ ጋዱ ገለገሌ ሥራን ከሌሎች 14 ሰዎች ጋር ሰርጎ-ገቦች ገድለዋል ። ሰርጎ-ገቦች የአሬሮን ከተማ በመከበባቸው የሚወጣና የሚገባ መኪና የለም ። መንገዱ በመታጠሩ እስካሁን ድረስ አስራ አምስት ሰዎች በረሃብ ሞተዋል ። ሌሎች በሞት አፋፍ የሚገኙ ተሉ ብሉ የምግብ እርዳታ ካልደረሰላቸው የሚሞቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ ። የድርቁ ማስተባበርያ ኮሚሽን ያለውን እህል በጸጥታ መናጋትና በእኝቢ እጦት ዛሬ ወይም ነገ እንሞታለን ብለው ቀናቸውን ለሚቆጥሩ ረሃብተኞች ለማድረስ አልቻለም ። በደምቢዶ አውራጃ የአጋሻኪሶ ወረዳ የሕዝብ ማስፈርና የርሻ መሥሪያ ቤት ኃላፊ በሰርጎ-ገቦች ተገድለዋል ። እንዲሁም በነቁ የገበሬ ማህበራት መሪዎች ሞተዋል በውጊያው ላይ የወረዳው የሕዝብ ድርጅት ኃላፊም ቆስሏል ። እንዲያውም ሰርጎ-ገቦቹ የወርቁ ማዕድኑን ሥፍራ ባይይዙ አይቀርም የሚል ፍርሃት አለ ። በጠቅላላው በክፍለሀገሩ ደረጃ የሰርጎ-ገቦቹ ጉዳይ አጅግ በጣም መታሰብ ያለበት ነው ።

ለሰርጎ-ገቦች ማስፋፋትና ሥር መስደድ ምክንያት የሆነው የክፍለ ሀገር በርካ ራሱና የነቃ ገበሬ በጊዜ አለመታጠቁ ነው ። አሁንም ቢሆን ሰርጎ-ገቦችን ለመደምሰስና በሶማሊያ ምድራችንን ቆርሶ ለመውሰድ ያላትን ዓላማ ለማክሸፍ ያለው አንድ መንገድ አብዮቱ የገባውን የነቃው ገበሬ ማስታጠቅ ብቻ ነው ። መታጠቅም ያለባቸው ሰዎች ሰርጎ-ገቦቹ ባሉበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች መሆን አለባቸው ። የትጥቁ ጉዳይ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚዘገይና መሣሪያ ላላቸው ሰዎች በቂ ጥይት የማይሰጥ ከሆነ ሰርጎ-ገቦች የዲሞን ክፍለ ሀገር በአጭር ጊዜ ውስጥ በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ የሚችሉ መሆናቸው መታወቅ አለበት ።

## የጓድ ታደሰ ጠገቶ በአናርኪስቶችና በአድሃሪያን መገደል

በሲዳሞ አውራጃ የአውራጃው የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች ምግብ በልተው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ከአናርኪስቶች በተከፈተባቸው ተኩስ ጓዱ ታደሰ ጠጊቶ ሲገደል የቀሩት በሕይወታቸው ርጠው ሊያመልጡ ችለዋል :: በሰፊው ሕዝብ በወሰደው የአፀፋ እርምጃ 4 አናርኪስቶች ተማሪዎችና 3 አናርኪስት መምህራን ተገድለዋል :: ሌሎችም የተጠረጠሩ አናርኪስቶች በሰፊው ሕዝብ እየታደኑ ታስረዋል :: ገበሬው ከገዱያ ጋር አያይዞ ባደረገው የመሣሪያ ፍተሻ የተቀበሩና የተደበቁ ብዙ መሣሪያዎችን አግኝተዋል :: ገበሬው ቢሮክራሲው እንቅፋት ባይሆንበት አናርኪስቶችና አድሃሪያንን በአጭር ጊዜ ውስጥ መንጥሮ ለማጥፋት ይችል ነበር :: አድሃሪ የክፍለ ሀገሩ ቢሮክራቶች በአናርኪስቶችና በአድሃሪያን ላይ ሰፊው ሕዝብ የሲዳማ አውራጃ አስተዳዳሪ አቶ ወልደአማኑኤል ዱባለና የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞችን ስም እያጥላሉ በአናርኪስቶች ላይ ለተወሰደው አብዮታዊ እርምጃ ተጠያቂዎች እነርሱ ናቸው በማለት በተራማጆች ላይ ነገር በመጠምጠም ተራማጆች ላይ አድሃሪ ዘመቻ ጀምረዋል :: የአድሃሪን ዋና ዓላማ ያለውን እንቅስቃሴ ገተው ሁኔታውን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ በተራማጆች ላይ ነገር በመጠምጠም ተራማጆች እንደ ፀረ-አብዮተኞች ተቆጥረው በደርግ ውስጥ ካሉና በክፍለሀገሩ ከተመደቡ ከአድሃሪ የደርግ አባላት ጋር በመሻረክ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ወይም ከክፍለ ሀገሩ ባሌ እንደተደረገው ለማባረርና እራሳቸው ዕረፍት ለማግኘት ነው :: ቢሮክራሲው፣ አናርኪስቶችና የኢዲዩ አባላት አንድ በመሆንና ኃይላቸውን በማስተባበር በተራማጆች ላይ በነሱም የክፍለ ሀገሩ ገበሬ በእነዚህ አድሃሪያን ላይ የማያወላውል አብዮታዊ እርምጃ ለመውሰድ ቆርጦ ተነስቷል :: ልዩ ልዩ የተጣመሙ ትርጉሞችን ገበሬው ለሚያደርጋቸው ድርጊቶች በመስጠት የገበሬውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለማረገና ለማቀዝቀዝ መላው ቢሮክራሲና ከአድሃሪያኑ ጋር እንደመዝገር የተጠበቀት ለክፍለ ሀገሩ የተመደቡት የደርግ አባሎች የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ላይ ናቸው :: በጓድ ታደሰ ጠገቶ ግድያ ምክንያት ከተገደሉ አናርኪስቶችና አድሃሪያን በስተቀር ብዙ አናርኪስቶችና አድሃሪያን ተይዘዋል :: ምርመራቸው ቀጥሏል :: ገበሬው በጓድ ታደሰ ጠጊቶ መሞት የወሰደው ቆራጥና አብዮታዊ እርምጃ ለአብዮታውያንና ለሰፊው ሕዝብ ሲሉ ሕይወታቸውን በመሰዋት ላይ ለሚገኙ ሁሉ ኩራትና ድፍረት የሚሰጥ ነው :: አብዮቱ ከመከላከል ደረጃ ወደ አጥቂነት መተላለፉን የሚያመለክት ጥሩ ማስረጃ ነው :: ገበሬውንና ተራማጆችን ለመወንጀልና ለመደምሰስ የተቀነባበረው ፀረ-አብዮት ሤራ በክፍለ ሀገሩ ደረጃ ብቻ የተወሰነ ስላልሆነና ዋና ፀረ-አብዮት ሤራዎች መነሻ አዲስ አበባ ስለሆነች ከክፍለሀገሩ ቢሮክራሲ ጋር ግንኙነት ያላቸው ከፍተኛ ቢሮክራቶች በአዲስ አበባ የሚገኙ ስለሆነ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ይህንኑ ሀቅ ተገንዝቦ የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ ያስፈልጋል ::



## የክፍለ-ሀገሩ ቢሮክራሲ

በጀኔራል ደስታ ገመዳና በኮሎኔል በለጠ በላይነህ የሚመራው ቢሮክራሲ ለሥራ ከፍተኛ እንቅፋት ሆኗል :: እነዚሁ ቀንደኛ ቢሮክራቶች በአስተዳደር ውስጥ የሚገኙትን አድሃሪዎችን የፖሊሱን ኃይልና በየከተማዎች ውስጥ የተሰገሰጉትን ከገጠር የሸሹ የመሬት ከበርቴዎችና በየድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ አናርኪስቶችንና አድሃሪያንን ለፀረ-አብዮት ሤራ በሚገባ አቀነባብረዋል :: የሰርጎ-ገቦች ሁኔታም እንዲባባስና በአጭር እንዳይቆ ልዩ ልዩ ምክንያቶችን እየፈጠሩ በወቅቱ በሰርጎ-ገቦች ላይ እርምጃ እንዳይወሰድ ያደረጉ እነዚሁ ቢሮክራቶች ናቸው :: የሲዳማና የጌዴኦ አውራጃ ሕዝቦች የእነዚህን ከፍተኛ ባለሥልጣን አድሃሪነትና ፀረ-አብዮት አቋም በመገንዘብ በእነዚሁ በተጠቀሱ ሁለት አውራጃዎች ውስጥ የሚኖሩ ገበሬዎች እነዚሁን አድሃሪ ቢሮክራቶች በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዋል :: ገበሬዎች ምንም አእምሮ እንደሌላቸውና እንደ እንስሳት በመቁጠር የእነዚህኑ ቢሮክራቶች አለመነሳት ከሚደግፉ ወገኖች ተቃውሞውን ገበሬው በሰላማዊ ሰልፍ እንዲገልጽ የገፋፉትና የቀሰቀሱት የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ሠራተኞችና ሌሎች ተራማጅ ሠራተኞች ናቸው እንጂ ገበሬው በራሱ ነገሩ ገብቶት አይደለም የሚል ድምፅ ይሰማል :: በአስተዳደር በኩል በክፍለ ሀገሩ ከሚገኙ የሰድስት አውራጃ አስተዳዳሪዎች ውስጥ ሁለት አስተዳዳሪዎች ብቻ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት ያተረፉ ሲሆን የደምደም፣ የወላይታ፣ የነገሌ ቦረናና የጌዴኦ አውራጃ አስተዳዳሪዎች የጀኔራል ደስታ ገመዳ ተጥሳዎችና ጥኑሮች ናቸው :: በክፍለ ሀገሩ ከሚገኙ ወረዳዎችና ፖሊስ ጣቢያዎችና እነዚሁ አድሃሪ ቢሮክራቶች ብዙ ደጋፊ አስተዳዳሪዎችና አዛዦች አሉዋቸው :: አብዮቱ በውጭና አድሃሪ ሀይሎች ተወጥሮ በተያዘበት ባሁኑ ወቅት ቢሮክራሲው አድሃሪ ኃይሎችን በማስተባበርና ሰዎና ወርቅ በማድረግ አብዮቱን ለመቀልበስ ከፍተኛ አሻጥር በመፈጸም ላይ ይገኛል :: ተራማጅ አስተዳዳሪዎች የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞችና የነቁ የገበሬ መሪዎች ተበሳጭተው እንዲሸፍቱ ወይም ወንጀል ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ ባላቸው ሙሉ የቢሮክራሲና የገንዘብ ኃይል በመጠቀም ላይ ናቸው ::

ለምሳሌ ጓሀል በደምደም አውራጃ የሶላም ወረዳ አስተዳዳሪ የነበረ አቶ ሀብተ ገብርኤል ሸከን በማበባዉት ላም ባለቤቶት ኩቦት ለቆማ እንደሚባለው ያልፈጸሙትንና ያላደረጉትን እንደፈጸሙና እንዳደረጉ በማስመሰል ደስታ ገመዳ በሠራባቸው ከፍተኛ አሻጥር ሊሸፍቱ ችለዋል :: ደስታ ገመዳ ሆነ ብሎ የያዘው የአስተዳደር ዘይቤ ተራማጅ አስተዳዳሪዎችን ማናደድና አብድ እንዲሆን ማድረግ ነው :: ባሁኑ ጊዜ ደስታ ገመዳ ከክፍለ ሀገሩ አውራጃዎች የአራት አውራጃ አስተዳዳሪዎች ደጋፊዎቹና ቡችሎቹ መሆኑን በመረዳት የሲዳሞ አውራጃ አስተዳዳሪ አቶ ወልደአማኑኤል ዱባለንና የአረር አውራጃ አስተዳዳሪ ሻምበል መብአጽዮን አሌን ለማስነሳት ነው ጥረቱ :: ጥቂት ተራማጅ የወረዳ

እስተዳዳሪዎች እንዲነሱና የራሱን ጋሻ ጃግሬዎች ለመተካት ነው ምኞቱና ፍላጎቱ ። ቢሮክራሲው ባሁኑ ጊዜ በሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች በተራማጅ አስተዳዳሪዎችና ግለሰቦች ላይ ከፍተኛ የወንጀልና የጎዶያ ሥራ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል ።

12.69

## የጓድ እሸቱ አራርሶ መቁሰል የከፍለ ሀገሩ ቢሮክራሲ፣ የኢህአፓና የኢዲዩ ሥራ ውጤት

ጓድ እሸቱ አራርሶ የካቲት 12/6/69 ዓ.ም. ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ እራቱን ለመብላት አለማየሁ ሆቴል ሄዶ ሳለ በኢህአፓ በኢዲዩና በከፍተኛ የከፍለሀገሩ ቢሮክራቶች ቅጥረኛ ፋሽስት ነፍሰ ገዳዮች በስድስት ጥይቶች መቁሰሉ የሚታወስ ነው ። ጓድ እሸቱ አራርሶ እንደማገኘውም ጠቀኛ አብዮታዊ በየካቲት ወር በ1966 ዓ.ም. አብዮቱ ከመፈንዳቱ አስቀድሞ ከአድሃሪ የመሬት ከበርቴዎች ጋር ብዙ ትግል ያደረገ ነበር ። አብዮቱ ከፈነዳም በኋላ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ከመቋቋሙ አስቀድሞ በሰፊው ሕዝብ ወገን በመሆኑ አያሌ ተቃውሞ ደርሶበታል ። ብዙ ጠላቶችንም አፍርቷል ።

የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አብዮቱ ትክክለኛውን ፈር እንዲይዝ ከአድሃሪያን ጋር ብዙ ትንቅንቅ አድርጓል ። በሰፊው ጭቁን ሕዝብ ከባርነት ለማውጣት ባደረጋቸው ትግል በሲዳሞ ክ/ሀገር ከሚገኙ ቢሮክራቶች ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል ። ገበሬው ነቀተ አድሃሪ ቢሮክራቶች ይነሱለን ብሎ በመጠየቅ ገበሬውን ያነሳሳው እሸቱ ነው የሚል ክስ ከአድሃሪያን ቀርቦበታል ። በጓድ እሸቱ ላይ የቀረበው የጎዶያ ወንጀል ከነዚሁ እንዲነሱ ከተጠየቁት ቢሮክራቶች አናርኪስቶችና የኢዲዩ አባሎች የመነጨ ፀረ-አብዮት ሥራ ነው ።ምክንያቱም በቀልባሽ የደርግ አባላት ላይ እርምጃ ከተወሰደና ጄኔራል ደበታ ገመዳ የሲዳሞ ክፍለሀገር ዋና አስተዳዳሪና ኮሎኔል በለጠ በላይ ነህ በገበሬውና በቀበሌ ማህበራት እንዲነሱ ከተጠየቁ ወዲያ እነዚሁ ቢሮክራቶች ተራማጆችን ለመደምሰስ ፀረ-አብዮት ሥራ ለመጠንሰስ ወዲያና ወዲህ ውር ውር ማለት ጀምረው ነበር ።

## የከፍለ ሀገሩ ገበሬ ስቃይና ችግር

በከፍለ ሀገሩ ከሚገኙ ገበሬዎች የሲዳማና የጌዴኦ አውራጃ በተለይ በኩል የሚፈለገውን ያህል ታግሏል ለማለት ባይቻልም ከቀሩት አውራጃዎች በጣም ለቀው ይገኛሉ ። በአውራጃዎቻቸው ውስጥ የሚገኙትን አድሃሪያንና አናርኪስቶችን ለማጥፋት ኃይል አሏቸው በጀምጀም አውራጃ፣ በነገሌ ቦረናና በአረሮ አውራጃዎች ውስጥ የሚገኙ ገበሬዎች በተጥቀ በኩል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ ። የተጥቀም ችግር እያለ የሰርጎ ገቦች ጉዳይ



እጅግ በጣም ከባድ ችግር ውስጥ ጥለውታል ። ከሰርጎ ገቦች ጋር የሞት ሽረት ትግል በማድረግ ላይ ይገኛሉ ። ዳሩ ግን ስላልታጠቁና በቢሮክራሲ በኩል ከባድ ሻጥር ስለ ሚሠራባቸው ሰርጎ-ገቦችን ሊቋቋሟቸው አልቻሉም ። ገበሬዎቹ ከሰርጎ-ገቦቹ ጋር በሚያደርጉት ትግል እያለቁና ንብረታቸው እየወደመባቸው ነው ።

የሲዳማና የጌዴኦ አውራጃ ገበሬዎች እንደ ጀኔራል ደበታ ገመዳና ኮሌኔል በለጠ በላይ ነህ ያሉ የቢሮክራሲው ቁንጮ የሆኑ ባለሥልጣናት እንዲነሱላቸው ጠይቀዋል ። በጸጥታ ምክንያት የአረሮና የነገሌ ቦረና አውራጃ ገበሬ ተወካዮች ለበላይ ባለሥልጣናት አቤቱታ ለማቅረብ ባይችሉም የቀሩት የአራት አውራጃ ገበሬዎች ተወካዮች እስከ አዲስ አበባ ድረስ ሄደው እነዚሁ ቁንደኛ ቢሮክራቶች እንዲነሱላቸው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለሥልጣናት አመልክተዋል ። ቢሮክራሲውና የአብዮቱ ጠላቶች ናቸው እንጂ የገበሬውን እንቅስቃሴ ለመገታት የሚሞክሩት ገበሬው ቢሮክራሲውን ለመደምሰስ ጥሩ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል ።

በጣም ከፍተኛ ችግር በሰድስቱ አውራጃዎች ውስጥ የሚገኙትን ገበሬዎች እርስ በርሳቸው ለማያያዝ አልተቻለም ። ትግላቸውን ለማቀነባበር በከፍለ ሀገሩ ባለው ሁኔታ ምክንያት አልተቻለም ። በሌላ አነጋገር ደግሞ በጌዴኦና በጉጂ ብሔረሰቦች፣ በሲዳማና በጉጂ ብሔረሰቦችና በጉጂና በቦረና ብሔረሰቦች መካከል ባሉት መሰስተኛ ቅራኔዎች ምክንያት የእነዚሁ ብሔረሰቦች ገበሬዎች ለብ ለብ ተገናኝተው ኃይላቸውን ሰብስበው አንድ ሊያደርጉ አልቻሉም ። የከፍለሀገሩ ገበሬዎች አንድ ባለመሆናቸውና መሰስተኛ ቅራኔዎች በመሀከላቸው ስለሚገኙ ሕብረታቸውና አንድነታቸው ለመበቅ አልቻለም ። ስለዚህ ሰርጎ-ገቦችና ፀረ-አብዮት ኃይሎች ፋታና ጊዜ አግኝተው በገበሬዎቹ መሀል የሚታዩ ደካማ ጎኖችን እያዩ ለራሳቸው አመቺ ሁኔታን ከመፍጠራቸው አስቀድሞ ገበሬዎች እርስ በርሳቸው እንዲያያዙና እንዲተዋወቁ ገበሬዎች በከፍለ ሀገሩ ደረጃና በአገር ደረጃ አጠቃላይ ማህበራትን እንዲያቋቁሙ መንግሥት በአስቸኳይ አቋም እንዲያወጣ ከፍተኛ ጥረት አብዮታዊ ኃይሎች ቢያደርጉ ጥሩ ነው ።

## ስለ ሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት

የከፍለ ሀገሩ ሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ሠራተኞች ባሁኑ ጊዜ የአድሃሪያን የአናርኪስቶችና የቢሮክራቶች ዐይን ያረፈባቸው ደመኛ ጠላት ሆነዋል ። የአድሃሪያን ምኞትና ፍላጎት ቢቻላቸው የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞችን ለመጨረስ ነው ። ለዚሁ ዓላማቸው የጓድ እሸቱ አራርሶ በስድስት ጥይቶች መቁሰልና የጓድ ታደሰ ጠጊቻ መገደል ጥሩ ማስረጃ ነው ።

በጀምጀምና በነገሌ ቦረናና በአረሮ አውራጃዎች ሰርጎ-ገቦች በብዛት በተሰገሰገቡትና ፀረ-አብዮት ድርጊታቸውን ባፋፋመባቸው ሥፍራዎች የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች

እንደተለመደው ሥራቸውን በሚገባ ሊያከናውኑ አልቻሉም ። ምክንያቱም ስርገ ገቦች በመጀመሪያ ደረጃ ሊገሉ የሚፈልጉት የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች በመሆኑ ነው ። በጸጥታ መበላሸት ምክንያት ሥራው በጣም ተበድሏል ። ሕዝቡ ራሱ የጸጥታው ሁኔታ ወፈናፈኛ ባባጣና ገራ ባጋባቸው ባሁኑ ጊዜ የሚሰጠውን ትምህርት ሊቀበል አይችልም ። ሕዝቡ የሚጠይቀው መሣሪያና ጥይት ነው ። የተራበው ምግብ ነው የሚጠይቀው ። የጸጥታ መናጋት ሁኔታ የማደራጀቱ ሥራ አደናቅፏል ።

ሌላው የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች ችግር የወር ደሞዛቸው በጊዜ አይደርሳቸውም ። ወሩ ካለፈ ብዙ ጊዜ ቆይቶ ነው ደመወዝ የሚከፈላቸው ። የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ አግኝተው የማያውቁ አውራጃዎችና ወረዳዎች አሉ ። ሠራተኞች በጊዜ ደመወዛቸውን እንዲያገኙ ገንዘብ ከዋናው ጽ/ቤት በጊዜ ቢላክ መልካም ነው ።

በአንዳንድ ሥፍራዎች ቢሮክራሲው የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞችን ለማንቀሳቀስ አልቻለም ። እንደ ማስረጃ የክፍለሀገር የጀምጀምና የነገሌ ቦረና ሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች ከቢሮክራሲው በኩል የሚደረግባቸው ተጽእኖ እንደዋና ማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል ።

## የከተማ ቀበሌ ማህበራት

የከተማ ቀበሌ ማህበራት ሙሉ ለሙሉ እምነት በእነርሱ ላይ ለማድረግ ባይቻልም ከቀላ ኀይል ደህና ናቸው ። አናርኪስቶችና አድሃሪያን የቀበሌ ማህበራት ከፊኛ በመፈታቱና አንዳንድ መሪዎችን በማወናበድ ላይ ይገኛሉ ። አናርኪስቶችና አድሃሪያኑ አብዮቱን ለመቀልበስ ይፍጨረጨራሉ እንጂ በተራማጆች ጥረት ቀበሌዎች ጥሩ በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው ። በተራማጆች ላይ የሚደረገው ግድያና የግድያ ሤራዎች ለቀበሌዎቹም ጥሩ የመነቃቂያ ትምህርት ሆነዋል ። ጊዜ አሸቶ በጡታ በማገስቱና በቀበሌ ቆናት የከተማ ቀበሌ መሪዎች የደርግ አባላት ስለግድያው ሙከራ ከሰጡት አስተያየት ግ ግ እንደሆነ ለማወቅና ለመገንዘብ ችለዋል ። በቁጣሪ ገበሬው በክፍለ ሀገር ደረጃ ከተደራጀ የከተማ ቀበሌ ማህበራት ከአድሃሪና ከአናርኪስቶች ሤራ ነፃ የሚሆኑበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ።

የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት
የፍልስፍና ማስፋፊያና ማስታወቂያ ኮሚቴ
የጋሞ ጎፋ ክፍለ ሀገር ወርሀዊ ሪፖርት
የካቲት 1969

የህዳር 23 ቀን 1969 ዓ.ም. ሪፖርታችን የጋሞ ጎፋን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሰሻለዊ፣ ድርጅታዊ፣ ትጥቃዊ ቴፕሮክዊ /አገደድርቀ ያለ/ ሁኔታዎችን በየአውራጃው ተዳሷል ። ያሁኑ ሪፖርታችን በፖለቲካ ላይ ያተኩረ ይሆናል ።

## ጋሞ ጎፋ

ጋሞ ጎፋ በምሥራቅ፣ በሰሜን ምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ ከሲዳሞ በምዕራብ በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ከከፋ በሰሜን ከከፋና በደቡብ ከኬኒያ ተዋስናለች ።

በዚህ ክፍለ ሀገር ከሰባት ብሄረሰቦች ይገኛሉ ። እነሱም 1/ ወላይታ—ነክ ክፍሎች፡- ለምሳሌ ጋሞ 2/ የኦሮሞ ብሔረሰብ ክፍሎች /ከንቦ፣ ጉጂ፣ ዱራሻ፣ አርቦሬ/ 3/ የገለብ ብሔረሰብ 4/ የፀመር ብሔረሰብ 5/ የሙርሲ ብሔረሰብ 6/ የኮይራ ብሔረሰብ 7/ የማሌ ብሔረሰብ 8/ የወረዛ ብሔረሰብ ...ወዘተ ናቸው ።

## የመደብ ትግል

የአርሶ አደር መደብና ህዝብ ተራማጆች ባንድ ወገን የመሬት ከበርቴዎች ታላላቅ ነጋዴዎችን፣ የቢሮ ከበርቴዎችና የኢምፔሪያሊስት ምንደኞች በሌላው ወገን በመሆን በመካከላቸው የከረረ መደባዊ የሞትና ሽረት ትግል ይካሄዳል ።

በገጠሩ የአርሶ አደሩ አብዮታዊ ትግል በመፋፋሙ የመሬት ከበርቴው መደብ ወደከተማው ሸሽቶ መሽጎ በቢሮ ከበርቴ ባለሥልጣኖች የበላይ አቀነባባሪነት እና በአናርኪስቶች ፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ ፀረ አብዮት ስራ ይሸርባሉ ። በተግባርም ከማሳየት አልተቆጠቡም ።

1. እስከጥር 1969 ዓ.ም.

ጭቁና ብዝበዛ ባለበት ሁሉ ተፃራሪ መደቦች አሉና ከነሱም በዛም መደባዊ ትግል ይካሄዳል ። በጋሞ ጎፋ ክፍለ ሀገርም መደቦች በኅብረተሰቡ ከተፈጠሩ ጀምሮ መደባዊ ትግሉ በመካሄዱ ላይ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ። የየካቲት 66 ዓ.ም. የአብዮት ፍንዳታ ለነበረው የአብዮት ወገን ኃይል (impetus) በመስጠት ትግሉ እጅግ እንዲፋፋም አድርጓታል ።

ታሪካዊ የኅብረተሰብ ዕድገት ያመጣው የትግሉ ሂደት አድሀሪያንን ክፉኛ ስላስፈራቸው የመደብ ጥቅማቸውን ለማስከበር፣ መልሰው በእጃቸው ለማስገባት በትምህርት ቤት አካባቢ ልጆቻቸው "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲጠይቁ በማድረግ፣ በገጠር አካባቢ ያሉ ሥልጣንን መከታ በማድረግ አብዮታውያን አቋሞችን ሲያጠምሙና በለዩ ለዩ መልክ ሲያናኩትኑ፣ እስከአፍ ጠመ የታጠቁት ጥቂት አድሀሪያን ደግሞ በአብዮቱ ላይ በማመጽ ጫካ ገብተዋል ።

ጭቁና ብዝበዛ መደባዊ ትግሉን ያስተማሯቸው የክፍለ ሀገሩ ሕዝቦች እስካሁን ድረስ የመደብ ጠላቶቻቸውን ቅስም እየሰበረ በአብዮቱ አንፃር የተቻለውን ያህል ወደፊት እየመጣ ነበር ።

ሀ. በክፍለ ሀገሩ ላይ የሚደረግ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ

በአዲስ አበባ የሚገኙ ከበሳይ የአድሀሪ መደብ አባሎችና አናርኪስት ልጆቻቸው በጋሞ ጎፋ "የጐሣ ልዩነት ትግል፣ የመጤ ጥላቻ አንቀሳቃሽ፣ የባሪያ አመፅ፣ የደርግ ፋሽዝም መናኸር፣ የጠባብ ብሔረተኝነት አብዮት የሚካሄድበት ነው" የሚል ርካሽና አድሀሪ ፕሮፓጋንዳ በተራ ወሬ ከአዲስ አበባ እንሰማ ነበር ።

ለ. በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ላይ የሚደረግ ያፕሮፓጋንዳ ዘመቻ

1. በወዝ አደር አካባቢ— የፋሽስት ቡችሎች የባንዳ ምሁራን ጽ/ቤት ነው ። የደርግን ዕድሜ ለማራዘም እና ንቀን ሥልጣን ለማሳጣት የተገዙ ቅጥር ማርክሲስቶች ናቸው ። ጠባብ ብሔረኞች



የተሰበሰቡበት መሥሪያ ቤት ነው ። የፊዳ ገንዘብ ዓይናቸውን ያሳወረባቸው የሥልጣን አድርባይ ፀረ ወዝ አደር ድርጅት ፣ ፀረ ኢህአፓ ድርጅት ነው ። ...ወዘተ

2. በአርሶ አደር አካባቢ— የፋሽስት ቡችሎች የባንዳ ምሁራን ጽ/ቤት ነው ። ጋሞ ጎፋን የሸጡ፣ የደርግን ዕድሜ ለማራዘም የተገዙ ቅጥር ማርክሲስቶች ናቸው ። ፊዳስቶች ። የፊዳ ገንዘብ ዓይናቸውን ያሳወረባቸው የሥልጣን አድርባዮች ናቸው ። ...ወዘተ

3. በትምህርት ቤት አካባቢ— የፋሽስት ቡችሎች የባንዳ ምሁራን ጽ/ቤት ነው ። ትምህርት ቤት ዘግተን እንዳንታገል የሚያደርጉ የተማሪን አንድነት የሚከፋፍሉ ፀረ ተማሪ አንድነት ናቸው ። ፀረ ሳብአደር የደርግ ዕድሜ ለማራዘም የተገዙ ቅጥር ማርክሲስቶች፣ ፊዳስቶች፣ የፊዳ ገንዘብ ያሳወራቸው የሥልጣን አድርባዮች፣ የባሪያ አመፅ መሪዎች፣ ጠባብ ብሔረኞች ፀረ ኢህአፓ ናቸው ። ...ወዘተ

4. በተራማጅ የመንግሥት ሠራተኞች አካባቢ— መጤን አይወዱም ። የጐሣ ልዩነት ያደርጋሉ ። የደርግ ቀኝ እጅ ናቸው ...ወዘተ እያሉ ይሰብካሉ ።

ከጥር 1969 ዓ.ም. ወዲህ

ከጥር አጋማሽ ወዲህ በጋሞ ጎፋ የፖለቲካ ሁኔታ አደገኛ ምናልባትም የቀለበሳ ምልክቶች እየታዩበት መጥተዋል ። በወሬ ከአዲስ አበባ አድሀሪያች አካባቢ ይነፍሱ የነበሩት ርካሽና አድሀሪ መፈክሮች ለምሳሌ "ዘረኝነት፣ የጐሣ ልዩነት፣ ጠባብ ብሔረተኝነት በጋሞ ጎፋ ነግሷል" የሚሉ በጋፋ አደባባይ ወጥተዋል ። ቅስቀሳም እየተደረገባቸው ነው ። የአሥራት አርምኛም በሁለት የተለያዩ ሥፍራዎች /አርባምንጭና ጊዶሌ/ ተወስደዋል ።

የዚህ ውጤት እንደታየው የኢዲዮ፣ የኢህአፓና የቢሮ ከበርቴዎችን ሞራል ከፍ ሲያደርግና ነበረታቸውን የበለጠ ሲያጠናክር በተራማጁ ወገን ሞራል ላይ ግን ውድቀት ሊያደርስ ነው ። አድሀሪ ድርጅቶችም ሀቀኛ ተራማጆችን በዝርዝር ማጥናት ይዘዋል ። ባጭሩ እና ጋ አብዮቱ የተቃራኒ ከመጠነኛ አጥቂነት ወደ ተከላካይነት ወርደአል ለማለት ይቻላል ።

ማጠቃለያ

በጨበጥ የጋሞ ጎፋ ሁኔታ "ዘረኝነት" የጎሣ ልዩነት፣ ጠባብ ብሔረተኝነት ...ወዘተ" የሚሉ መፈክሮች ፀረ አብዮት መፈክሮች ናቸው ። የሌሉ ነገሮች ናቸው ።

ዘረኝነት በማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል አለ ብለን አናምንም ። ጎሣም ቢሆን በጥንታዊ የጋርዮሽ ዘመን ብቻ የሚገኝ ስለሆነ በፊውዳ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ሊኖር ስለማይችል መፈክሩ ፍጹም ቅዠት ነው ።

ጭቁና ብዝበዛ ባለበት መደቦች አሉ ። በአንድ ጨቋኝ በዝባዥ ሥርዓተ ማኅበር ብሔረሰቦች ካሉ ሁሉም እኩል ሊሆኑ አይችሉም ። ስለዚህም በዚህ ዓይነት ሥርዓተ ማኅበር የብሔር ተምክህተኝነትና ጠባብ ብሔረተኝነት ያለጥርጥር ይኖራል ። የኢትዮጵያ ሁኔታም ከዚህ ለዩ አይሆንም ። አንዱንም መደገፍ አድሀሪነት ስለሆነ ሀቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስት ምሁራን ሰፊውን ጭቁን ሕዝቦች እያስተባበሩ መታገል ግዴታቸው ነው ።

ጋሞ ጎፋ ብሔረሰቦች የሚገኙበት እንጂ የአንድ ብሔረሰብ ክፍለ ሀገር አይደለም ። በብሔረሰቦችም መካከል የሚታረቅ (non antagonistic) ቅራኔ የለም ማለት አይደለም ። በሌላ በኩልም በየቦታውና በየወቅቱ በአብዮቱ ደጋፊ መደቦች በፍሎች የሚወሰደው እርምጃ ሁሉ ሁልጊዜ ትክክል ወይም ፍጹም ነው ማለት አይደለም ። በአርሶ አደሮች አካባቢ ባለሠላሣ ብር የእህል ወፍጮ አክስዮን (So-called mative) "አድሀሪያች" ተብለው የታሠሩበት ጊዜ ነበር ። በትዕግሥት ሊታለፍ የሚቻለውን በስሕተት ለአብዮቱ ታማኝ የሆኑ መሰሎቻቸው ጭቁን የመደብ ጓዶቻቸውን የገረፉበት፣ የገደሉበት ወይም ገለሌ ሰቀ በሌ የተዋጉበት ቦታ ወቅት አልነበረም ማለት አይደለም ። አናርኪስቶችና



አስመሳይ ተራማጆች ገጠርንና ከተማን ያጣሉበት ወቅት እንዳለም የማይካድ ነው ። ሆኖም እነዚህ ሁኔታዎችና እነኝ ስሕተቶች በክፍለ ሀገሩ በመደብ አንፃር የሚደረገውን ከፍተኛ አብዮት በመሸፋፈን ሊያፍኑ አይገባም፣ አይችሉም ። በተጨማሪም ክፍለ ሀገሩ በማንኛውም እድገ በጣም ወደኋላ የቀረ መሆኑ እየታወቀ ሊረዱት የሚችሉት ከሌሎች ክፍላተ ሀገር ወይም ወዳጅ አገር የሚመጡ ምሁራን ባለልዩ ልዩ ሙያዎች መሆኑ በግልጽ እየታየ ክፍለ ሀገሩ ጭቁናና ብዝበዛን በመጥላት በመደብ አንፃር የሚያደርገውን በመደብ አንፃር ሳይሆን በስመ መጤ ማንገም ይጠላል ተብሎ የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ በእውነት ከፀረ ጭቁን መደብ ወገን ብቻ ነው ።

አንገብጋቢ ጥያቄ

ጋሞ ጎፋ ከአድሶ አዘር ቀኝ አገር ከኬኒያ ጋር በደቡብ ተዋስናለች ። በጋርዱላ አውራጃ በጉማይዴ በኮንሶ አካባቢ የሶማሌ ሰርጎ ገብ ምልክቶች ታይተዋል የሚል ጠቅላይ የአስተዳደር ሪፖርት አለ ። በዚሁ አካባቢ ከኦሞ ወንዝ ማዶ በኩል ኮንታ አውራጃ የአድሀሪያን መሸሸግ ይነገራል ።/ስለዚህ ወደፊት የተጠናውን ሪፖርት በዝርዝር እናቀርባለን/

የክፍለ ሀገሩ አንገብጋቢ ጥያቄ "ትጥቅ" ነው ። የክፍለ ሀገሩ ሁኔታዎች ተመዝነው መጠይቁ በአስቸኳይ ቢሟላ ለአብዮቱ ዋስትና ይበጃል ።

አስተያየት

በጨበጥ የጋሞ ጎፋ ሁኔታ የወህኒ ቤት በሮች ለተራማጆች ክፍት የሆኑ ይመስላል ። በአርባምንጭ እርሻ ልማት አካባቢ 16 ሀቀኛ ተራማጅ ወዝ አደርችና ተማሪዎች በአናርኪስቶች ሴራና ጥቆማ ካሁን በፊት ባንዳ ፋሽስት ደርጊት በመባል የታሠሩትና የተደበደቡት [illegible] አወህኒ ቤት ገብተዋል ። ሦስቱም በጥብቅ በመፈለግ ላይ ናቸው ። በጋርዱላ አውራጃ በጊዶሌ ከተማም ተራማጅ ተማሪዎችና አስተማሪዎች አናርኪስት ተማሪዎችን አስተማሪዎችን ስላጋለጡ ይህ አድራጎት ዘረኝነት የጎሣ ልዩነት ተብሎ የአጸፋ እርምጃ(counter measure) እየተወሰደ በዙ ሀቀኛ ተራማጆች መታሠር ጀምረዋል ። የክፍለ ሀገሩ የሕዝብ

ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ከመቸውም ይበልጥ ፈተና ከፊቱ ተደቅኖበታል ። የክፍለ ሀገሩ አስተዳደርም ለሥራው አንደኛው መፈናፈኛ ወደማጣት አካባቢ ይመስላል ።

## ከፋ ጥናታዊ ሪፖርት

ሠፊው ጭቁን ህዝብ ሲረገጥና ሲበዘበዝ የነበረበት የከፊል ፊውዳልና ከፊል ከበርቴአዊ ሥርዓት ከሥሩ ተብርብሮ እንዲገረሰስ ጭቁኑ ወዝ አደርና አርሶ አደር ከፍተኛ መስዋዕትነትን አድርጓል ። በከተማ ወዝአደሩ የለለውን የሥራ ዋስትና መብት በመንጠቅ ለአብዮቱ መጀመር ዋና መንስኤ ሆኗል ። በገጠር ያለው ሠፊው አርሶ አደር በተጋጋለ ሁኔታ ለመብቱና ሀብቱ ለሆነው መሬት ከጥቂት ከበርቴዎች ጋር ከባድ ትንቅንቅ አድርጓል በማድረግም ላይ ነው ።

የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ሁኔታ በየአቅጣጫው ከተመለከትን በመሬት ሥሪት በኩል ልዩነቶች መኖራቸው የታወቀ ነው ። በሰሜን ያለው የመሬት ሥሪት ከደቡቡ የተለየ ነበር፤ ለዚህም መሬት እንደ ቀደሞ የጋርዮሽ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ነው ባይባልም ተመሳሳይነት እንዳለው ይነገራል ።

የደቡቡ ቀደም ሲል እንደሚታወቀው ያለው መሬት በጥቂት ባላባቶች እጅ ሲያዝ በመሬት ላይ ላቡን የሚያፈሰው ግን ብዙሀኑ ጭሰኛ ነበር ። በጉልበቱ ያመረተውን ምርት የመሬት ጌታ በመባሉ ብቻ ለባላባቱ ያለምንም ውጤት ያስረክብ ነበር ። በዚህ ዓይነት ይበዘበዝና ይጨቆን የነበረው ጭሰኛ ጭቆናውን ስለመረረው ከወዝ አደሩ ጋር በመተባበር ጭቁኑ መለዮ ለባሽ መሪነት በየካቲት 66 ዓ.ም. አብዮቱ ጀምሮ በአራቱም ማዕዘናት ማስተጋባት ቀጠለ ።

ጭቁኑ አርሶ አደሮች የተበዘበዙበትና አብዮቱን ከገፉት ከደቡብ ክፍላተ ሀገራት አንዱ ከፋ ሲሆን ይህ ክፍለ ሀገር ቡና አብቃይ በመሆኑ ጥቂት ባላባቶች ብዙሃኑን ገበሬ ሲበዘብዙት ኖረዋል ። በተለይም ይህ ክፍለ ሀገር አብዮቱ በማራመዱ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከቱ ጭቁኑ አርሶ አደር ላይ የነበረውን ጭቆና ምን ያህል ከባድ እንደነበር ያሳያል ።

ከፋ ክፍለ ሀገር 6 /ስድስት አውራጃዎች ሲኖሩት በስድስቱ አውራጃዎች 38/ ሰላሳ ስምንት/ ወረዳዎች ይገኛሉ ። የገጠሩን አካባቢ ያየነው እንደሆነ በ1906 የገበሬ ማህበራት /ቁጥሩ በመጨመር ላይ ነው/ የተደራጀው አርሶ አደር አብዮቱን ከአድሃሪዎች ለመከላከል 15,740 የጥበቃ ጓድ ሲኖሩት በትጥቁ በኩል ይህ ነው ባይባልም ከአድሃሪያን የተረከቡ መሳሪያዎች በመኖራቸው ከጠቅላላው የጥበቃ ጓድ አባሎች ሃያ በመቶ /20%/ ታጥቋል ለማለት ይቻላል ። አርሶ አደሩ እስከሁን ድረስ ባጠቃላይ በወረዳ ሲሆን ጅማ አውራጃ ብቻ በአውራጃ ደረጃ ተደራጅቷል ።

አርሶ አደሩን የመደራጀት ጥረት ለማገዝ እንዲረዳ ታስቦ በታህሣሥ 68 ዓ.ም. የታወጀው የገበሬዎች ማህበራት ማጠናከሪያ አዋጅ የአርሶ አደሩን አቋም በሚገባ አጠንክሮታል ። በዚሁ መሠረት አርሶ አደሮች እራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር በየማህበራቱ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ በመምረጥ የደህንነት ጥበቃ ጓድ በማደራጀት አብዮታቸውን እየጠበቁና በሥራቸው በኩል ኅብረት በመሥራት የምርታቸውን ውጤት ከፍ በማድረግ ላይ ናቸው ። አርሶ አደሩ በአሁኑ ጊዜ በተለይም በጅማ አውራጃ የሚገኙት አርሶ — አደሮች የህብረት እርሻቸውን ከመቸውም ይበልጥ በማስፋፋት ላይ መሆናቸው ታውቋል ።

ጭቆኑ ገበሬ የመሬት ባለቤት ከሆነ ጀምሮ ጥቅሞቹ የተነካባቸው አድሀሪያን የኢ.ዲ.ህና የኢ.ህ.አ.ፓ. አባሎች ገበሬውን ለማባባትና በአብዮቱ እንዲያምፅ ቀደም ሲል መፍጨርጨራቸው ታውቋል ። በተለይም በጊሚራ፣ በከፋና በኩሉ ኮንታ አውራጃዎች በየጫካው በመመሸግ አብዮቱን ለመቀልበስ ይፍጨረጨሩ የነበሩ የኢ.ዲ.ህ. ርዝራዦች የገበሬው የጥበቃ ጓድ ከፀጥታ አስከባሪዎች ጋር በመተባበር አንበርክኳቸዋል ። የገበሬው ምርት እንዲቀንስና ከርዝራዡ ጋር መቃቃር እንዲፈጥር የኢ.ሕ.አ.ፓና የኢ.ዲ.ህ. ቡድን አባሎች በመተባበር መንግሥቱ ያወጣቸውን አዋጆች በመቃወምና በአስፈጻሚዎች ላይ ተፅዕኖ በማድረግ በኩል ቀደም ሲል በከፋ አውራጃ የዘማቾች መቃጠልና በሌሎች በታዎች በቢሮክራሲው ተፅዕኖ ገበሬዎች በመንገላታቸው በአሁኑ ጊዜ አርሶ አደሩ ይህንን ሁሉ ለማስወገድ ይበልጥ በመገስገስ ላይ ነው ። በተለይ የኢ.ዲ.ህና የኢ.ሕ.አ.ፓን የተቀነባበረ አሻጥር በመቋቋም በኩሉ ኮንታ አውራጃ ተራማጅ በመሆ ሰለ በመሬት ከበርቴዎች ረዳትነት አርሶ አደሩን በማደናበር አርሶ አደሩ የምርት መሣሪያ የሆነውን 153 በሬዎች እንዲታረዱ ማድረጋቸው ታውቋል ። ከዚህም ሌላ አልፎ አልፎ አንዳንድ ፀረ አብዮት ድርጊት በፈፀሙ ተፅዕኖው እንዲወገድ በመታገል ላይ ነው ። የሚፈጸሙትን አሻጥሮችና ተንኮሎች ለማውደም አርሶ አደሩ ዋና ችግሩና ጥያቄው ድርጅትና ትጥቅ ሲሆን መንግሥትም ለሟሟላት ቃል ገብቷል ።

የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ ትግል የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነታቸውን የገረሰሰባቸው በመቀሳቀሱ አብዮቱ የመደብ ጥቅማቸውን የነካባቸው አድሀሪ ግለሰቦችና ቡድኖች ጭቆኑ ህዝብ ለዕለት ኑሮው የሚፈልጋቸው ዕቃዎች ከገበያ እንዲጠፉና በኑሮ ውድነት ተማሮ ከመደብ ጠላቱ ጋ በመሰለፍ የራሱን አብዮት እንዲጠላ በማድረጋቸው የተነሳ የኑሮ ውድነት በመፈጠሩ በርዝራዥ አካባቢ በዚሁን ጊዜ የሚነሱት ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ናቸው ። ቢሆንም ወዳጅና ጠላቶቻቸውን በንቃታቸው ሲለዩ የተበታተነውን ሀይላቸውን በአንድነት ሲቀናጁና በከፍተኛ ደረጃም የተሳካ አመፅ አድርገው የፖለቲካ ስልጣን የሚጨብጡት በከፍተኛ ትግል በመሆኑ ከፍተኛው ጥያቄ ድርጅትና ትጥቅ ነው ።

ምንም እንኳ ከታዩ የርዝራዡ ጥያቄ ኢኮኖሚያዊ ቢሆንም ችግሩን ያመጣው የአድሀሪያኑ ሴራ ሲወድም አብሮ እንደሚወድም የታወቀ ነው ። በትጥቅ በኩል ከድርጅት ጥንካሬ ጋር አብሮ የሚሄድ ስለሆነ አብዮቱ እየገፋ ሲመጣና የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ሲያስተማምን ትጥቅ እንደሚስተካከል የታወቀ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ በዋናው ከተማ ጅማና በሌሎች አውራጃ አልፎ አልፎ የሚገኙት ወዛደሮች በህዝብ ድርጅት አባሎች በየጊዜው በሚሰጠው ትምህርት ንቃታቸውን እያዳበሩ በመሄድ ላይ ሲሆኑ በተለይ በመካከላቸው ተሰግስገው የነበረው የኢ.ሕ.አ.ፓ. ኃይል ከወዛደሮች ሁኔታ እንደሚታየው ከጥቂት ወራት በፊት ከነበረው ሁኔታ አሁን ለውጥ በማሳየት በአጭር ጊዜ ውስጥ ይደመሰሳል ለማለት ይቻላል ።

የከፋ ሀገሩን የሴቶች ሁኔታ ካየን ጭቆኑ ሴቶች መብታቸውን ለማስከበር ለሚያደርጉት ጥረት በአሁኑ ጊዜ በጅማ ከተማ 27 የሴቶች ማህበራት ሲኖሩ በገበሬው አካባቢ በአውራጃዎች በሙሉ 317 የሴቶች ማህበራት ይገኛሉ ።



በማህበር የተደራጁት የገጠር ሴቶች የጓሮ አትክልት ከመትከል አልፈው ከገበሬው ለርሻ አብሮ በመሳተፍ ማህበራቸውን በማጠናከር ላይ ሲሆኑ በከተማው የሚገኙት የሴቶች ማህበራት የባልትና ሥራዎችን በመሥራት የህብረት ሱቅ በማቋቋም ሽማዎችን በመስራትና ማህበራቸውን በማስመረቅ በኢኮኖሚ መስክ በማደራጀት ላይ ናቸው ።

ጭቆኑ ሴቶች በተለይም በገጠሩ የሚገኙት ሴቶች የሚያነሷቸው ጉዳዮች እንደሚያስፈልጋቸው በየጊዜው በመጠየቅ ላይ ሲሆኑ በከተማው የተደራጁት ሴቶች ያለባቸው የመሰብሰቢያ ቤት እጦትና አንዳንድ የቀበሌ ማህበራትም ሆኑ ቢሮክራሲው ማህበራቸውን በህጋዊነት ደረጃ እንደማያዩላቸው የሚገለፁት ችግር ነው ።

በአውራጃዎችና በወረዳዎች በመቋቋም ላይ ያለው የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ያለውን የሰው ኃይል በማስተባበር የጭቆኑ ሴቶችን ንቃት ለማዳበር ታጋዮችን መልምሎ ለፖለቲካ ት/ቤት መላኩ ሲታመንበት በሌላ በኩል ያለው ችግር ሴቶች በሚያሳዩት የትግል ውጤት እንደሚፈታ የታወቀ ነው ።

አድሀሪያንና የአናርኪስቶች ቀንደኛ መሪ ራሱን ኢ.ሕ.አ.ፓ. ብሎ የሚጠራው ቡድን ከዘመቻ ጊዜ ጀምሮ ወጣቶችን እንዳያነብና እንዳይደራጁ አፍኖ በመያዝ ከጥቂት ወጣቶች በስተቀር የወጣቱ ንቃት ዝቅተኛ ነው ። በተለይ በአሁኑ ጊዜ የወጣቶች ማህበር በከፋ ሀገሩ ባይኖርም በአንዳንድ ተራማጅ ወጣቶች አማካይነት በዚ ያሉት የጥናት ክበባት በመመስረት ላይ ናቸው ። ቀንደኛው የኢ.ህ.አ.ፓ. ኃይል እንደ ዋሻ በሚቆጠረው በጅማና በአጋሮ ከተሞች ጥቂት ወጣቶችንና የንዑስ ከበርቴዎችን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ቢሞክርም ከሁለት ወራት ወዲህ ወጣቱ ክፍል ሁኔታው እየገባው ሲመጣና የኢ.ሕ.አ.ፓን መጋለጥ ሲመለከት ለብቻው የመደራጀት ፍላጎት እየጨመረ በመምጣት ላይ ነው ።

የአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከታወጀ ጥቂት ጊዜያት ሲያልፉ በሌሎ በጅማና በከፋ አውራጃዎች ሕዝቡ ስለአዋጁ በመጠኑ በተለይም የገጠሩ ገብቶታል ። በቀሩት አውራጃዎች የሰው ኃይል እጥረት ሲቃለል ጭቆኑ ሕዝብ በይበልጥ ይገባዋል ተብሎ ይታመናል ።

ይህ አዋጅ ወደ ሶሻሊዝም እንደሚሸጋገርና ጭቆኖችን እንደሚያስደስት ሁሉ በአንፃሩ አድሀሪያንን እንደሚያስቆጣ የታወቀ ነው ። ስለሆነም በገጠሩ ተሰግስገው የነበሩት ርዝራዦች የአዋጁን መንፈስ በመረዳት ምህረት በመጠየቅ መስመራቸውን አስተካክለው ከሠፊው ሕዝብ ጋር ሲዳመሩ በከተማው ካሉት ጥቂት አናርኪስቶች በስተቀር ሕዝቡ በሰሚናርም ሆነ በልዩ ልዩ ትምህርታዊ ገለፃዎች በቂ ትምህርት አግኝቷል ።

በከፋ ሀገሩ በገጠሩ የሚገኘው አርሶ አደርና በከተማው የሚገኘው ወዛደር ዋና አጠቃላይ ጥያቄአቸው ድርጅትና ትጥቅ ሲሆን ባለው የኑሮ ውድነት ባቢያ የኢኮኖሚ ጥያቄ እንደሚነሳ ቀደም ሲል ተገልጿል ።

ሠፊው ሕዝብ ወደ ስልጣን ግፋና የሚያደርገውን ጉዞ ለማገዝ በሚያዝያ ወር 68 ዓ.ም. የተቋቋሙት የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት በየክፍለ ሀገሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በማቋቋም ሥራውን በተቀላጠፈ አኳኋን በማካሄድ ላይ ቢሆንም በከፋ ክፍለ ሀገርም የተቋቋመው የህዝብ ድርጅት ጽ/ቤት በዋናው ከተማ ሥር ሰደዱ ጅማን የአናርኪስቶች የጠነከረ ግፋፊት ራሱ ፖስኮር ነው :: ጽ/ቤቱ በተለይም በጅማ አውራጃና የወዝአደሩ ክፍል በሚበዛበት በሊሙ አውራጃ /ቀደም ሲል የክፍለ ሀገሩ ዋና ረዳት ሀላፊው ባደረጉት ጥረትና ከዋናው ጽ/ቤት በተሰጡ ሰነዶች/ ሥር ሰዶ ለማለት ይቻላል :: በቀሩትም አውራጃዎች በቅርቡ እንደሚቋቋሙ መጠን በሠፊው ሕዝብ ዘንድ ሥር መሰደዱም ከሚሰጠው ትምህርት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው ::

ጽ/ቤቱ አሁን ከተቋቋሙት 7 የወረዳ ጽ/ቤቶች ሌላ በቀሩት ወረዳዎች ለመክፈት ተራማጅ ወጣቶች በመመልመል ይበልጥ እንዲነቁ በመላክ ፖለቲካ ት/ቤት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ናቸው :: በአውራጃ ደረጃ ጽ/ቤት ያልተቋቋመበት ግሺ አውራጃ ቢሆን እሱም በቅርቡ እንደሚቋቋም ታውቋል ::

የክፍለ ሀገሩን ሠፊ ሕዝብ በየገጠሩ በመዘዋወር የሴቶችን ማህበራት የገበሬ ማህበራትና የወዝአደር ማህበራትን በማደራጀት በማጠናከርና የጥናት ክበቦች በመመስረት ንቃታቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ ላይ የሚገኘው የክፍለ ሀገሩ የሕዝብ ድርጅት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከየአቅጣጫው ብዙ ችግር እንደሚደርስበት የታወቀ ነው :: በተለይም በቢሮክራሲው በኩል ከፍ ያለ ችግር ሲኖር፣

ወዝአደሩን ለማንቃት እንዳኳን የአሰሪዎች ተፅዕኖ ባለመወገዱ የወዝአደሩን ሙሉ ተሳትፎ ለማግኘት ችግር አለ ::

የአስተዳደሩ ክፍል ሠራተኞች አንዳንዱ የአሰራር ጉድለት በማጋጠሙ ብዙውን ጊዜ ችግር በመፍጠሩ ዋናው መፍትሔ ባስቸኳይ ተጠንቶ ርምጃውን መውሰድ አጣዳፊ ተግባር ነው ::

ከዚህም ሌላ የቀሩት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ባለሥልጣኖች ከጥቂት በስተቀር ብዙዎቹ ከጽ/ቤቱ ጋር የሚተባበሩ ናቸው ::

አድሀሪያን ከገጠር የኮበለሉና የከተማ ከበርቴዎች እስከ አፍንጫቸው የታጠቁ በመሆናቸው አልፎም ለአናርኪስት ክፍል ይቀበላሉ የሚል ስጋት በከተማ የተሰገሰጉትን አድሀሪያን ትጥቅ የማስፈታት ተግባር አጣዳፊ ነው ::

በአሁኑ ጊዜ የወጣቶችንም ሆነ እንደ መምህራን ያሉትን የንዑስ ከበርቴ አባሎች የአሰላለፋቸውን መስመር ያየ እንደሆነ ብዙዎቹ ወደነፈሰበት መንፈስ በስተቀር የራሳቸው የሆነ አቋም የላቸውም እነዚህኑ በቅርቡ ተገናኝቶ አቋማቸውን እንዲያስተካክሉ የጥናት ክበባት በመቋቋም ላይ መሆናቸው ቀደም ሲል ተገልጿል ::



በየዋህነት ተወናብደው ከመሰረታቸው የተጨበረበሩም ሆኑ አውቀው ተወናብደው የሚያወናብዱትን ወጣቶች ወደመሪያ በጥናት ክበብ አማካይነት አቋማቸው ከተስተካከለ በማህበሩ የመደራጀታቸው ጉዳይ አሳሳቢ ነው :: በወዝአደሩ ክፍል ንቃቱ ከፍ እንዲልና ትክክለኛ መስመሩን ይዞ እንዲጓዝ ለማድረግ ምንጊዜም የቀረበ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው የታወቀ ነው ::

የክፍለ ሀገሩ ጭቁን ህዝብ ቀደም ሲል በጥቂት የገጠርና የከተማ ከበርቴዎች ሲበዘበዝ የኖረ እንደመሆኑ መጠን ጭቁኑ የከፋ ህዝብ አብዮቱን የሚመለከተው እንደ አይን ብሌን ነው :: አድሀሪያንን ለመደምሰስ የትጥቅ ጉዳይ አሳሳቢ ቢሆንም መታጠቅ የሚገባው ክፍል አቋምና የመደብ ይዘት በሚገባ መጠናት አለበት ::

በሌላ በኩል ወዝአደሩ በአሁኑ ጊዜ የአሰሪዎች ተፅዕኖ ስላለበት የሚሰጠውን ትምህርት እንዳኳን በደንብ ሊያገናዝበው አልቻለም :: ይህ የአሰሪዎች ተፅዕኖ ለአናርኪስቶች ወዝአደሩን በእጅ የማግቢያ ዘዴ ለማድረግ ስለሚቃጡ ያለው የአሰሪዎች ተፅዕኖ መወገድ ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ነው ::

የወጣቶች ክፍል መስመር ለማስተካከል በት/ቤት አካባቢ የሚሰጠው ትምህርት ፖለቲካውን ቢያዳብልና በተለይም በከተማው የቀሰቀሱ ጽሁፎችን ለማጣራት ይረዳን ዘንድ አንድ ቤተ መጽሐፍት ተቋቁሞ የመጽሐፍት ርዳታ ቢገኝ ጥሩ ውጤት ያስገኛል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ::

ባጠቃላይ ከሁለትና ከሶስት ወራት በፊት በክፍለ ሀገሪቱ በዋና ከተማው ያለውን የአድሀሪያንና የአናርኪስቶች እንቅስቃሴ ከአሁኑ ሁኔታ ጋር ስናገናዝበው ምን ያህል ሀይላቸው እንደተቀነሰ ለመገንዘብ ብንችልም፤ ለሀይላቸው መቀነስ ምክንያት የሆነውን እንዲገፋበት በማድረግ የህዝብ ድርጅት ጽ/ቤትም ሆነ ተራማጆች ትግል ቢገፉ በቅርቡ የአድሀሪው ቡድን ሀይል ይደመሰሳል ብለን እናምናለን ::

ድል የሠፊው ሕዝብ ነው

<u>ማ ስ ታ ወ ሽ</u>

የፀጥታ ጓድ አባሎችና የገበሬ ማህበራት ቁጥር የኩሎ ኮንታና የማጂ አውራጃ ለወደፊት እስክናቀርብ ድረስ ለጊዜው ባለማግኘታችን ከላይ የተጠቀሰው ቁጥር የአራት አውራጃዎች ጠቅላላ ድምር መሆኑን እንገልፃለን ::

ጆን.ኤች.ስፔንሰር የተባለ አሜሪካዊ የኢትዮጵያ አብዮት

ለመቀልበስ ስለሚቻልበት ዘዴ ለአሜሪካ ምክር ቤት

/ሴኔት/ ያቀረበው ሪፖርት ሲጋለጥ

ኢምፔሪያሊዝም በብዝበዛና በጭቆና በገነባት ተከትሎ በያዛቸው አገሮች በሰላ ኪራይነት በአስተማሪነት በታዛዥ ወኪልነት በለማኝነት በአገር ክኅደትና በሌሎችም የውጭ ዘርፎች አቀጣጥሮ ከኢምፔሪያሊስት አገሮች የሚመጡ ቡድኖችና ግለሰቦች የኢምፔሪያሊስቶችን ሰላዮች አንደሆኑ ለመጠራጠር አይቻልም ። እነዚህ ሰላዮች ደግሞ በበለጸጉ የሥራ ክፍል የተሰበሰቡ ድርጅቶችና አጋጣሚዎች ሲሆኑ ። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ በቀጥታ ጉዳዮች ወይም በአጠቃላይ በአንድ አገር ላይ ኤክስፐርቶች ሆነው የሚሠሩም አሉ ። የኢምፔሪያሊስት አገሮች አምባሲዎችና ጉዳይ ፈጻሚዎች ደግሞ ይህንኑ የሰላይ ተግባር የሚፈጽሙ የሚያቀናብሩ ስሆናቸውም ከቶውም ለመጠራጠር አይቻልም ። በተለይም የሰፈሩና የተጋጋለ አብዮታዊ ትግል በሚካሄድ ላይ ባለን ሀገር ግን ወደዚህ አይደለ ግን በመቀላቀልና በይሉኝታ በኅቡዕ ኢምፔሪያሊስቶች ሜሬዎችን የተናጠ እንዲያ እንደ ሚገባው የተከበተን ነገር የለም ማለት ነው ።

ከዚህ በታች የምናቀርበው ጆን.ኤች.ስፔንሰር የተባለ አሜሪካዊ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በሚመለከተው በኩል ኤክስፐርት ተብሎ አንድ አጠቃላይ ሪፖርት ለአሜሪካ ሴኔት /ምክር ቤት/ አቅርቧል ። ሌላን የተባለ አሜሪካዊ ቀጣጣይ ሪፖርት ለምክር ቤቱ አቅርቧል ። ለጊዜው የምንለግለው በስፔንሰር ሪፖርት ላይ ነው ።

ጆን.ኤች.ስፔንሰር ከ40 /አርባ/ ዓመታት ጀምሮ ኢትዮጵያን እንደሚያውቃት ይናገራል ። ለዚህን ያህል ዓመት ለሲ.አይ.ኤ. በቅጥር ወረኛ እንደሰበሰበ ለመገመት አያስቸግርም ። በዚህ ዓይነት በአገራችን ሌሎችም ብዙ ዘመን የተቀመጡ የሚገኙ የሚሠሩ አሜሪካኖችና ሌሎችም ደህና አድርገው እንደሰለሉን ጥርጥር የለውም ። ጆን.ኤች.ስፔንሰር ያቀረበውም ሪፖርት በበኩሉ ከአንዱ የአሜሪካን ሰላይ እንደቀረበ አድርጌ እወስደዋለሁ ። ይህ 45 /አርባ አምስት/ ገጾች ያሉት ሪፖርት " የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በተለይም ከአሜሪካ ጋር ያለውን አገናዘበ የሚያጠቃልል " ተብሎ የቀረበ ነው ።



በዚህ ሪፖርት ብዙ የሚያሳስቡ ነጥቦች አደገኛ ገምገማዎች ተደርገዋል ። አሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያ አብዮት ለመቀልበስ የሚያዘጋጃቸው ኃይሎች አነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠቁማል ። ይህ ሪፖርት እርግጥ ሚስጢራዊ ቢሆን ኖሮ በግልጽ ለአሜሪካን ሴኔት /ምክር ቤት/ ቀርቦ ከዚያም በዜና ማሰራጫ አገልግሎቶች ለአሜሪካ ሕዝብ /ፐብሊክ/ በቀላሉ ባልደረሰም ነበር ። አሁንም ቢሆንም በአገራችን ሊወጣ ባልቻለም ነበር ። ስለዚህም አንድ ወቅት ማለፍ የሚፈልገው ነገር አለ ። አብዮታችንን ለመቀልበስ ብዙ ሚስጢራዊ ጥናቶችና ዝግጅቶች አሜሪካኖች በስለላ ድርጅታቸው /ሲ.አይ.ኤ./ አማካኝነት በግ ከናወን ላይ እንደሚገኙ በማያጠራጥር ነው ። እንዲህ ዓይነት ጥናትና ዝግጅት አሁን በአገራችን ከሚገኘው የስፔንሰር ሪፖርት አንጻር የሪፖርቱ ዶናልባትም የሚገለገልባቸው ወሬ ኛዎች እንደዚህኛው ያሉ ቶሎና የተዘጋ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ ። ስለዚህም ሲ.አይ.ኤ. የሚሰበስበን ሤራ ከሙሉ እንዳለሆነ ተረድተን የበለጠ ወዛጅነት አለብን ። በበኩሌ የስፔንሰርን ሪፖርት ለማጋለጥ ከሪፖርቱ ውስጥ ብዙ ነገሮችን ወጥቶ ያስፈልጋል ። ነገር ግን የማተኩረው ከሪፖርቱ ዋና ነጥብ በዋነኛ ነጥብ ላይ ነው ።

ላለፉት 40 ዓመታት የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ ግንኙነቶች በሚመለከተው በኩል ታዋቂነት በማትረፍ ራሱን እንደ አዋቂ የሚቆጥረው ጆን.ኤች. ስፔንሰር ለአሜሪካን ሴኔት /ምክር ቤት/ ባቀረበው ሪፖርት እንዲህ በማለት ይጀምራል ።

" ለመጀመሪያ ጊዜ በሰሜን ኢትዮጵያና በኢትዮጵያ መካከል ወርቅነት በተካሄደበት የወርቅ የተካሄደት ወገኖቻቸው ወርቅነት /ሌን እና ሂንዶን/ ሰታቸው በነበረበት በዚያን ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ በመጣ የአሜሪካና የኢትዮጵያ ግንኙነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኝ ነበር ። ነጻነት እስከ ተመለሰበት ዕለት ድረስና ከዚያም በኋላ በዚሁ ደረጃ ላይ ይገኝ ነበር ። በተከታይ ግን ይኸው ግንኙነት እንዲሠራር ተ ከበሩ ዘውዱ /ባይከለ/ አንጻር ከፍ ተኛ በሆነው ማዕከላዊ ሥፍራ ደርቦ ከዚያ እንደገና ዐይታቸው በማሸቆልቆል የወፍ ከፍ ረበት ዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ይገኛል ...." ይላል ። ስፔንሰር በዚሁ አባባሉ ዛሬ የኢትዮጵያና የአሜሪካን ግንኙነት የሚገኝበትን ደረጃ ካመለከተ በኋላ የወደፊት ተስፋውን እንዲህ ወንድሙ ከእንግሊዝና በሎ ይቀጥላል ። " በአንድ ወቅት ከበ ዘውዱ /ኃይለ ሥላሴ/ ላይ የግንኙነት ደረጃ እላለሁ

ሠራዊት ከጎለበተ ወቅት ላይ እንደሚገኝ በእርግጥም ብዙ ለማድረግ በቂ ምክንያት አለ ።/ ይህንኑ ስጋት አትጠፎና ወነሽ ምክንያቶችን በማቀረበው ጽሑፍ ለመጠቆም እፈል ጋለሁ" ይላል ጀን.ሉቺ. ቢንገር ። /ሰረዝ የተጨመረ/

የጀን.ሉቺ. ቢንገር ራፖር " አሁንም ለቀጣዩ ሚናዋ የአሜሪካን ፖሊሲ ለሶማሊያ ዛሬ እንደ ተጨፈረው ባደረር በአገራችን ሊያገሠራፉና ሊገሠሩ የሚችሉበትን እቅዱ በማቀረቡ በፊት በለኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በአጠቃላይ ለማመን ይቀበራል ።

" ኢትዮጵያ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ነጻነቷን ጠብቃ ለተቀዩ የጋለቸው አካባቢውን በምዕራባውያን ለማዳከም ከፍተኛ ፖሪት በነበራቸው ኃያላን መንግሥታት መሀል አ የገኛት በአገሯ ከቤላ ሊያውን ለማገለል በአጋለች ነው። ይህ ፖሊሲ ግን ሳይሠራላት በቀረ ጥር ነጻነቷ ይደረር ነበር" ይላል ።

ይህንን ገዱዲ ሀሳብ ተከበለኛ ለማስጊት የቢንገር ራፖር ካለገበት ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ኢትዮጵያ ከምዕራብ ዓለም በተለይም በየጊዜው ኃያላን ከነበሩት መንግሥታት /ዛሬም በጠየቀ ቀንቀን ጨምሮ/ ጋር የነበራትን በአገሯ ከቤላ ሊያውን የማ ለለ ፖሊስ በዚህም ፖሊሲ ባቢያ ተፈጠሩ የሚያገኙን ሁኔታዎች ይዘከዝባል ። እነዚህ ተረቶች በለሆኑ አነርሱን ለሳነሳም ። ከዚያም በለአሜሪካና ኢትዮጵያ ግንኙነት በፕሬቀ ለመመርመር በእነዚህ ግንኙነቶች ላይ የበላይነት ለሳገው የሚገኙን በተፃራሪነት የሚ ወደሱ ሁለት ኃይሎች በሳሉ እነርሱን ማስጠቅ እለበኝ ይላል ።

ለመሆኑ እነኚህ የተባሉት ሁለት ምድብ ኃይሎች ምንድና ናቸው?

የቢንገር ራፖር " በተቀዳሚ የሄበረው የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ በአ ፍሪካ ቀንዱ የሚኖረውን ሁሉ ገበ ሚና ለማስቀረት የሚቀበር የኃይል ሰምራት አለ ። ይህንን ምድብ " ክፍል ሀ " ብዬ አጠራቸዋለሁ። ሌላው ተጻራሪ የኃይል ምድብ " ክፍል ለ " ደግሞ ኢትዮጵያን ቋሰቡ በአሜሪካ ዙሪያ ከለለ ወጥቶ እንደትገኝ የሚገፋ ኃይል አሉ። ይህንን ደግሞ " ክፍል ለ " ብዬ ሰይሜዋለሁ" ይላል ።



ከዚህ በኋላ " ክፍል ሀ " እና "ክፍል ለ " የተባሉት ምድብ ኃይሎች ካለገበት ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በአሜሪካና በኢትዮጵያ ግንኙነት ላይ የነበ ራቸው ተጽእኖ እነኚያ እነኚህ ነበሩ ተብሎ ተዘርዝሯል ። በራፖርቱ ወጥቶ በበራው ከበረፈት የታሪክ ምንባቦች ለገረኝ የሚገኘው ነገር በኛ አሜሪካ በበቀው ከነበረው የሞንሮ ደክተሪን /የውጭ መመሪያ/ የትሩማን የኔቶ ደክተሪን እስከ ዛሬው ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ ወጥቶ በዙ ወገኖች መነሻ ደርሶብኝ በኋላም ለረጅም ጊዜ እስከ 1970 ዓ.ም. በአገራቱ የነበረኝ የበላይነት በማለም ነው ፍንት አሸቶ ቀመጡኝ እዚህ ደርሻ ለሁ እንደምትል ነው ።

የቢንገር ራፖር የመደረሻ ገበ ኢትዮጵያን ቋሰቡ በአሜሪካ ዙሪያ ከለለ ወጥቶ እንድትገኝ የሚያገዝ ኃይል የት እንዳለ ካመለከተ በኋላ አሜሪካም ይህንን ኃይል ይህና አጠርጎ እንድትጠቀምበት መገፋፋት ነው። እንደርሰበታለን ።

በ1970 ዓ.ም. ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት በውጭና በውስጥ ቀራኒዎች በመፀ ጠቀ በተለይም ከዓረቦች ጋር የነበረው ግንኙነት በመሻከሩ አገሪቱም በአገሪቱ ውስጥ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውሶች /በራዝ/ ተባበሰ ገንዘብ የሚደማውን መገፋት ተረዱቶ ተዋጊውን ለማዘጋጀት ራያደር ባለመሆኑ " የተባበረው የአሜሪካ መንግሥት ከገንዙ ወዲያ በኋላ በቀላሉ ሊገረሰሰ ከሚችለ አገዛዝ ጋር ተደምሬ ወታየት ለለፈለገችም ነበር" ይላል ራፖሩ ። ራፖሩ ከዚሁ ጋር አያይዞ " በ1973 ዓ.ም. ገዢው የነገሥቱ በሽግ ግ ተገ ለቶ ዝግጅት ባደረገበት ጊዜ በኤርትራና በኦጋዴን ያለውን አበጊ ሁኔታ አበመለ ከቶ ተረግሬ ወታደራዊ እርዳታ በመደቀም አሜሪካ ፈቃደኛነቷን አላገኘችም ነበር ። ይህም በመሆኑ ቀውጦሬያው ዓመጽ ከፈነዳበት 1974 ዓ.ም. እገበቶ እስከ ገዢው ነገ ሥቱ ዕለተ ሞቱ /አረፍቱ/ ድረስ ሚለትም በነበረው አበጊና መንግሥቱ ለማበርገድ እስ ከተጋለበት ድረስ በነበረው የፖለቲካ ዝግጅት አሜሪካ በእጅ አበባ ለመወከል ፍረጠ ቸው በጉዳይ ፈጻሚ ደረጃ በቻ ነበር ። " /ሰረዝ ያልደረሰ/

ከራፖሩ ውስጥ የተመቸው ይህ አባባል ሊያሳዩ ነገ የሚቀበረው አሜሪካ ከጣቂት እንቅስቃሴ ቀደም በሎና እስከ ኃይለሥላሴ መውደቅ ድረስ በኢትዮጵያ ጉዳይ ገለለተኛ

ተወካዮች ነበረች ። ለንጉሡም " የኔ ቦታ አይደለም " ፤ " እኔን በጋን የሚያ ሳኝ የለም " የሚል መንገድ በሊነበሩት አይደለም በኢትዮጵያ በመሰብሰብ ላይ እንደነበረች ለማሳመን ይሞክራል ። በፔንበር አሜሪካ ዝቅተኛው ነበር የግሉ የተወካዮችነት እንዲ ዛሬ በአገራችን ለተፈጠረት ሁኔታዎች ተጠያቂ ይሆን እንጂ አንገሰጸው የጠላ አድርጎ ይናገራል ።

" አሜሪካ በተለይ ፍርሃት ከተወሰኑ ነገ ከሚመራ መንግሥት ጋር አንድ ወሰሉ ሳለመታየት የሚል ፖሊሲ በተከተሉም በመሠረቱ ግን አሜሪካ የተተካው መንግሥት ለረጅም ጊዜ ከምዕራብ ዓለም ጋር ከነበረው ወዳጅነት ይልቅ የሶሻሊዝምን አቋሟ መረጠ ። "

ሶሻሊዝም
አገቢቢ ከና ብቻ ወቀሜው የነበረውን ካፒታሊስት አሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚ ኖሩትን ግፍ ለማስቆረጥ የሚጠበቅ የኃይል ምንጭ መሆኑ ነው ።

ታዲያ ኢትዮጵያን ወልበ በአሜሪካ ዘሬያ በሌለ እንደተገኘ ለማድረግ የሚያበቸለው 'አሁን አቋሟ' ምን ይሆን ? ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከረዥም ጊዜ አገብቶ ከምዕራብ ዓለም ጋር የነበረውን ወዳጅነት ትቶ የሶሺያሊዝም አቋሟ ተከተለ የሚለውን በመቀበል የተነሳ የተጋነነበትን ዐረፍተ ነገር በፔንበር ትገሮ አለበትም ። 'የዋንቱ ወዳጅነት' ተወለሰ እንዴት እንደሚነገሩ ይናገራል ። ማለትም የኢትዮጵያን አብዮት ለመጠበብ ወሰበም የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም የበላይነት በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ጫንቃ ላይ ለማስፈር አሜሪካ በየትኛው ኃይሎች መጠቀም እንደምትችልና እንደሚገባትም ከመጠቆም ወደኋላ እንደማለ ዘዬ በለን እናያለን ። ከዚያ በፊት አንድ ለምክር ቢቀ በፔንበር ባቀረበው ፊታር የገለፈረ አበኛን ጉዳይ አለ ። ለምን እንደሆነ ግን ለመስተላልፍ አልቻልም ። ወቂሼ ብቻ አለፋለሁ ።

'የአሁኑ የደርግ አዘማሚያ በቃል ዘተደርጓልት ይልቅ ወደ ሶቪየት ሶሺያሊዝም የተጠጋ ነው ። ይሆም የሆነበት ምክንያት ደርግ ከልሆበ ደርጉት ጉዳይ ሊ/ቤት ከፍተኛ ትኩረት በሰጥደርበት ነው ። ሊ/ቤቱም ራሱም በዚሁ አቋሟ የሚገፋው በኢ.ሠ.አ.ፓ. ነው .... ። የሊ/ቤቱ የኢ.ሠ.አ.ፓ. ማዕከላዊ አመራር የተያዘው ትምህርታቸውን በውጭ ሀገር ቀቆ ከሚኒሆች ነው ። " ይህ እንግዲህ ከፊታሪ የምናነበው ነው ። ነገር



ግን እውነት በፔንበር ራሱም ሆነ ወይም አሜሪካኖች በዚህ አባባል በጣም ያምኑበት ይሆን? አጠራጣሪ ነው፣ ምናልባት አንድ ነገር ይኖራቸው ይሆናል ።

ከዚህ በኋላ በፔንበር ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከሶማሊያ ጋር ስለ ጋጋና በኩት ገብሬ በአገር ውስጥ ስሆን ተቃዋሚዎች ስለሰሉት ችግሮች ውስጥ ይገኖለ ካለ በኋላ " የአሜሪካ መንግሥት በተለይ ዛሬ ባለንበት ወቅት ወደ ክሙኒስቶች ለሚያዘነብለው ከዚህም ጋርከፋን ወደ ፋን ወጥቶ ለተረጋገጠለት መንግሥት የሚለብቻ ውጊያ እንደምንት ማበቃቀም ይቻላል? አሜሪካ በ1973 እስከ 1974 ዓ.ም. ለክ በዚሁ ዓይነት በኢትዮ ከኃይለሥላሴ መንግሥት ፊቅ በሉ ነበር ........ አሜሪካ የተኛውን ለመምረጥ አስቸጋሪ ለሆኑት ወገን ችግሮች ምትሰጠው ወለበች ወገናዊ ሆኖ ነገር ግን የሚያወለዳ መሆን የለበትም ። " /ገጽ 37/ ይህ እንግዲህ የበፔንበርን የሮጣቶት ወገድ ከፊታር አገበበን ምናገኘው ነው ።

በፔንበር በሮጣቶቱ ያለዘነበትን ወደ ተጠግተኘት ለጠም ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሊያገለግሉ ይችላሉ በሎ ያመነባቸውን ክፍሎች በፊታሩ ውስጥ አቀርቧል ። ወታደራዊ አርዓታ መበጠብ ቢያበረለን ምን መከተል እንደሚገባ በሶማሊያና በኢትዮጵያ ማሀል ባለው አለመግባባት በመጠቀም አሜሪካ ድር ሠራዊት በሱዳ በርሀ ክሳም ጥበቃ ጋር ክለ እንደሰፈረ በአጋዥን ወበረር ቢችል ደብ እንደሚለው በፔንበር አለደበም ። ሌላው ደግሞ በአካባቢው ካሉ የዓረብ አገሮች ሌላ /ሁሜንጉ ወምሮ/ በኢራንና በዛይር ጭምር ተጠቅማ አሜሪካ ኢትዮጵያን በመንፈሥር ለማቆየት በትችል አሜሪካ ለዳንዶ ማሸት እንደ ሌለባት ይናገራል ። በሌላ በኩል ደግሞ በፔንበር 'የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያ ግንባር' የሚባለው ድጋፍ ገቱ ፋሺስታዊ ድርጅቱ የረቦ ፀረ አብዮት ሥራ መበራቱን ይጠራጠራል ። የጎሳየ ከፍላቱ ሀገሮችን አየወለደ ለትለቢ ግልጋሎት እንደማይሰጡ ይናገራል ። ፀረ አብዮት ኃይሎች ገና ባልተወተባት ከፍላተ ሀገሮች እውነተኛ የሚያበሩትን ለወፊር እንደሌላቸው በፊታሩ ለመገለጽ አላፈረም ። ፊታሩ አድሲኛ ሲያበና ወሰጋ ክርስሉት ከመሬት አየዳ ወሠ ደርግ ይጋሬዎች ሆነዋል ይላል ።

ታዲያ የሚያስተማምኑ ቁጠኛ ኃይሎች የት ይሆን ያሉት? ለመፈናገስ በሚያስቶ ማን መንገድ መውሰድ የሚችለው ማን ነው?

ጀ.ጌ.ኤች. ሰኔገበር ይህንን ጥያቄ ፍርጥርጥ አድርጎ መለሰው ለአሜሪካ ምክር ቤት አቀርቦለ ። ከሰኔገበር ሪፖር እጅግ ማብር የሚገኘው በዚሁ ላይ ነው ።

አዲስ አበባ ለቀለበት አስተማማኝና አማካይ ሥፍራ ሆና ተመርጧለች ። "ገቀና ው ቀደሚያ ለመውሰድ የሚችል ኃይልም ያለው አዲስ አበባ ነው" ይላል ጀ.ጌ.ኤች. ሰኔ ገበር ይበልጥ ገለፃ ሲያደርግም "፤ እዚሁ አዲስ አበባ መንታና መረሻን ለዘጠኝ ኃይለኛ ሸበር ላይ ትሎታለ ። በመለቀ ለቢሾ ወለል መታተር ይታያለ ። የሆለታ ራዲዮ የሮፋታ የበላይነት በሳሳቸው ሙረር ወገ አትግቶ ሮፋታን አሸቀገገረው ግደ ተቃሚ ሠፈር አንጓጉን አድርገቶዋለ ። በሆለታው ገሬኝ የሸቀ ተዐሰዶች ተክአና በሊሊቸው በሠ ራዊት ወገኖ ቀሬታ ባደረባቸው በአማራና በኦሮሞ ተዐሰዶች ላግ ሆነዋል ፡፡" የሰኔ ገበር ሪፖር በተለይ የሚተማመነበትን አኳኋኗ ሲጠቁም "በተለይም አየር ኃይል ተወካዮቹ የነበረውና የደርጉ የፖለቲካ ቡሚቴ ሊቀመንበር የነበረው ሻለቃ ሲሣይ ሀብቴ በግልጽ ከአሜሪካኖች ጋር ግንኙነት ለለሀ ቁጥሩ በመገደሉ አየር ኃይል ቁረረ ተቃውሞ ያለበት ማቋቋሚያ ስፈር ሆኗል ፡፡"ሰኔገበር በመቀጠል " በቀርጡ ከጠር ሠራዊቱ ከአየር ኃይል ከሃያ የሚበልጡ ወኪሎች መገደላቸው የተቃዋሚው አመራር በተከከለ የት ሠፈር ሊገኝ እንደሚችል ያመለክታል" ይላል ፡፡ ሰኔገበር በዚሁ ብቻ አላቆመም ፡፡ " ሰላን በተለይም ኩሬ በለሊት ጨዋ ወታደራዊና የፖለቲካ ሁኔታ ባሳቸው ብሬ አንቀየ ከፍተኛ አገልግሎት ሊያበረክት ይችላሉ ...... ከዚያም አለፍ ሰላን ወደሌት ጨዋ ወስፕ የሚገባውን ጥር መዛሬያ በቻቸን ለተጫጠር ትችላለች ፡፡ በለዚሁም ጥር መዛሬያ ወደሌት ጨዋ ለማስገባትም ሆነ የሚገቡትም ንም ለመቆጣጠር ደህና ለታገለገል ትችላ ለች" ይላል ፡፡

ጀ.ጌ.ኤች.ሰኔገበር ለአሜሪካ ሰኔት /ምክር ቤት/ ካቀረበው ሪፖርት ዋናው ም ና ቋኦርበት ነገበ ከዚሁ በላይ ከፍ በሉ የጠቀስኩት ነው ፡፡ ሰ.አይ.ኤ. የኢትዮጵያ



ሕዝቦች አበዮታዊ ትግልና በትግላቸው የተጐናጸፏቸውን ድሎች ለመቀልበስ አገኛችለ የሚያቋርጧቸው አካባቢያዎችና ኃይሎች የትና የትኞች እንደሆኑ ከሰኔገበር ሪፖርር ለመ ረዳት ይቻላል ፡፡ ሰኔገበር በዙ ዝርቦችን ሲያቀርብም የበለጠ ትኩሬ ያደረገው በጥናው ከተማ ባሉ ኃይሎችና በተለይም በጦር ኃይሉ ወስጥ ነው ፡፡ ሰኔገበር በሪፖርቱ ያነሳቸውን አንዳንዶችን ^ነጥቦች^ ወስዶ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያገናዘበኩ ጠቅ ለናገር ፡፡

አዲስ አበባ ለቀለበት አማካይ ሥፍራ መሆኗን ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቻ ባይሆን ተራማጅ አበዮታውያን ሁሉ ያውቃታለ ፡፡ "ገቀና ው ቀደሚያ ለመውሰድ የሚችለም ኃይል" አዲስ አበባ ወስጥ እንዳለ በአሜሪካን ሰላዮች ወደገሬ ሊያስገርም አይችልም ፡፡ ለምን አዲስ አበባ ለቀለበት አማካይ ሥፍራ ሆነች? በአበዮቱ የመቀ በመረት ላይ ከነ በራቸው ባለቤትነት አገበቶ በከተማ የነበራቸው ትርፍ ቤትና ቦታ ያሙ አዱኃሪያች በበ ዛት ያሉት በጥናው ከተማ ነው ፡፡ ከገጠር የተባረረ አሮጌ ሁሉ የተጠራቀመው እዚሁ አዲስ አበባ ነው ፡፡ እነኚህ በተጨባጭ መንገዱ የአብዮቱ ጥቅሞቻቸው የተነካባቸውና በነ በራቸው ድርሻ በሕበረተሰቡ የነበራቸውን መደባዊ የበላይነት ያጡ ኃይሎች ደግሞ በቻ ቸውን አይደሉም ፡፡ በአበዮቱ ፈጣን ገስጋሴ ተገፍቶ ተቶፍቶ የወጣ የገዐሰ ከበርቴው ቀኝ ክንፍ ደግሞ አለ ፡፡ ይህኛው ዛሬ ከተጨባጭ መንገዱ አለፎ በድርጅት ደረጃ በአበ ዮቱ ተቀማቸው ከተነካ ጭሬት ከበርቴ ወገኖች ጋር ተሰልፍና ተባብሮ ይገኛል ፡፡ በሬው ሕዝበ ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ታግሎ ያገኛቸውን ድሎች ከመንከባከ በና የበለጠ ወደ አገኘት ከዐሬ ፊውዳልና ከዐሬ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር መ ተባበ ሩን እርገና እርጉ ወለቦ እነኚህን ኃይሎች በሰሚተን 90 %. የኢትዮጵያ አርብ አደር አገቀርም ፍቶት ዛሬ ይህ ደገሬ በውን የሚገኘው በዋና ዋና ከተሞቻች በተለይም በአዲስ አበባ ነው ፡፡ ይኸው የፋሽስት ዘገባሌ ያለው የቀኝ ገዐሰ ከበርቴ በኢ.ሀ.አ.ፓ. ስለ ተባባሪነትና ወራነት የኢትዮጵያን ወዘ አደር መደበ በተለያየ ጊዜ የሥራቢን መግባ እዱ ርጉ ሲጠዋበት የደቀቿ ከዘሳቴ ጠላቶች ይለቀ ከጊዜያዊ ወዳጆች ጋር እያጋረጠ ያበቧሬ ገሬው መሆኑን ወዘ አደሬ እየነያበት ከወጠም አቀነጠረ ሲያገኘው ይታያለ ፡፡ ይኸው በኢ.ሀ.አ.ፓ. የሚመራው የቀኝ ገዐሰ ከበርቴ ሌሎ ተባባሪዎና መመኸኚያው ቢርበራቢው ስለሆነ የቀለበት መጠንሰሻ ጓዳው አድርጉ በለማጠቀሙበት ዛሬ የዚሁ ክንፍ በዚሁ ኑ ቀጥር

ለቀበበባ የሚሆነው እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ነው። በቀጣ የኢ.ህ.አ.ፓ. የተረፍ ነፍሰ ገዳዮች በሀገሮ አብዮታዊያን ላይ የፈፀሙት ግድያ የተከናወነው በዚሁችው የአይ ሄሬጆችና የእነዚሁ ፋሽስት ነፍሰ ገዳዮች መናሀሪያ በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ ነው። ኢ.ህ.አ.ፓ. ፋሽስታዊ ግድያ በአብዮታውያን ላይ ለመፈጸም የተነሳው በደረሰበት የሞ ለቱ ከበረት አደጋ በሰ ዘመቻ ሊያ አማራ፣ አቶ ተው ከሲ.አይ.ኤ. ጋር በተደባ፣ ወገ ገዱ በመሰባሰር ፀደዚሁ ነፍሰ ገዳይነት አምር ተኛለ ። ለምሳሌ በቀርጡ በገዱ ናቀሬ ወርዐው ላይ ግድያ የፈጸሙት ነፍሰ ገዳዮች የሲ.አይ.ኤ. ሰላዮች እንደሆኑ በእጃቸው የተገኙ አንዳንድ መረጃዎች እንዳሉ ይነገራል ፤ ታዲያ ይህ ሁሉ አደሀፈና ነፍሰ ገዳይ በበዛት የተከገበገው አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን በጌገበርም ለገጠሞበት የጋቻለ ኃይል የሚሰጥ ይሆናል ነው።

ስለዚህም አዲስ አበባ ለሞካይ ሥፍራ ተበሳ ወቀረጹና "ነቀና ም ሆነ አርም ለመጣው የሚችል ኃይል" ስለ ወገሉ የፈፀፃሎችን፤ የቢሮክራቶችን፤ አንዲሁም የእነዚሁ ሁሉ ከበበ ተኖና የሆነው የገዐብ ከበርቴ ቀኘ ከገና ዐረ ሕዝብ ደባ አገኜ ሊሳ ሊሆን አይችልም ። በጌገበር በቀቀኑ በአዲስ አበባ ከተማ በሚደርሰው ወታደርና ወረሽን የተነሳ ሐዘብ ታሳቀ ሽበር ላይ ጋዜጣ የሚሰጥ የሰሬ አብዮታዊ ሠፈር መረበሽና ወሽ በር የሚገለፅ አገኜ ሊሳ ሊሆን ፍሬሽ አይችልም ። በጌገበር ከደርግ ውም ሆነ በደርግ ዉጣ በሬ አብዮት ኃይሎች ላይ የተጠበቀ አርምኞች ሁሉ በበፊው ሐኪባ ላይ እንደ ደረሰ አደርጉ ለማቀረብ ይቃከራል ። ዘር ዘር የዚህ ሰላይ ፍሳሽ "ነቀና ም ሆነ አር ምኞ ለመጠው የሚችል ኃይል" ለማለው የሰሬ አብዮት ሠፈር ለወራር እገበዮ እንዲሁናከር አርምኞ አገወበው ለማለት እንደሆነ ባይታለም የተፈታ ነው። በጌገበር "አዲስ ለቀጫ" ከሚለው አንቀ ይህ ነው።

ሁለተኛው የበጌገበር ፊፖር የሚናገረው በመለዮ ለባሹ ወሀስ ስላለው ክፍፍል ነው። እኔ በበኩሌ በመለዮ ለባሹ ወሀስ እርግጥ ክፍፍል አለ እላለሁ። ይሁንን ሁቀ በተለያዩ አገሮች ተነስተ ለመሸፋፈን ወቃከር አይቻልም ። ዝህያ ፀታደራዊ አስ ተዳደር ደርግ ራሱም በለዮ ለባሹ ወከፋፈለ Reality ሆኖ ባለ ይሁንን ለሽፋፍ ነው ይቃከራል ። እርግጥ ደርግ ፀታደሩ ከተከፋፈለ የሀገሪቱን አገዛዙንና አብዮቱን ሊጠበቀ ሊን አይችልም የሚለ ስጋት አለው። ይህ ምክንያት ራሱም ሲሆን ከበንካሳነት አይቃል ጥም ። ይህ የደርግ አቋም ከጋደቦች ተገለ ጉዑ አብዮት አገዶጋሽት ይቆጠራል ።



በበኩሌ በለዮ ለባሹን ወከፋፈለ የምታስቀምጥ አገባር ስበጌገበር አወቢ ቢከተ ጭራሽ ቶሺራሪ ነው። አንደኛ ነገር በመለዮ ለባሹ ወሀስ ክፍፍል ወኖሪ የሚ ደነቀ ነገር አይደለም እላለሁ። ወቀቀ የአብዮቱ እስከሆነ ደረስ በሕበረተከባችን ያሉ ትም ወደቦች የተፋፋወ ትግል በሚያደርጉበት ወቀቀ እስከሱ ደረስ የሁኑ ሚያ ወለዩ ለባ ሽም በዋደበ ቶሮሙ ነበሰም ሲሸበቀ ወታየቀ የሚገርም ነገር ሊሆንበን አይችልም ። በሚቲት የፊንቶው አብዮታዊ አገዐበያሬ አበበዟሬ ደረስ ከመለዮ ለባሹ ወሀስ ከአብዮቱ ደጋፊነቱ ወደ ፀረ አብዮታዊነት የተሸጋሹጉ ኃይሎች የቲት እንዳሉሆኑ ነው። በበጌገበር ሉ—ባይገባዊ ፊፖር ወሀረት የሁለቱ ፊሚሳ ምፈታ እንደ ሺለቃ ወገዳዎት የሚገለፆ ገለበቦች በበረር አኳኋኤ ምፈታ ላይ የበሳይነት በሳሳቸው ወደ እነዚሁ ገለበቦች የሽቀ አሚፊ በለሆኖ በወጋደፊ ወሀሰ ባሉት የሰሳ ክፍለ ሀገር አሚሮችና ለሮዎች ላይ የበላይነት በሳሳቸው አይደለም ። በመለዮ ለባሹ ወሀስ ሳለው ክፍፍል ወወረታዊው ም ክ ንያት ከአብዮቱ ዉጭ ወወረታዊ ምክንያት የሚለይ አይደለም ። ይህንም ሺኔበበጌገበር ሊያጠሳሳቸው በሚፈለጉቸ ገለበቦች ላይ በዘፈቀደ የሚወባች አይደለም ። ርደፊቱም ሲሆን በመለዮ ለባሹ ወሀስ ያለው ክፍፍል እየሰፋና እየጠነከ ወቀቀ አይቀርም ። መለዮ ለባሹ ራሱ በአብዮቱና በሰሬ አብዮት ሠፈር እንደሌሎች ወደቦችና የኅበረተሰብ ክፍሎች ተከፋፍሎ መጋጠሙ አይቀርም ። በፍፃሜም የሚያበቃው ከአብዮቱና ከሰፊ አብዮት አንደኛው ሲያሸንፍ በቻ እንደሆነ ለታሪካዊ አብዮታውያን ግልፅ ነው። እርግጥ ሲ.አይ.ኤ. ከመ ለዮ ለባሹ ወሀስ አደራጅቶ ወገን ለመሰብሰብ ለማደራጀትና ለመፈር(አ...)ጸሙ ወስጡን በመ ሥራት ላይ እንዳለ አይካድም ። በጌገበርም በፊፖሪ የሚጠቅሰው ደገሙ ሥራ የበለጠ እን ዲገፋበት ነው። በቅርቡ ጊዜያት የሽፍታ አውጊ የፈነዳለ ወገንሥቀ ወተራሪዎች የሲ.አይ.ኤ. ሥራዎች ወሆናቸው ተረጋግጦ ተነግሯል ። በተለይ ሲ.አይ.ኤ. እንዲህ መለዮ ለባሹ ወሀስ እንደሚሠራ ለማስቀጥ የሚሰሳ ምክሬ ለዚሁ አዮር ኃይል ነው። እንደገና አጠቀስ የሊሁበጌገበር ስለአየር ኃይል ምን ይላል?

" በቅርቡም አየር ኃይል ተሰማቶው የነበረውና ደርጉ የሻለቃ ከሚቴ ሊቀ ወገበር የነበረው ሺለቃ ሰባዶ ሀበቴ በሚሰለ ከለሚሰጭኞች ጋር ግንኙነት አለህ ብለው በመግደሉ አየር ኃይል ቸረረ ተቃውሞ ያሰተ በሰር ሀጂሽ በየደቡ ከወር ሠራዊትና

ከአየር ኃይሉ ከፍ ያሉ የሚገለጡ መኮንኖች ወገደሏቸው የተያዙው አመራር በተከበበ የት ሠፈር ሊገኙ እንደሚችሉ ያስለብሷል ።"

ይህ ወሬ አድን ያጋጣ ፈጠራ ነው ። ነገር ግን ደግሞ ሲ.አይ.ኤ. ተባብሮ የሚያስበት ኃይል ያለው ምናልባት እዚሁ አየር ኃይል ውስጥ ስለሆነ እንኳንም ይገኝበ ታል ብያለሁ ። እስቲ በበኩሌ ከሚጠቁሙኝ ነ ተነስቼ ለስፒገበር ፊታር ወሰስ ላስት ።

1ኛ/ ሻለቃ ሰሰይ ሀብቴ ከአሜሪካኖች ጋር ተባብሮ ፋሺስታዊ ወፈገዛለ ወገ ገሥት ለማድረግ ሲጥር ተደርበት የተፈለጠበትን ጭት የሷት በዙሃኑ /ከየ ፍትኑ በበተቀር/ የአየር ኃይል ወለቆ ለባሽ በጸኑ ደገፈውታል ።

2ኛ/ ሻለቃ ሰሰይ ሀብቴ ረዥም ካለ ጊዜ ጀምሮ በአየር ኃይል ውስጥ "ማፍያ" በጋባለ የሚታወቅ ፋሺስታዊ ቡድን አደቅ በመፈራት አየር ኃይለን ከመንግሥቱ ጋር በተገበለ እንድቶቀ በሴታውን ለቀለበኗ ለመዘጋ ጀት ሲሞደፉ ያጋለጡትና "ማፍያ" በለተባለው ስም ዐረ ሕዝብ ቡድን በደርግና በሰፊው ሕዝብ እንዲጋለጥ ያደረጉት ቴማጅ አበዮታውያን የአ የር ኃይል ወለቆ ለባሾች ናቸው ።

3ኛ/ 'የቀዩን ወቃደርዋ ውጻ' የሚለ አደንቃና ዐረ ሕዝብ በራፊ ወረቀት በአ የር ኃይል ለለም በሠራዊቱ ውስጥ እንዳሰራጭ የሚገፋፋ ሻለቃ ሰሳይና ዘሪሁ ለነርሱን ተከተው የሠፈ ማፍያ ቡድኖቹና ሲ.ሀ.አ.ጄ. ወሆናቸውን ተጋለጦ ፍንጭ የሰጡ አነኚሁ በዙሃኑ የአየር ኃይል ቴማጅ አበዮታውያን ናቸው ።

4ኛ/ ከሻለቃ ሰሰይ ሀብቴና ግብረአበሮቹ ወገደል በኋላ አንተገዱ የአየር ወለዱ ዐረ አበዮታውያን ሲላ የቀለበኗ መከፊ ለማድረግ አየር ኃይል እንዲተባበሩ ቸው ሲገደቀ በኋላ አበዮታዊ ውፍረትና ቁጥ የቀለበኗ መከፊውን ተያጋው በአየር ወለዱ ተሰበው የነበሩትን ዖገደኞች አሰና ሬው የወለዱን ለአበዮቱ ወጋፈኝነን ያበጋቀ በዙሃኑ የአየር ኃይል ወለቆ ለባሾች ናቸው ።



ሌሎችም ተመሳሳይ ፖሊሲዎች እንዳሉ ለመጥቀስ ሲቻል፣ ስፒገበር ግን በአየር ኃይል በዙሃን ወለቆ ለባሾች ዘገዶ አንደም ጊዜ ተወዳጅነት ያልነበረው የሰሰይ ሀብቴ ወገደል አየር ኃይለን በሙሉ እንዳስበጠው አንዳለ ደርጃ እንደሚያው ማቀረቡ ኹሸ መሠረቱ ቢስ ነው እርግጥ ስፒገበር በአየር ኃይል ስም ለማሰማት የፈለገው ድምጽ አለ ። ይኸውም ቀርገፄ እንጂ ሥራ ገና ያልተነካው የ"ማፍያ"ን የበሰበሰና የተያዠ ድምጽ ነው ። የማፍያ ቡድን በአየር ኃይል ውስጥ በቻ ሳይወሰን ፖናለብቶም በሠራዊቱ ውስጥ ሥር ሥሩን እንደሚሠራና ለመፈነቅም በቻት ያለው መሆኑን ስፒገበር ለአሜሪካ ፖበር ቤት ማመለከቱ ግልጽ ነው ።

በጀገ ሌቸ ስፒገበር ራፖር ላይ ያቀረቡት አስተያየት የበለጠ ትርጉም ሊኖረው ይችል የነበረው አገር ቤት በሚገኙ ተራማጅ ፊት በግልጽ ውይይት ቢደረግበት ቢያጋለጡት ዎና ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም እንዲያውቀው ማድረግ ሲቻል ነበር፡፡

እንደ ስፒገበር ራፖርና ሌሎም አቢዮታችንን ለመቀለበስ የሚነሱ ሴራዎች ሰፊው ሕዝብ አውቀት እንዲጋለጥና ሕዝቡ ራሱ እርምጃ ለመውሰድ ዝግጅት እንዲያደርግ ካልተደረገ የስንዱ አገር ፀረ ኢምፔሪያሊዝም ትግል የተባካ ውጤት ሊያስገኘ አይችልም፡፡

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የስፒገበርንና ሌሎችም ሰላዮች በኢትዮጵያ አብዮት ላይ የሚፈፀሙት በመረጃ የተደገፈ ጥቃት በእጅ ሳይወድቅ እንዳልቀረ እገምታለሁ፡፡ ታዲያ እነኚህን የመሳሰሉ ጽሑፎች ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ራሱ ሕዝብ እንዲያውቃቸው ማድረግ ነበረበት፡፡ሌላው ቢቀር በመንግሥት የዜና ማሰራጫዎች ለሕዝብ ተገልፀው እንዲጋለጡ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኀይት ከፍ እንዲልና እነዚህ ጠላቶቻችን አብዮታችን ላይ የሚያደርሱትን አደጋ ለመከላከል የበለጠ የተመቸ አጋጣሚ ይኖር ነበር፡፡

አሁንም በመጨረሻ ለመግለፅ የምወደው ኢምፔሪያሊስቶች በፀረ ኢትዮጵያ ግርጋንጎች አሰፈው መላ አድሃሪያችን በማስተባበር በአገሪቱ ውስጥ ቀጥተኛ ቀለበሳ ለመፈጸም መጣደፋቸው ስለማይቀር የሕዝቡ ትግል ባጭር ጊዜ በተጥቀ እንዲደገፍ አጣዳፊ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ለተጥቀ ጥያቄ መልስ እስከጠም የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የትጥቅን ጥያቄ ነፃ እርምጃዎችን በራሳቸው መውሰድ እንደሚጀምሩባቸው አውቀው ለዚህ መነሳት አለባቸው፡፡

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፣

የውጭን ንቅናቄ ከውስጥ ሆኖ በርብሮ ለማዳከም ያደረገው ሙከራ ስላልተሳካለት አርሱን ከንቅናቄያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጉን በመሰለፍ ያለማቋረጥና ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግል ሲያካሄድ በኖረው ማህበራችንና በነዚሁም አስር ዓመታት ያለተሰጣቸውን ነፃነት በመንጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፤ከየተናጠም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መቀስቀሻ ሆነው በቆዩት በታጠቅና በትግላችን ስም መጠቀም ጀምረዋል። የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም ታጠቅና ትግላችን በአስር ዓመት ቆራጥ ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው።እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያቃተውን የኢትዮጵያ ተማሪያችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ወንገበር በመንዛት ለማፋፋም ነው።ይህም እንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው። ለማንኛውም፣የተለመደው የመጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያልያዙ፣የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር አባልነትን የማያመለክቱ ገን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንድታውቁልንና እንድታስታውቁልን እንጠይቃለን።ለእነዚሁ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው ‥ዓለም ዓቀፍ ፊዴሬሽን ‥ በሚባል ስም የታወቀው የነ አሰፋወሰን — መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው።

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደ
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በስኢተማ የመጽሄት አዘጋጅ ቦርድ